# 6

# ላሊሶ

## የወርቅ ቅጠሎች

*«እኔ በመንገድ ሳለሁ እግዚአብሔር ወደ ጌታዬ ወንድሞች ቤት መራኝ::»*

ዘፍጥረት 24:27

*«ምንም ቅርብ ቢሆን እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ምድር መንገድ አልመራቸውም፤ . . . ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን በዙሪያ መንገድ በኤርትራ ባሕር ባለችው ምድረ በዳ መራቸው::»*

ዘጸአት 13:17-18

*«በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና::»*

ሮሜ 8:14

ባለቤቴ ወደ ክሊኒኩ በፍጥነት እንድመጣ ማስታወሻ ስትልክብኝ ጉዳዩ ጠንከር ያለ መሆኑን አልተጠራጠርኩም:: እንደዛ ባይሆን ኖሮ፣ ከሥራ ቦታዬ እንደማትጠራኝ ግልጽ ነበር! ስደርስ ባለቤቴ በጣም የታመመች ሴት ስትመረምር ነበር:: ብዙ ሰዎች በየተራ እየተቀያየሩ በቃሬዛ ተሸክመዋት ነበር ያመጧት:: ሴቲቱ የወንጌላዊ ላሊሶ ሚስት ስትሆን፣ ለአንድ ሳምንት በከፍተኛ ራስ ምታትና ትኩሳት ስትሠቃይ ነበር የቆየችው:: ሰውነቷ «እሳት እንደ ተለኮሰበት» ሁሉ የሚያቃጥላት መሆኑን ላሊሶ ለባለቤቴ ነገራት:: የሚነዝረውን ራሷን እንደ ያዘ፣ ለቀናት ምንም ነገር ሳትመገብና ሳትናገር ነበር የቆየችው:: ትኩሳቱ እየባሰባት



በመምጣቱ አሁን በጣም ተዳክማ ነበር:: ይህ የሆነው በሸለቆው አካባቢ ከተንሰራፋው ወባ ሳቢያ ይሆን? ወይስ መንጋጋ ቆልፍ? የአንጎል ወባ?

ባለቤቴ የነርስነት ልምዷን ሁሉ ተጠቅማ ሕይወቷን ለማትረፍ ከፍተኛ ጥረት አደረገች:: የዶክተር፣ የሆስፒታል፣ የበሽታ መመርመሪያ ያለህ የሚያሰኝ ነበር! ዶክተር ያለበት ቦታ ለመድረስ በቀናት የሚቆጠር መንገድ መጓዝን ይጠይቃል:: መንገዱ ደግሞ ከወንዞች ሙላት የተነሣ የሚሞከር አልነበረም:: ምንም ዓይነት የሬድዮም ሆነ የስልክ መገናኛ አልነበረም:: ልናደርግ የምንችለው መጸለይ ብቻ ነበር:: ባለቤቴ ትኩሳቱ እንዲቀንስ ለማድረግ የምትችለውን ጥረት ሁሉ አደረገች:: የተለያዩ መድኃኒቶችን፣ ቀዝቃዛ ስፖንጅ ተጠቅማ መሥራቷን ቀጠለች:: ለተወሰነ ጊዜ ምንም ዓይነት ውጤት የሚታይ አይመስልም ነበር:: እየሞተች ያለች ይመስል ነበር:: እኛም መጸለያችንን ቀጠልን::

ለቀናት ሕይወቷ በጣር ላይ ሰነባተ:: ባለቤቴ ታይፈስ ;:ኖርባት ይሆናል በማለት መድኃኒት ሰጠቻት:: የላሊሶ ባለቤት በመጠኑ ተሻላት:: ባለቤቴ ለብዙ ቀናትና ሌሊቶች ስትንከባከባት ስለ ቆየች፣ በጣም ደከመች:: ይህም ሆኖ ጦርነቱ በድል ተጠናቀቀ:: ተስፋ ከቆረጥን በኋላ የላሊሶ ሚስት ራሷን ስታ ከቆየችበት ሁኔታ ነቅታ ቀስ በቀስ ታገግም ነበር:: እግዚአብሔር ጸሎታችንን መለሰ:: መድኃኒቱም ሠራ:: የሕክምና እንክብካቤውም ስለ ጠቀማት፣ ቀስ በቀስ ጤንነቷ እየተመለሰ መጣ:: ላሊሶና ባለቤቱ በጣም አመሰገኑን:: እግዚአብሔርንና ባለቤቴን እየደጋገሙ አመሰገኑ:: በዚህ ጊዜ ነበር ላሊሶ ቀጣዩን ታሪክ የነገረኝ::

ላሊሶ የአይዳ ጎሳዎች በሚገኙበት የጎይቢ መንደር ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ለመድረስ ይፈልጋል:: ብዙ ነብሮች ባሉበት ጫካ ውስጥ እያለ እንዲመሽበት አልፈለገም ነበር:: ወንጌላዊው ከሸለቆው በጊዜ ተነሥቶ ወደ አሥር ሰዓት አካባቢ ከጎይቢ ለመድረስ ዐቀደ::

ነገር ግን ላሊሶ በመንገድ ላይ ፖሊሶች ይጠብቁኛል ብሎ አላሰበም ነበር! በሁለት መንገዶች መገናኛ ስፍራ ተቀምጠው ነበር::

መንገዱን በጠመንጃቸው ዘግተው ስሙ ማን እንደ ሆነ፣ ከየት እንደ መጣና ወዴት እንደሚሄድ ጠየቁት:: ላሊሶ ከዚህ ቀደም ፖሊሶች ገጥመውት ስለ ነበረ ፈራ:: ለምስክርነት የሚሆኑ ሰ ዎችም በአካባቢው አልነበሩም::

ላሊሶ በአንድ ወቅት ባርኔጣውን ሳያወልቅ ሰንደቅ ዓላማን አልፎ በመሄዱ ለአምስት ዓመታት ታስሮ ነበር:: ከትልቅ እንጨት ላይ የተሰቀለውን ባንዲራ አለማየቱን ቢናገርም፣ የሚሰማው አላገኘ ም! ነገር ግን «ለአገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ ክብር እንደ ሌለው» እና «መንግሥትን እንደሚቃወም» የሚያስረዱ ክሶች ተመሠረቱበት:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለእስራት ቢዳረግም፣ ብዙ እስረኞችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ችሏል:: በመሆኑም፣ አሁን ለሚናገረው ነገር ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት በመገንዘብ፣ እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጠው በልቡ ጸለየ::

ባርኔጣውን በእጁ ይዞ፣ «ሰላም፣ ሰላም ናችሁ ወዳጆቼ? ስሜ ላሊሶ ይባላል:: የምመጣው በሸለቆው አካባቢ ካለው ከሳውላ ነው:: ወንድሜን ለመፈለግ እየሄድኩኝ ነው፣» አላቸው:: በርግጥም፣ የጠፉትንና በክርስቶስ ወንድሞቹ እንዲሆኑ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ለማግኘት ነበር የሚሄደው!

«ለምን? ወንድምህ ምን ሆነ? አሁን የት ነው ያለው?» ሲሉ ጠየቁት::

«የአባታችንን ቤት ትቶ ወደ ጨለማው ሄደ:: የጠፋ በመሆኑ፣ ፈልጌ ሳገኘውና ወደ ቤት ሳመጣው ብዬ እየሄድኩኝ ነው:: አባታችን ስለሚወደው ወደ ቤት እንዲመለስ ይፈልጋል:: እንደሚመስለኝ ተራራው ላይ ነው ያለው፣» ሲል መለሰላቸው::

«ወንድምህ ከጠፋ ቆይቶአል? ለምን ያህል ጊዜ ልትፈልገው ነው?» ብለው ፖሊሶቹ ጠየቁት::

«አዎን፣ ከጠፋ ብዙ ጊዜው ነው:: ነገር ግን ፈልጌ ወደ አባቴ እስከማመጣው ድረስ መፈለጌን እቀጥላለሁ፣» አለ ላሊሶ::

ፖሊሶቹ «ስጦታ» ብቻ እንደሚፈልጉ ላሊሶ ገባው:: መንገዱን



ለማለፍ ጉቦ እንዲሰጣቸው ጠበቁት:: ለብዙ ሰዓታት እዚያው አቆዩት:: ላሊሶ እግዚአብሔር ትዕግሥት እንዲሰጠው ጸለየ:: ምንም ዓይነት የመበሳጨት ምልክት ላለማሳየትም ተጠነቀቀ:: ጊዜ ው እየመሸ በመሆኑ፣ መሄድ ያስፈልገው ነበር! ሌሎች መንገደኞች ይመጣሉ ብሎ ቢጠብቅም፣ ብቅ ያለ ሰው አልነበረም:: ምናልባትም ፖሊስ በአካባቢው እንዳለ ተወርቶ ሊሆን ይችላል! በመጨረሻ ፖሊሶቹም ወደሚቀጥለው ከተማ ገብተው ለማደር መሄድ ስላለባቸው፣ ላሊሶ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ጠየቁት:: ላሊሶ፣ «የምሰጣችሁ ገንዘብ ቢኖረኝ ደስ ባለኝ ነበር:: ነገር ግን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በሰላም እንዲያደርሳችሁ እመኛለሁ፣» አለ:: ፖሊሶቹ እያመነቱ እንዲሄድ ፈቀዱለት:: ላሊሶም የባከነውን ጊዜ ለማካካስ እየፈጠነ ወደፊት ይገሰግስ ጀመር::

እየፈጠነ ሲጓዝ፣ ላሊሶ ከፖሊሶቹ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ እግዚአብሔር «እንደ እባብ ብልህና እንደ ርግብ የዋህ» ስላደረገው አመሰገነው:: ፀሐይ በመጥለቋ ብዙም ሳይቆይ ጨለመ:: ከአነስተኛ ወንዝ አጠገብ የምታልፈውን ጠባብ መንገድ ተከትሎ መጓዙን ቀጠለ:: ውኃ ቢጠማውም፣ ወደ ወንዙ የሚያስገባ መንገድ ሊያገኝ አልቻለም:: ውኃውም አይታየውም ነበር::

ላሊሶ በዚያን ዕለት እግዚአብሔር በሰላም እንዲያደርሰው መጸለዩንና እስካሁን ነገሮች በጥሩ ሁኔታ አለመከናወናቸውን አስታወሰ:: አሁን ጌታ በሰላምና በፍጥነት ከአንድ መንደር እንዲደርስ ሊረዳው ይችል ይሆን? ላሊሶ እየጸለየ ሳለ፣ ድንገት እግሩ ከጠርዙ ተንሸራተተና ወደ ወንዙ ውስጥ ገባ! በከፍተኛ ድምፅ ውኃው ውስጥ እንደ ወደቀ፣ መላ ሰውነቱ ራሰ! ከወደቀበት ተነሥቶ በእግሩ ለመቆም ሲታገል፣ ድንጋዮቹ መጠነኛ ጉዳት አደረሱበት:: ነገር ግን ጉዳቱ ያን ያህል ከባድ አልነበረም:: እንዴት ያለ ተአምር ነው ብሎ እያውጠነጠነ ሌላ ምን ይከሰት ይሆን? ሲል አሰበ:: መጽሐፍ ቅዱሱና ወረቀቶቹ በሚገባ ታስረው በመገኘታቸውና ውኃ ውስጥ ወድቀው ባለመበስበሳቸው ደስታ ተ ሰማው:: ላሊሶ በጨለማው ውስጥ ሆኖ ከወንዙ ለመውጣት ሲሞክር አቃተው፣ የወንዙ ዳርና ዳር ገደል በመሆኑ፣ መውጣት

ከባድ ሆነበት።

ላሊሶ በውኃ ውስጥ ወደፊት እየተንዘ በእጅ ለመያዝና ከወንዙ ተንጠላጥሎ እንዲወጣ የሚያስችለውን ቅርንጫፍ ወይም ሥር ለማግኘት ጥረት አደረገ። ለአንድ ሰዓት ያህል ጥረት ሲያደርግ ከቆየ በኋላ ቁልቁል ወደ ወንዙ የመጣ የቀጭን መንገድ መውጫ አገኘ። ከአካባቢው ሽታ ስፍራው ሰዎች ውኃ ለመቅዳት፣ ልብሶቻቸውን ለማጠብና ለእንስሶቻቸው ውኃ ለማጠጣት የሚመጡበት መሆኑን ተገነዘበ። በአቅራቢያው የመኖሪያ ቤቶች እንደሚኖሩ ስለ ገመተ፣ በተደጋጋሚ የድረሱልኝ ጥሪ አሰማ። ወዲያውም ድምጾች ወደ እርሱ እየቀረቡ ሲመጡ ሰማ። ብዙ ሰ ዎች መጡ። አንደኛው ችቦ እያበራ ነበር የመጣው። ላሊሶ ውኃው ከሰውነቱ ላይ እየተንጠባጠበ ወደ ደረቅ መሬት ወጣ። ጎይቢ ምን ያህል እንደሚርቅ ሲጠይቃቸው ያለው እዛው መሆኑን ሲነግሩት ደስ አለው!

ችቦውን የያዘው ሰውዬ ለሌሎች እንዲህ አለ። «ቀይ ሰው ከውኃው ውስጥ በሰላም ወደ እኛ መጥቷል።» ይህም በሕዝቡ መሐል የደስታ ሁካታን ፈጠረ። አንድ ሽማግሌ ደግሞ፣ «ነገርየውን ይዞ ይሆን? የወርቅ ቅጠሎቹን አምጥቶ ይሆን?» ሲል ጠየቀ።

የመንደሩ ሰዎች ጥሩዎች በመሆናቸው ወደ አንደኛው ቤተሰብ ላሊሶን በመውሰድ ከእሳት ዳር ተቀምጦ ልብሱን እንዲያደርቅ አደ ረጉት። ላሊሶ ከልብሶቹ ብዙ ውኃ ጨምቆ አስወጣ። የእሳቱ ሙቀት ደስ አሰኘው። ከቀርከሃው መከታ በስተኋላ ሴቶች ለእራት በአንድ በኩል ይቀቅሉ፣ በሌላ በኩል በቆሎ ይቆሉ፣ ስኳር ድንች ይልጡ ጀመር። ቡና በእሳቱ ላይ ተጥዶ በጀበና ውስጥ ይንፎቀፎቃል። ላሊሶ ረሃብ ተሰማው። ምግብ ከበላ ምን ያህል እንደቆየም ታወሰው!

ሌሎችም ሰዎች በመምጣታቸው ቤቱ በሰው ተሞላ። ላሊሶን እየተመለከቱ እርስ በርሳቸው ይንሾካሾካሉ። ከእነርሱ ጥቁር አብ ረቅራቂ መልክ ጋር ሲነጻጸር መልኩ ቀይ ነበር። አብዛኞቹ



የወላይታ ወንጌላውያን ቡናማ ቀለም አላቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ጠቆር ያሉ ናቸው። እንደ ሌማ፣ ዳናና ላሊሶ የመሳሰሉ ጥቂቶቹ ብቻ በጣም ቀዮች ነበሩ። ይህ ለእነርሱ ትልቅ ነገር አልነበረም። ላሊሶ ጥቋቁሮቹ የጎይቢ ሰዎች ቀይ በመሆኑና ከውኃ ውስጥ ወጥቶ ወደ እነርሱ በመምጣቱ ለምን እጅግ እንደ ተደሰቱ ሊገባው አልቻለም። እርሱ ዐቅዶ አልነበረም በዚህ ዓይነት እነርሱ ዘንድ የደ ረሰው!

ጉጉት ያደረባቸው የአካባቢው ሰዎች ገና እየገባ ለነበረው የመንደራቸው ሰው መንገድ ከፈቱለት። ሰውዬው ንግርተኛ፣ መናፍስት ጠሪና የባህላዊ መድኃኒት አዋቂ ነበር። ላሊሶን ለአፍታ ትክ ብሎ ተመለከተው። ከዚያም እጆቹን በማጣመር መዝጋትና መክፈት ጀመረ። ሁኔታው ልክ መጽሐፍ እንደ መክፈትና እንደ መዝጋት ነበር። «ቅጠሎች። ቅጠሎች። የወርቅ ቅጠሎች፣» እያለ በተደጋጋሚ ተናገረ።

ላሊሶ ሰውዬው ምን ለማለት እንደ ፈለገ ባይገባውም፣ ጠንቋዩ ከልቡ ነበር የሚጥረው። ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር መሆን አለበት ሲል አሰበ! እግዚአብሔር ጥበብና ምሪት እንዲሰጠው ጸለየ። ሕዝቡ ጸጥ ብሎ በጉጉት ይጠባበቃል። ወንጌሉን ለመስበክ መልካም አጋጣሚ! ላሊሶ ቀስ ብሎ በጥንቃቄ ይዞት የመጣውን ጥቅል ፈታ። መጽሐፍ ቅዱሱና ወረቀቶቹ አሁንም በደህና ሁኔታ ላይ መሆናቸውን በመመልከቱ ደስ አለው።

ላሊሶ መጽሐፍ ቅዱሱን በከፈተ ጊዜ ሰዎቹ የሰጡት ምላሽ አስገረመው። መጽሐፍ ቅዱሱ ጥቁር ሽፋን ቢኖረውም፣ ዳር ዳሩ ወርቃማ ቀለም ተቀብቶ ነበር። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ እጆቻቸውን በማጨብጨብ፣ «እውነት ነው! የወርቅ ቅጠሎች መጥተዋል! ሲሉ ጮሁ። ጠንቋዩ በጉልበቱ ተንበርክኮ መጽሐፍ ቅዱስን በእጁ ነካ። «አዎ፣ እውነት ነው። እውነቱ በመጨረሻ መጥቶአል። አሁን የሕይወትን መንገድ ልናውቅ እንችላለን።»

ላሊሶ ምን ማለታቸው እንደ ሆነ ሲጠይቅ፣ ጠንቋዩ እንዲህ አለ፣ «ከብዙ ዘመን በፊት አባቴ ከመሞቱ በፊት ቀይ ሰው የወርቅ

ቅጠሎችን ይዞ ከወንዝ እንደሚወጣ ትንቢት ተናግሮ ነበር:: የወርቅ ቅጠሎቹ የሕይወትን መንገድ የሚያሳየንን እውነት የሚያመለክቱ ናቸው:: ለብዙ ጊዜ ይህንን እውነት ስንጠብቅ ቆይተናል:: አሁን አንተ መጥተህልናል::» (በጎይቢ መጻሕፍትን ለመግለጽ የሚያስችል ቃል ስላልነበረ፣ የመጽሐፍ ገጾችን ለማመልከት ቅጠሎች የሚለው ቀራቢ ቃል ነበር::)

ላሊሶ ይህንን አስመልክቶ ለእኔ ሲናገር፣ «ይህ የእኔ ሥራ አልነበረም:: እግዚአብሔር ያደረገው ነው:: ሁሉም የእርሱ ዕቅድ ነበር:: ሰዎቹን ያዘጋጀው እርሱ ነው:: እውነትን ሲጠብቁ ነበር:: የእውነትን መንገድ ለማወቅ ፈለጉ:: እኔ መልእክተኛ ብቻ ነበርኩ:: ከእኔ የሚጠበቀው መናገር ብቻ ነበር:: በቀጣዩ ዓመት እጅግ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ:: ጠንቋዩ ሰይጣንን በመካድ ወደ ኢየሱስ ተመለሰ:: በብዙ መንደሮች አብያተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ:: በርካታ አዳዲስ አማኞች ተጠመቁ:: ሌሎች ወንጌላውያን እነዚህን አዳዲስ አማኞች በማስተማር ሊረዱኝ መጡ:: እግዚአብሔር ይመስገን ሥራው አሁንም ስለ ቀጠለ፣ መልካሙ የምስራች በጎፋ ተራሮችና ሸለቆዎች ላይ እየተነገረ ነው» አለ::

እኔም ራሴን በመነቅነቅ ከላሊሶ ጋር ከመስማማት ውጭ የማደርገው ነገር አልነበረም:: አብረን እግዚአብሔርን ስለ ጸጋውና ሰዎችን ስለሚለውጠው የወንጌሉ ኃይል አመሰገንን:: ስለ ታማኝና ቆራጥ የወላይታ ወንጌላውያንም እግዚአብሔርን አመሰገንኩት:: ጌታን በመታዘዝ በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ሆነው ለሚጠባበቁ ሰዎች የደኅንነትን መልካም የምስራች ለመውሰድ በሁሉም ነገር በአደጋ መካከል አልፈዋል:: አንዳንዶች የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስን ለማግኘት ብዙ ጠብቀዋል - በጣም ብዙ!



# 7

# አኒሳ

## ከጌታ ዘንድ ወሬ ሰማን

*«ከእግዚአብሔር ዘንድ ወሬ ሰምተናል፤ መልእክተኛ ወደ አሕዛብ ተልኮ...»*

አብድዩ 1

*«እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ:: ይህም ዝና ስለ እርሱ በይሁዳ ሁሉ በዙሪያውም ባለች አገር ሁሉ ወጣ::»*

ሉቃስ 7:16-17

አንድ ወጣት ጠንቋይ፣ «አንተ ኢየሱስ ነህ?» ሲል ጠየቀኝ:: እርሱና አብሮት የነበረው ሰውዬ ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩት ነጭ እኔው ነበርኩ:: በጥያቄው ግራ ተጋብቼ ቆምኩ:: መልሶ እንደገና፣ «አንተ ኢየሱስ ነህ?» ሲል ጠየቀኝ:: «አይደለሁም:: እኔ ኢየሱስ አይደለሁም:: እርሱ ጋ ለመድረስ ብዙ ይቀረኛል፣» አልኩት:: ግልጽ ቅሬታ እየታየባቸው ሁለቱ ሰዎች እርስ በርስ ተያዩ::

«የለም እኔ ኢየሱስ አይደለሁም:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ እዚህ ይኖራል፣ እኔም እርሱን አውቀዋለሁ:: እርሱን እንዳስተዋውቃችሁ ትፈልጋላችሁ?» አልኳቸው:: ደስ አላቸው:: ይህንን ነበር ማወቅ የፈለጉት:: ከዚያም በኢትዮጵያ ባህል መሠረት፣ «እስኪ ቁጭ በሉና በወጉ እንነጋገር፣» ስል ጠየቅኩአቸው:: ቁጭ አሉ:: ለቀጣይ ሦስት ሌሊቶችና ሁለት ቀናት በአብዛኛው ስለዚሁ ጉዳይ ተነጋገርን::

ጊዜው ሰዎች በቀላሉ እኛን ለመጠየቅ የሚችሉበት አልነበረም::

ባለቤቴና እኔ አገራችን አውስትራሊያ እረፍት አድርገን መመለሳችን ነበር:: በዚህ ጊዜ እኛ በምንሠራበት የጎፋ አውራጃ ውስጥ ከፍተኛ ስደት ተነሥቶ ነበር:: በጥቂት ወራት ውስጥ፣ በተለያዩ መንደሮች ውስጥ የነበሩት ሃያ «የጸሎት ቤቶች» ተቃጠሉ:: 1500 አዳዲስ አማኞች ቤታቸው በመቃጠሉ ምክንያት ቀዬአቸውን ለቅቀው ተበታተኑ:: በመቶዎች የሚቆጠሩ አማኞች ታስረው ያለ ምንም ክስ ለብዙ ወራት ተሠቃዩ:: ግርፋት፣ ድብደባና በሰንሰለት መጠፈር ደረሰባቸው:: አንዳንዶችም ተገደሉ::

ብዙ ክርስቲያኖች መሬታቸውን፣ ከብቶቻቸውንና እህላቸውን ተነጥቀው ለድህነት ተጋለጡ:: በሌላ ስፍራ ሦስት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከዛፍ አጠገብ ተሰልፈው በጥይት ተደብድበው ተገደሉ:: በሌላ መንደር ደግሞ አንድ ወጣት በዱላ ተደብድቦ ተገደለ:: በእስር ቤት ደግሞ ብዙዎች ተረገጡ:: አንደኛው አማኝ በወታደሮቹ ክፉኛ ተረግጦ ተገደለ:: ረሃብ፣ ታሞ መሞት፣ ለተለያዩ ችግሮች መጋለጥና ግፍን መጋት ዕጣ ፈንታቸው ሆነ:: አንዳንድ ክርስቲያኖች በሌላ ስፍራ ባሉ ዘመዶቻቸው ዘንድ መጠጊያ አገኙ:: ሌሎች ደግሞ በየዋሻው ወይም ጊዜያዊ መጠለያ ሠርተው በየጫካው ተጠለሉ:: በተለይ ሕፃናት ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ዘግናኝ ወቅት ነበር:: እኛም በተቻለን መጠን ምግብና መድኃኒት በማቅረብ እገዛ ለማድረግ ሞከርን:: አንዳንድ ወዳጆች ለእስረኞችና ለተበተኑ ቤተሰቦች ምግብ መስጠታቸውን ቀጠሉ::

ከዚያ በኋላ ዝናቡ ጀመረ! ብዙውን ጊዜ የበልግ ወራት ዝናብ ለስድስት ሳምንታት ይቆያል:: ከዚያ በኋላ ለሁለት ወራት ያህል ጋብ ይልና የክረምቱ ዝናብ ይጀምራል:: ይህ ዝናብ ለቀጣይ ሦስት ወራት የሚቆይ ይሆናል:: በዚያን ዓመት ግን ዝናቡ ለስምንት ወራት ያለማቋረጥ ሲዘንብ ቆየ:: ይህ ከገጠሙን ዓመቶች ሁሉ በጣም ዝናብ የበዛበት ነበር:: በበልግ ወራት የመጣው ዝናብ መብረቅና ነፋስ የቀላቀለ ሲሆን፣ ወንዞች ሁሉ በፍጥነት ነበር የሞሉት::

አንድ ቀን ኃይለኛ ማዕበል አካባቢውን በመምታቱ በቡልቂ ከተማ ውስጥ የሚገኙትን በመቶዎች የሚቆጠሩ ቤቶችና ሱቆች ጠራርጎ ወሰደ:: የነጎድጓዱ ማጓራትና የመብረቁ ብልጭታ፣ እንዲሁም የዝናቡ ኃይልና የነፋሱ ፉጨት ሁላችንንም አስፈራን:: እንዲህ ያለ ማዕበል ታይቶ አይታወቅም! በተዘጉት በሮችና መስኮቶች ዘልቆ የሚገባውን ዝናብ ለማስቆም እንችል ዘንድ ፎጣዎችን ለመጠቀም ተገደድን:: ጥረታችን ግን ከንቱ ነበር!

ድንገት ከፍተኛ ነጎድጓድ በመጣሉ ቤቱ ተነቃነቀ፣ መብረቅም ከሰማይ ወረደ:: ድንገት የቤታችን ጣሪያም ተመትቶ ፈራረሰ:: የጣሪያው ልዩ ልዩ ክፍሎች በድንገት ፈራርሰው ከብዙ መቶ ሜትሮች ማዶ ወዳደቁ:: ቆርቆሮዎቹ በኃይለኛ ነፋስ ተገንጥለው በረሩ:: ከእነዚህ ቆርቆሮዎች አንዳንዶቹ ከሩቅ ስፍራ ሲገኙ፣ ሌሎች ጭራሽ አልተገኙም:: በጭቃው ኮርኒስና ግድግዳ እየሰረሰረ ይወርድ ጀመር:: ቤቱ ገና አዲስ ቀለም የተቀባ ነበር:: አሁን ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር ልጆቻችንን ሰብስበን ከበሩ ላይ መቆም ብቻ ሆነ:: የኮርኒሱና የግድግዳው ጥቁር ጭቃ ወድቆ እያየን በአልጋችን፣ በወንበሮችና በጠረጴዛዎች ሁሉ ላይ ተከመረ:: ቤቱ ውስጥ ቢያንስ አሥር ሳንቲ ሜትር የሚሆን ጎርፍ ተፈጠረ:: የዚያን ቀን ሌሊት የማይመች ነበር ማለቱ ሁኔታውን በሚገባ አይገልጸውም! ገና ሌሎችም ችግሮች ይጠብቁን ነበር::

ከቤቱ አጠገብ ሁለት ተጨማሪ ክፍሎችን ገንብቼ ነበር:: እያንዳንዱ ክፍል ሦስት ሜትር በሦስት ሜትር ሆኖ ጠፍጣፋ ጣሪያ ነበረው:: ግድግዳው ገና ጭቃ ተመርጎና ተለስኖ ማለቁ ነበር:: እስኪደርቅ ድረስ ብዙ ጊዜ እንደሚወስድ ግልጽ ነበር:: እነዚህ ሁለት ያልደረቁ ክፍሎች ማዕበሉን ተቋቁመው በመትረፋቸው ቤታችን እስኪጠገን ድረስ ወደዚያ ተዛወርን:: የሚገርመው ከቤቱ ቅዝቃዜና እርጥበት ባሻገር፣ በዚያን ዓመት ማናችንም አልታመምንም:: ጉንፋን እንኳ የያዘው ሰው አለመኖሩን ስናይ፣ ጌታ እንደ ጠበቀን ግልጽ ነበር:: አንዳንድ ዕቃዎቻችን ስለ ጠፉብንና ቤታችንም ስለ ተበላሸ፣ መከራ ከሚቀበሉ ክርስቲያኖች ጋር የነበረን ግንኙነት ከወትሮው በበለጠ ተጠናከረ:: ይህ በሌላ መንገድ ልናገኝ የማንችለው ጥብቅ ቅርርብ ነበር:: ጌታ መከራና

ችግር እንደማይደርስብን አልተናገረም:: ነገር ግን በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ አብሮን እንደሚሆን ቃል ገብቷል:: በዚያን ዓመት የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን ክርስቲያኖች ከእኛ ጋር ሆነው አረጋገጡ::

እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ በመስጠት፣ ከወላይታ 42 ኢትዮጵያውያን ወንጌላውያንን አምጥቶ ነበር:: እነዚህ ወንጌላውያን ወንጌሉን በመስበክ ትናንሽ አብያተ ክርስቲያናትን መሠረቱ:: ከዚያም ታላቅ ስደት ተነሣ:: በዚህ ጊዜ 41 ወንጌላውያንና ሌሎች በርካታ አማኞች ታሰሩ:: አንድ ወንጌላዊ ብቻ ሳይያዝ በመቅረቱ በየቦታው ይታደን ጀመር:: ናና በማሎ ተራሮች ነበር የሚኖረው:: ይህም ስፍራ ከእኛ የሦስት ቀን መንገድ ነበር:: እርሱ ሁልጊዜም ሊያስሩት ሲመጡ አይገኝም ነበር!

ናና ከልጁ ጋር ሁልጊዜም ለታሰሩት ወንጌላውያንና አማኞች፣ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች በየዋሻውና በየጫካው ተበትነው ለተደበቁት ክርስቲያኖች ምግብ እያመላለሰ ሁልጊዜም በመንገድ ላይ አይታጣም ነበር:: የእስር ቤቱ ዘበኞች ለይተው አያውቁትም:: አይተውትም አያውቁም! ናና ለእስረኞች መድኃኒትና መልእክት ያደርሳል:: ለቤተሰቦቻቸውም እንዲሁ መልእክቶችን ያመጣ ነበር:: ናና እንዴት እንደማይያዝ የሚገርም ነበር:: ብዙውን ጊዜ ባለሥልጣናት፣ ፖሊሶች፣ ቄሶችና ጠባቂዎች በመንገድ ላይ አልፈውት ሲሄዱ የሚያዩት አይመስልም::

ከዚህ ሁሉ ስደትና ሥቃይ ባሻገር፣ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ በመሥራቱ አንዳንዶች አሁንም ባለሥልጣናት ለማጥፋት የሚሞክሩትን «አዲስ ትምህርት» ለመስማት ይፈልጉ ነበር:: አማኞችም በሚቻላቸው መጠን በቤታቸው፣ በጫካ ውስጥና በዛፍ ጥላ ሥር ሆነው ይጸልዩ ነበር:: ከሁሉም በላይ ለዘመዶቻቸውና ለጓደኞቻቸው ይመሰክሩ ነበር:: እንደ ቀድሞይቱ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ. 8:1-8)፣ የጎፋ ቤተ ክርስቲያን በተበተነችበት ሁሉ የወንጌሉን ዘር አሰራጨች:: እግዚአብሔር በእነርሱ አማካኝነት የብዙዎችን ሕይወት ይነካ ነበር:: በዚህ መንገድ ባይሆን ኖሮ ሊሰሙ የማይችሉ በእስር ቤቶችና በፍርድ



ቤቶች የሚገኙ ሰዎች፣ እንዲሁም አስተዳዳሪዎች፣ ባለሥልጣናትና ገበያተኞች ሁሉ ወንጌሉን በመስማታቸው ቤተ ክርስቲያን እየተባዛች ሄደች::

ዝናብና ጭቃ በበዛበት፣ ቤቶች ፈራርሰው ዛፎችም ተነቃቅለው በወደቁበት፣ የቤት ጣራና ቆርቆሮዎች በያሉበት በተንጠባጠቡበት ለጎብኝዎች በማይመቸው በዚያን ወቅት ሁለት ሰዎች ከወደ ምዕራብ አቅጣጫ ብቅ አሉ:: በቡልቂ ወዳለው የሚሲዮን ጣቢያችን ለመድረስ ለሁለት ቀናት ተኩል ተጉዘው ነበር የመጡት:: አንድ የሚያስደንቅ ታሪክ ሰምተው እውነትነቱን ለማረጋገጥ ብለው ነበር የመጡት! ከሩቅ የሸለቆ መንደራቸው ሆነው ነበር ወሬውን የሰሙት:: ለእነርሱ ይህ «ከጌታ ዘንድ የመጣ ወሬ» ነበር::

አንድ ቀን አንድ ነጋዴ ገበያ ውስጥ ልብሶችን ሲሸጥና ቡና ሲገዛ አዩ:: ነጋዴው የሰዎችን ፍላጎት ለመቀስቀስና ሰብሰብ ብለው እንዲሰሙት ለማድረግ ሲል በመንገድ ላይ ከሌላ ሰው የሰማውን ታሪክ ተናገረ:: ታሪኩን ለእርሱ የተናገረውም ሰው ከሌላ ሰው ነበር የሰማው:: እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን በተናገረ ቁጥር የተወሰኑ ነገሮች ተጨምረውበት ነበር:: ሰዎቹ ታሪኩ እውነት መሆኑን ስለ ተጠራጠሩ ራሳቸው እውነትነቱን ለማረጋገጥ ፈለጉ!

ከሁለቱ ሰዎች በዕድሜ ወጣት የሆነው ኦኒሳ ጠንቋይ ነበር:: ሙያውን የወረሰው ከአባቱ ነበር:: ኦኒሳ መተጣጠብ፣ ጸጉሩንና ጥፍሮቹን መቆረጥ ከማቆሙ በፊት በራሱ ላይ የከብት እበት መቀባት ጀመረ:: በትከሻው ላይ ጣል ከሚያደርገው የነብር ቆዳና ቡቱቶ ቁምጣ በቀር ልብስ አይለብስም ነበር:: በእድሜ የገፋው ገብሬ ደግሞ ባሪያ ነበር:: ወላጆቹ የሀብታም ባላባት ባሪያዎች ስለ ነበሩ፣ ገብሬ ባሪያ ሆኖ ነበር የተወለደው:: ባርነት በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ የተከለከለበት ዘመን በመሆኑ ገብሬ «አገልጋይ» እየተባለ ይጠራ ነበር::

የሰሙት ወሬ ኢየሱስ የተባለ አንድ ነጭ በቡልቂ አካባቢ በሚገኝ ተራራ ላይ እንደሚኖርና ይህ ሰው አዳዲስ ሰዎችን እንደሚፈጥር ነበር:: ይህ ኢየሱስ እጆቹን በወንድ፣ ሴት፣ ልጅ

ብለው ተባረሩ። የሚሲዮን ንብረት፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮችና ትምህርት ቤቶች ሁሉ ተወረሱ። አንዳንድ ክርስቲያን መሪዎች ተ ገደሉ። በሺዎች የሚቆጠሩ አማኞች ታሰሩ። ግራ እጃቸውን ጨብጠው ወደ ላይ በማንሣት የኮሚኒስቶችን መፈክር ለማሰማት ያልፈለጉ ሁሉ ለዓመታት ወኅኒ ቤቶች ውስጥ በሰበሱ። ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው፣ እንከተለዋለን አሉ። ይህንን ማድረግ በጊዜው ውድ ዋጋ የሚያስከፍል ነበር።

ተካ ወደ ገሊላ ተራሮች በዓይኑ እያማተረ ነበር። ናና ግን በቅርቡ የላስካ መንገድ መሄድ አለብን አለ። ከኋላችን ዕቃችንን ጭነው የሚመጡት ሰዎች ባልተለመደው መንገድ መሄዳችንን ለማወቅ አይችሉም ነበር። እየረፈደ ሄደ። እንጠብቃቸው ይሆን? የሚል አሳብ ተነሣ። እንደዚያ ብናደርግ፣ ጫካ ውስጥ ይመሽብናል። ያ ደግሞ መልካም የማይሆን ነገር ነው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ግልጽ ምሪት እንዲሰጠን መጸለይ ነበረብን። ግን አልጸለይንም። በላስካ በኩል ብንሄድ ይሻላል ብለን ደመደምን። እዛ ስንደርስ ገበያው ይበተናል ብለን አሰብን። ተካ እያመነታ ተ ስማማ።

ተካ እንደተለመደው ወደፊት አልገሰገሰም። ነገር ግን «በግድ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄድ እንደ ተደረገ ልጅ» እያቅማማ በዝግታ ያዘግም ጀመር! እየተጨነቀና እየተበሳጨ ልክ አይደለም አለ። አብረን በመጓዝ ከገበያ የሚመለሱትን ብዙ ሰዎች አገኘን። ገበያው ቦታ ላይ ስንደርስ ግማሽ የሚሆነው ሕዝብ ተበትኗል። ነገር ግን በጥቂት መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አሁንም የቡና፣ የጥራጥሬና የእንስሳት ግብይት በማካሄድ ላይ ነበሩ። ብዙዎች ኃይለኛውን አረቂ በመጠጣታቸው ምክንያት ጸቦች መከሰት ጀም ረው ነበር። ይህ እዛ ለመገኘት እጅግ የማይመች ጊዜ ነበር። የገበያውን ጥግ ጥግ ይዘን በመሄድ ለማለፍ ተቃረብን። በዚህ ጊዜ አንድ ሰውዬ፣ «ሚሲዮን» ብሎ ሲጣራ ሌሎች ካድሬዎች ተ ሯሩጠው ደረሱብን። ተንኮለኛና ጠበኛ የሆነው መሪያቸው ሞቅ ብሎት ነበር። እንድንቆም አዘዘን። ስንቆም ሰዎች ይጎትቱን ጀመር። ከመጠጥ ቤቶች የሚወጡ ብዙ ሰዎች «ነጭ፣ ሚሲዮን» እያሉ መጮህ ጀመሩ። የዛቻ እሩምታ ለቀቁብን። «ግረፏቸው! ግደሏቸው!» ይሉ ጀመር። መሪው ሕዝቡን በማነሣሣቱ ወዲያው «ግደሏቸው! ግደሏቸው! ግደሏቸው!» የሚል ጩኸት በረከተ።



ተካን ዘወር ብዬ ሳየው፣ «ብዬህ ነበር። ሁልጊዜም ላስካ ችግር አያጣውም» የሚል ፊት አነበብሁበት። በመጠጥ ኃይል የተ ጋጋሉት ካድሬዎች በሕዝቡ መሐል እየገፈታተሩ ይዘውን ሄዱና ከአጥር ጥግ አስቆሙን። የካድሬዎቹ መሪ ጠመንጃ እንዲመጣለት በመጠየቁ ዘጠኝ ካድሬዎች ከቀትር ጀምሮ በመጠጥ እንደ ተ ሟሟቁ መጥተው ተሰለፉለት። ሕዝቡ ጸያፍ ቃላትን ሲወ ረውርብንና ሲተፋብን ሳለ ካድሬዎቹ ለተኩስ ተዘጋጁ። ነገሮቹ አስከፊ መልክ በመያዛቸው ሁላችንም ወደ ጌታ ልንሄድ ተቃርበናል ብለን አሰብን።

ይህ ሁሉ ለእኔ እውነት አልመሰለህ አለኝ። ሁሉም ነገር በዝግታ የሚጓዝ ይመስላል። ድንገት የሚያስገርም ሰላም ልቤን ሞላው። ለመሞት መቃረቤን ሳውቅ ትልቅ ሰላም ተሰማኝ። ወደ መንግሥተ ሰማይ የቀረብኩ ሲመስለኝ፣ የማይገለጽ ደስታ ተሰማኝ። «በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ። ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» የሚለው የጌታ የተስፋ ቃል ትዝ አለኝ። ከአጥሩ ኋላ ሆነው ሰዎች ይሰድቡናል። ከፊታችን ያለው ሕዝብ «ግደላቸው! ግደላቸው! ግደላቸው!» ፈጽሞ እንደ እብድ እያደረጋቸው ማለታቸውን ቀጥለዋል። የካድሬዎቹ መሪ እጁን እንደ ጨበጠ ክንዱን በአየር ላይ ወድሮ፣ «አምላካችሁ ሞቷል! «አምላካችሁ ሞቷል! ኢየሱሳችሁ ሞቷል! ማርክሲዝም ለዘላለም ይኑር!» አለ። ሽጉጡን ሲያወጣ ሲንጫጫ የነበረው ሕዝብ መበተን ጀመረ። ሦስቱ ከበስተቀኜ በነበረው ናና ላይ፣ ሦስቱ በስተግራዬ በነበረው ተካ እና ሦስቱ ካድሬዎች በእኔው ላይ መሣሪያዎቻቸውን አነጣጥረው ለመተኮስ ተዘጋጁ። ሁኔታው በሕልም ውስጥ የሚፈጸም ይመስል ነበር። የጌታ ሰላም ልቤን ሞልቶታል። ተካና ናናም እንዲሁ በሰላም ተሞልተው ነበር።

«ተዘጋጅ» ሲል ጠመንጃዎች ወደ ላይ ተነሡ። «አልም»

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ እኔ ያንተ ነኝ።»

ወይም አዋቂ ላይ ያደርጋል:: ከዚያም ሰዎቹን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ካዞረ በኋላ አንዴ ያሽከረክርና ልዩ ሰዎች አድርጎ ይለውጣቸዋል የሚል ወሬ ሰምተው ነበር! ይህን የሚያደርገው ኢየሱስ እኔ መሆኔን ለማወቅ ነበር የፈለጉት::

በዚህ ጊዜ፣ ወንጌላዊ ናና በሰሜናዊ ተራሮች አንድ ሳምንት ከፈጀ የአገልግሎት ጉዞው መመለሱ ነበር:: ሁሉን ነገር አጥተው በኀዘንና በችግር ላይ ለነበሩት ሰዎች ምግብና ልብስ ሲያዳርስ ነበር የቆየው:: ለእነዚህ ሰዎች በመጸለይና በማጽናናት የሚችለውን ያህል የመጠለያ ድጋፍ እንዲያገኙ ጭምር ረድቶአቸው ነበር:: ናና ደክሞ ቤት ሲገባ ለባለቤቱና ለቤተሰቡ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ፣ እግዚአብሔር በሰላም ስላመጣው ተንበርክኮ አመሰገነው:: በዚያን ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ ተኝቶ አደረ::

ጠዋት ናና መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነብና ሲጸልይ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ፣ «ወደ ሚስተር ማክሊላን ዘንድ ሂድ» አለው:: ናናም፣ «እሺ፣ ጌታ ሆይ፣» ሲል መለሰ:: ነገር ግን አልሄደም:: ማታ እንደገና ለጸሎት ሲንበረከክ የጌታ መንፈስ ወደ እኛ መምጣት እንዳለበት አጥብቆ አሳሰበው:: ነገር ግን ደክሞት ስለ ነበረ ወደ እኛ ሳይመጣ የሰላም እንቅልፍ ተኝቶ አደረ:: ጠዋት የጌታ መንፈስ «አሁኑኑ ወደ ሚስተር ማክሊላን ሂድ፣» አለው:: ናና ሚስቱ በቡልቂ እስር ቤት ውስጥ ላሉት እስረኞች የጋገረችውን ቆጮ ጠቀለለ:: በፍጥነት እየተራመደ በመሄድ ከኦኒሳና ገብሬ ግማሽ ሰዓት ያህል ዘግየት ብሎ ቡልቂ ደረሰ!

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናትና ሦስት ሌሊቶች ናና እና እኔ ለኦኒሳና ገብሬ የወንጌሉን ታሪክ የመናገርና ከክርስቶስ ጋር የማስተዋወቅ ዕድል አገኘን:: ያስተዋወቅናቸው አንድን ነጭ ሳይሆን፣ ለእኛ ለመሞት ሲል ሰው የሆነውን የክብር ንጉሥ ጌታ ኢየሱስን ነበር:: ሁለቱ ሰዎች ወንጌሉን አምነው ክርስቶስን ተቀበሉ:: በጥቂት ሰዎች ፊት እጆቻቸውን ወደ ላይ አንሥተው ሰይጣንን፣ የደም መሥዋዕቶችን፣ ክፉ ሥራዎችንና ኃጢአታቸውን ሁሉ ካዱ:: አሁንም ሁለት እጆቻቸውን አንሥተው፣ «ሰይጣንን በመካድና ኢየሱስ ለኃጢአቴ የሞተ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን



በማመን አዳኜ እንዲሆን ሁለት እጆቼን አንሥቼ እጠይቀዋለሁ:: ከእንግዲህ ወዲህ በፍጹም አልክደውም፣» አሉ:: ሁለት እጆችን ማንሣት ሙሉ በሙሉ «የመማረክ» ምልክት ነው::

እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች ልብ ውስጥ ስለ ሠራው የማዳን ሥራ እጅግ አመሰገንነው:: ወደ ወንዝ ወረዱና ኦኒሳ ሰውነቱን ታጥቦ፣ ፀጉሩን ተላጭቶ፣ ጥፍሮቹን ቆራርጦ በውስጡ በክርስቶስ አዲስ ሰው እንደ ሆነ ሁሉ፣ በውጭ ሰውነቱ ተለውጦ መጣ! የሰሙት ወሬ ከጌታ ዘንድ መሆኑን ተገነዘቡ፣ አዲስ ሰው የመፍጠር ተግባር የእርሱ ነውና:: ምክንያቱም፣ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል» (2ኛ ቆሮ. 5:17):: ከመሄዳቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱስ እንድንሰጣቸው ጠየቁን:: ማንበብ ባይችሉም፣ የቃሉን እውነት አምነው ነበርና!

መጽሐፍ ቅዱስ ተቀብለው ወደ ቤታቸው ጉዞ ጀመሩ:: ወደ እኛ ለመምጣት ሁለት ቀናት ተኩል ብቻ ነበር የፈጀባቸው:: አሁን ግን በየመንደሩ፣ በየገበያውና በየመስቀለኛ መንገዱ በመቆም ወሬው እውነት መሆኑን ሲመሰክሩ በመቆየታቸው የመልስ ጉዞው ስምንት ቀናት ፈጀባቸው:: በርግጥ ኢየሱስ ሰዎችን አዲስ ያደርጋቸዋል:: እነርሱንም እንደዚያ ነበር ያደረጋቸው:: አሁን አዲስ ሰው ሆነዋል:: በመለወጣቸው እጅግ ተደስተው ሰዎች ሁሉ አዳኛቸውን እንዲያውቁላቸው መመስከር ጀመሩ:: ለክርስቶስ ወንጌላውያን ሆኑ!

የኋላ ኋላ የራሳቸው ጎሳዎች ካሉበት ሽለቆአማ መንደራቸው ደ ረሱ:: ሊነገር የሚገባ ታላቅ ታሪክ እንደ ያዙ! አዳዲስ ሰዎችን ስለሚፈጥረው የእግዚአብሔር ልጅ ለመናገር ወደ ተለያዩ የመንደራቸው ክፍሎች ተጓዙ:: በኦኒሳና ገብሬ ሕይወት ውስጥ የተፈጸመውን ለውጥ በመመልከታቸው፣ የመንደሪቱ ነዋሪዎች በሙሉ ተደነቁ:: ብዙ ሰዎች ይህንን ሰላምና ደስታ እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠይቁአቸው ጀመር:: በክርስቶስ ከኃጢአትና ከጨለማ ነጻ መውጣት እንደሚቻልና ክርስቶስ ከሰይጣን የበረታ ስለ መሆኑ ሲናገሩ ጠንቋዮቹ ሁሉ ተበሳጩ:: ከፍርሃት ነጻ ስለ መውጣትና የእግዚአብሔር መንግሥት ሲናገሩ ሀብታሞቹ የመሬት

ከበርቴዎች ተበሳጩ። ይህ አዲስ ትምህርት በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እነርሱን ሲፈሩ የኖሩትን ሰዎች ከእነርሱ ቁጥጥር ነጻ ሊያወጣቸው ይችል ነበር። ስለዚህ በፍጥነት እነዚህን ሰዎች ለማስቆም እርምጃዎችን መውሰድ ጀመሩ!

የመሬት ከበርቴዎች፣ የኦርቶዶክስ ቄሶችና ጠንቋዮች ኦኒሳና ገብሬ የአካባቢውን «ጸጥታ እንዳደፈረሱ» እና «ዐመፅ እንደ ቀሰቀሱ» በመግለጽ እንዲታሰሩ አደረጉ። ኦኒሳና ገብሬ ስለ ወሬው በሰሙበት የገበያ ሜዳ ተደብድበው በጭቃ ውስጥ ተዘፈቁ። እያንዳንዳቸው 100 ጅራፍ ተገረፉ። ከትከሻቸው አንሥቶ ጀርባቸው ተተለተለ። በቁስላቸው ውስጥ ጨው ተጨመረበት። እጅ እግራቸው ተጠፍሮ እስር ቤት ውስጥ ተጣሉ። ይህ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ያደርጋል የሚል እምነት ነበራቸው! ይህን «አዲስ የሕይወት መንገድ» እከተላለሁ ብሎ ለሚያስብ ሰው ይህ ጥሩ ትምህርት ይሆናል ብለው ገመቱ።

ኦኒሳና ገብሬ ሁሉንም ነገር አጡ። ከፍተኛ የሕመም ስሜት እያሠቃያቸው ርቃናቸውን ፍርድ ከተሰጣቸው ነፍሰ-ገዳዮች ጋር ታሰሩ። እስረኞቹ ምንም ጥፋት ላልፈጸሙት ለእነዚህ ሰዎች አዘኑላቸው። ኦኒሳና ገብሬ ለዛጠኝ ወራት ታስረው ቆዩ። ቤቶቻቸው ተቃጠሉ፣ እንስሶቻቸው ታረዱ፣ መሬታቸው ተወሰደ። ሚስቶቻቸው ለሌሎች ሰዎች ተሰጡ። ልጆቻቸው ለሰዎች ለባርነት ተሸጡ። ልጆቻቸውን በጭራሽ እንደገና ሊያገኙአቸው አልቻሉም። ምናልባትም ከአገር ውጭ ለባርነት ተሸጠው ይሆናል።

ለዘጠኝ ወራት በአሰቃቂ እስራት ከቆዩ በኋላ ለቀቁአቸው። በእስር ቤቱ ውስጥ ላሉት ነፍሰ-ገዳዮች ሁሉ ወንጌሉን መመስከርና የጸሎት ስብሰባ ማድረግ ጀምረው ነበር። ስለዚህ ውጭ ወጥተው የሚፈጽሙት ጥፋት ከዚህ የከፋ አይሆንም የሚል ግምት አድሮባቸው ነበር ያስወጡአቸው! ረዥሙን የእስራት ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲወጡ፣ ከነፍሰ-ገዳዮች አንዳንዶቹ ወደ አካባቢያቸው በሜሄድ ቤተ ክርስቲያን መሥርተው በመሪነት ማገልገል ጀመሩ።

ኦኒሳና ገብሬ ሲለቀቁ ናና እና ማሄን ጨምሮ አያሌ



ወንጌላውያን በዚያ አካባቢ ወንጌልን ለመመስከር ጉዞ ጀመሩ። እኔም ራሴ እጅግ የከፋትን ኃጢአተኞች ወደ ቅዱስነት ስለሚለውጠው የእግዚአብሔር ልጅ ለአሪ ሕዝብ ለመናገር በተራራዎቹ መካከል አያሌ ጉዞዎችን አደረግሁ። ገብሬ ከደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ የተነሣ የጤንነት ቀውስ ተፈጠረበት። ከእስር ቤት ከወጣ ከአንድ ዓመት በኋላ ወደ ጌታ ሄደ። ከመሞቱ በፊት ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ የጎሳው ሰዎች ተጠምቀው «የጌታን መንገድ» ሲከተሉ ለማየት በመብቃቱ ተደስቷል። በቀጣይ አምስት ዓመታት ውስጥ ከጎሳው አባላት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው ሰጡ። በመንደራቸው 150 «የጸሎት ቤቶች» ተመሠረቱ። እግዚአብሔር በአሪ ሕዝብ መካከል ስለ ቀጠለው ታላቅ ተግባር ስሙ ይክበር።

ይህ ከሆነ ከ30 ዓመታት ያህል በኋላ ከወንጌላዊ ማሄ ጋር በኦሞ ወንዝ ሸለቆ አካባቢ ስንዝ ነበር። አንድ ቀን በጣም መሽቶብን በአንዲት አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ለማደር ስንል ወደዚያው አመራን። መምጣታችንን ያወቀ ሰው አልነበረም። አሥሩ ዋና ዋና የአሪ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚያ ስፍራ ለጸሎትና በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ወስጥ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት ሲሞክሩ በመድረሳችን ተገረምን። በዚህ ጊዜ ከወደ ጥግ ካለው ጨለማ አዛውንቱ ኦኒሳ ሲመጣ አየነው። በትልቅ ፈገግታ እጆቹን ዘርግቶ ተጠመጠመብኝ። ከእነዚያ ሁሉ ዓመታት በኋላ ዳግም መገናኘታችን እጅግ ደስ የሚል ነገር ነበር። ኦኒሳ፣ «አንተን ኢየሱስ ነህ ብዬ አስቤ ነበር፣» አለኝ። እኔም እየሳቅሁ፣ «አንተ ደግሞ የሰይጣን ባሪያና ጠንቋዩ መስለኸኝ ነበር፣» አልኩት። አብረን ተሳሳቅን። ጌታ በቡልቂ ከተገናኘንበት ጊዜ አንሥቶ ስለ ሆነልን መልካምነቱ፣ ስለ በዛልን ጥበቃውና በሕይወታችን ላይ ስለ ተዘረጋው መልካም እጁ ሳቃችንን፣ ልቅሶአችንንና ምስጋናችንን አዋህደን ለእግዚአብሔር በጋራ አቀረብን።

ይህ ሁሉ የሆነው ለምንድን ነው? ድንገት ኦኒሳና ገብሬ በገበያ ቦታ ወሬ ስለ ሰሙ አልነበረም። ይህ የሆነው በሚከተለው ምክንያት ይመስለኛል። ባለቤቴና እና እኔ ወደ አገራችን ተመልሰን ባለንበት እኔ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ንግግር በማድረግ

ላይ ነበርሁኝ:: ንግግር በማደርግበት ጊዜ የአገራችን ሰዎች በወቅቱ ወንጌል ሰምተው ለማያውቁ፣ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የወንጌል መልእክተኛ አይተው ለማያውቁ ሰዎች እንዲጸልዩ እጠይቅ ነበር::

አንድ ምሽት፣ በደቡብ ኒው ሳውዝ ዌልስ ውስጥ በምትገኝ የሪ ቨሪና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ሁለት ሴት ልጆች ከስብሰባው በኋላ ወደ እኔ መጥተው የጸሎት ካርድ እንድሰጣቸው ጠየቁኝ:: በየቀኑ ሊጸልዩልን የሚፈልጉ መሆናቸውንም ነገሩኝ! ካርዱን ከተመለከቱ በኋላ፣ እርስ በርሳቸው ተያዩ:: ከዚያም ካርዱን መልሰው ሰጡኝ:: ከዚያም በምንሠራበት አካባቢ ካሉት ወንጌል ያልደርሳቸው ጎሳዎች የአምስቱን ስም እንድጽፍላቸው ጠየቁኝ:: ስለዚህ ባስኬቶ፣ ገሊላ፣ ዶኮ፣ ማሎና ሲዶ ጎሳዎችን ጻፍኩ:: ልጆቹ በአንድ አልጋ ላይ አብ ረው የሚተኙ የ11 እና 12 ዓመት እኅትማማቾች ነበሩ:: በየምሽቱ ለእኔና ለባለቤቴ፣ እንዲሁም ለልጆቻችን ስማቸውን እየጠሩ ይጸልዩ ነበር:: ከዚያም የካርዱን ጀርባ እያዩ እግዚአብሔር ወደ እነዚህ ጎሳ ዎች የወንጌል መልእክተኞች እንዲልክ ይጸልዩ ነበር::

በቀጣዩ የአገር ቤት ጉዞአችን ወደዚያች ትንሽ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ በሚሲዮናውያን ስብሰባ ላይ ተገኘሁ:: ለተሰብሳቢዎቹ የማቀርበውን መልእክት ለማዘጋጀት ፕሮጀክተሩን እና ስላይዶችን በማስተካክልበት ጊዜ፣ በሩ ተከፈተና ሁለቱ ልጃገረዶች ገቡ:: አሁን ወደ ወጣትነት እድሜ ደርሰዋል:: በጎሳዎች አካባቢ ምን አዲስ ነገር እንደ ተፈጠረ ሊጠይቁኝ ገና ሲጠጉ «የጸሎት ካርድ ከእኔ ወስዳችሁ ነበር:: ምን አደረጋችሁት?» ብዬ በመናገር አስደነገጥኳቸው:: ለዓመታት ይዘው ሲጸልዩበት የነበረውን ያረጀ ካርድ አሳዩኝ:: ጌታ ከእነዚህ ጎሳዎች በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩትን ወደ ራሱ እንደ ጠራ በነገርኳቸው ጊዜ ምን ያህል እንደ ተደሰቱ መግለጽ አስቸጋሪ ነው:: እኔና ወንጌላውያኑ ወንጌልን ለገሊላ፣ ባስኬቶ፣ ደኮና ማሎ እንዴት እንዳደረስንና አሁን በዚያ አብያተ ክርስቲያናት ስለ መመሥረታቸው ነገርኳቸው:: አምስተኛው ጎሳ ሲዶ «ከጌታ ዘንድ ወሬ ሰምተው» የመጡ ኦኒሳና ገብሬ የተገኙበት መሆኑንም ነገርኳቸው:: ይህ ሁሉ የሆነው ሁለቱ ትናንሽ ልጆች በታማኝነት ስለ ጸለዩ ነበር:: «ጌታ ላደረገው ታላቅ ነገር ምስጋና ይድረሰው::»



8

# ተካ

## መላእክትን ሳያውቁ

*«እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤ አንዳንዶች ይህን ሲያደርጉ፣ ሳያውቁ መላእክትን አስተናግደዋልና::»*

ዕብራውያን 13:2

ቡም! በገበያ ሜዳ በተሰበሰቡት ሰዎች ላይ የተተኮሰው ጥይት በአናታችን ሽው ብሎ አለፈ:: የሆነ ብረት አገኘና በሕንጻው ላይ ነጥሮ ወደ አየሩ ተመለሰ:: ሁለት ጊዜ ደጋግሞ ያጓራው ጥይት ሁሉንም ሰው በድንጋጤ አራደው:: በገበያ ቦታው ውስጥ የነበረው የሰዎች ጫጫታ በአንድ ጊዜ ጸጥ አለ::

ይህ «ከእነዚያ ቀናት አንዱ ነበር! የተካን ምክር ሰምተን በ ረዥሙ መንገድ ዞረን መሄድ ነበረብን:: ተካ፣ ናና እና አሊ ከተ ባሉት ወንጌላውያን ጋር ከጊዩ ቦዲ ወደ ቡልቂ እያዘገምሁ ነበር:: አንድ ማታ የአካባቢውን አማኞች ለማበረታታት ስንል በዲማ ጌሮ ጸሎት ቤት አደርን:: ተካ፣ ናና እና እኔ በተቻለ ፍጥነት ሞቃቱን ሸለቆ ለማለፍ ስለ ፈለግን፣ ጠዋት ተነሥተን ሄድን:: አሊ በጌሮ አህያ ያለው ነጋዴ ጓደኛውን አገኘ:: ጓደኛው ወደ ቡልቂ ገበያ ወስዶ የሚሸጠውን ጨው፣ ዘይትና ሳሙና ለመግዛት ወደ ገበያ ሄዶ ነበር:: አሊ ሻንጣችንንና ልብሳችንን አህያ ላይ ከጫነ በኋላ፣ ከጓደኛው ጋር «ቡና ጠጥተው» እንደሚደርሱብን ነገረን::

ቅልጥማሙ ተካ ፊት ፊት ቀደመ:: እኔ ልደርስበት እየታገልኩ እርሱ ያለ ብዙ ችግር ረዣዥሙን ሰንበሌጥ እየጣሰ ቁልቁል ወደ ሸንተረሩ ይወርድና ከዚያም ያለፋታ ወደ ማዶ ይሻገራል:: እኔ

ላቤን እያንጠፈጠፍኩና ትንፍስ ትንፍስ እያልኩ ስደርስ ተካ ከዛፍ ጥላ ሥር አርፎ እንደገና ለመጓዝ ተዘጋጅቷል:: ለመውደቅ እየተንገዳገድሁ ናና እስኪደርስብን እንጠብቅ አልኩት:: ከሃያ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ናና ደረሰ:: በዚህ ጊዜ እኔም እንደገና ለመጓዝ ዝግጁ ነበርኩ:: ናና በቀስታ መጓዙን ነበር የሚያምነው:: ቀኑን ሙሉ ቀስ እያለ ያለማቋረጥ ይጓዛል:: የሚቆመው የሆነ ነገር ለመጠጣት ብቻ ነበር:: እኛ ለምን እንደምንቸኩል የገባው አይመስለኝም!

በባስኬቶ ተራራ ሥር አረፍ ብለን ከወንዙ ለመታጠብ፣ በኪሳችን የያዝነውን ቆሎ ለመብላትና ኮዳችን ውስጥ ውኃ ለመሙላት ፈለግን:: ከዚያ በኋላ ሽቅብ ወደ ተራሮቹ የሚወጣውን መንገድ ባልወደውም ሌላ አማራጭ መንገድ አልነበረም:: አብረን ከጸለይንና በተራራው ጫፍ ላይ እንደገና ለመገናኘት ከተስማማን በኋላ ጉዞ ጀመርን:: ልክ እንደ ገመትኩት፣ ተካ ወደፊት ሲርቅ፣ ናና ደግሞ ወደ ኋላ ይርቅ ጀመር:: ተራራውን በምወጣበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ባርፍም ናና ብቅም አላለም:: በመጨረሻም፣ በጣም ደክሜ ከጫፉ ላይ ወጣሁና እግሮቼ እየተንቀጠቀጡ የምቀመጥበትን ድንጋይ ፈለግኩ! ከእኔ ቀረብ ባለ ስፍራ ተካ ለአንድ የአካባቢው ገበሬ በርጋታ ስለ ክርስቶስ እየመሰከረ ነበር::

ከአንድ ሰዓት በኋላ አቶ «ዘገየ» ደረሰ! በዝግታ የሚጓዘው ናና ሳይቀር እረፍት አስፈልጎት ነበር:: ተካ ግን ተራራውን ጨምረን ወደ ሽቅብ በመውጣት በገሊላ በኩል ወደ ቡልቂ እንድንሄድ አሳብ አቀረበ:: የባስኬቶ አውራጃ ርእሰ-ከተማ በሆነችው በላስካ በኩል እንድንሄድ አልፈለገም ነበር:: ላስካ ልንደርስ የተቃረብን ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ መንገዱ ቁልቁል ወደ ኢሪጊኒ ወንዝ የሚወስድ ነበር:: ከወንዙ ወደ ቡልቂ የሚወስደው መንገድ ከዲማና ባስኬቶ የሚመጡ እንዲሁም ወደ እነዚሁ ስፍራዎች የሚሄዱ መንገደኞችና የተጫኑ በቅሎዎችን እየነዱ የሚጓዙ ነጋዴዎችም የሚጠቀሙበት የታወቀ መንገድ ነበር::

እኔና ናና ተቃወምን:: «ለምን?» ስንል ጠየቅን:: በገሊላ በኩል የሚወስደው መንገድ ሩቅ፣ ዳገትና ቁልቁለት የበዛበት፣ ጭቃማና



የሚያዳልጥ ነበር:: ቀላሉን መንገድ ነበር የፈለግነው:: ተካ ግን «ላስካ ሁልጊዜም ችግር አያጣውም:: በዛ ባለፍኩ ቁጥር ሁልጊዜም ችግር ይገጥመኛል - ሁልጊዜም! ገበሬው እንደ ነገረኝ የደርግ ካድሬምች እዛ አሉ:: ስለዚህ በዛ በኩል ማለፍ የለብንም:: ገሊላ ወዳጆች ስላሉኝ እነርሱ ጋ ልናርፍ እንችላለን:: በዚያ በኩል ብንሄድ ነው የሚሻለው» አለ:: በአገጩ ወደ ገሊላ ተራሮች አመለከተን:: እኔ አመነታሁ:: እኔም ብሆን ከካድሬዎች ጋር የመገናኘት ፍላጎት አልነበረኝም::

ደርግ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴንና ሚኒስትሮቻቸውን በመግደል ሥልጣን የተቆናጠጠ ኮሚኒስታዊ ጭፍራ ነበር:: ደርግ አገሪቱን ከጸረ-አብዮተኞች ለማጽዳትና ለመላው ሕዝብ የማርክሲዝም-ሌኒኒዝምን ጽንሰ-አሳብ ለማስተማር በሚል ፈሊጥ ካድሬዎችን ሃያ ሃያ በሚሆኑ ቡድኖች አሰማርቶ ነበር:: ይህ ከቻይና የባህል አብዮት ጋር የሚመሳሰል ነገር ነበር:: የዩኒቨርስቲና የኮሌጅ ተማሪዎች የለውጥ፣ የመሬት የዞታ መሻሻል እንደሚደረግ፣ ጉቦ፣ ሙስናና ብዝበዛ እንደሚወገዱ፣ ቃል ተገብቶላቸው ርእዮተ-ዓለሙን ለማስፋፋት ይሯሯጡ ነበር:: የሩሲያ፣ የቻይና፣ የምሥራቅ ጀርመንና የኩባ ሥልጠና ያገኙ ታላላቅ ኮሚኒስቶች የተለያዩ ቡድኖችን ይቆጣጠሩ ነበር:: በሺዎች የሚቆጠሩ «አማካሪዎች» ከእነዚሁ አገሮች «ነጻ አውጪዎችን»፣ ጦር ሠራዊቱን ለመርዳት ወደ ኢትዮጵያ ይጎርፉ ነበር:: ጦር ሠራዊቱ አዲሱን የ«ሶሻሊዝም» ቃላት እንዲማሩ በተገደዱት ሕዝብ ላይ ጫናዎችን ማብዛት ጀመረ:: ካድሬዎቹ ብጥብጥ በማስነሣት ሀብታም የመሬት ከበርቴዎችንና ነጋዴዎችን ይገድሉና ንብረቶቻቸውን ይዘርፉ ነበር:: ሱቆች ከተዘረፉ በኋላ ይደመሰሱ ነበር:: የገበያ ቦታዎች ደግሞ ሀብታሞች፣ የተማሩና ካድሬዎቹን የሚቃወም ማንኛውም ሰው የሚደበደብባቸው፣ የሚታሰርባቸው ወይም የሚገደልባቸው «የግፍ ስፍራዎች» ነበሩ:: በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አብዮቱን በመቃወማቸው ምክንያት ለመገደል ወይም ለመሰደድ ተገደዱ:: ሥለዓመታት ሽብር በመንገሡ የኢትዮጵያውያን ሕይወት ተናጋ::

ምዕራባውያን ሚሲዮናውያን፣ የኮሌጅ አስተማሪዎች፣ ዶክተሮችና ነርሶች «የምዕራቡ ዓለም በዝባዦችና አታላዮች» ናቸው ተ

«ተኩስ...»

«ቡም» ጥይቱ በአናታችንና በሕዝቡ ላይ አልፎ ሄደ:: ከኋላችን ባለው ሕንጻ ላይ የነበረውን ብረት መትቶ ተመለሰና በአየሩ ላይ አልፎ ሄደ:: ያልታሰበው ጩኸት ሁላችንም በድንጋጤ እንደ ሀውልት ደርቀን እንድንቀር አደረገን!:

አንድ የፖሊስ መኮንን ወደ አሥር ከሚሆኑ ወታደሮች ጋር መጣ:: ሠላሳ ዓመት ያህል የሚሆነው ወጣት ኮሎኔል ነበር የተኮሰው:: ወታደሮቹ ጠመንጃዎችን ሁሉ እንዲሰበስቡና ሕዝቡን እንዲበትኑ ትእዛዝ ሰጣቸው:: ከካድሬዎቹ መሪ እጅ ሽጉጡን ቀምቶ ከተከታዮቹ ለአንዱ ሰጠው:: ጠመንጃዎቹ ሁሉ ተሰብስበው ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንዲወሰዱ ትእዛዝ ሰጠ:: ገበያተኞቹ እንዲበተኑ ካዘዘ በኋላ፣ በንዴት ካድሬዎቹ ነገ ጠዋት ሪፖርት እንዲያደርጉለት አዘዘ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ሰው ተበተነ:: የቀረነው ተካ፣ ናና፣ እኔ፣ ኮሎኔሉና ወታደሮቹ ብቻ ነበርን::

ኮሎኔሉ ወደ እኛ ተመለከተና፣ «ተከተሉኝ» የሚል ምልክት አሳየ:: እርሱ ፊት ፊት ሲሄድ፣ እኛ ተከተልነው:: ከኋላችን አራት ወታደሮች ያጣድፉናል:: ወደ ፖሊስ ጣቢያ የምንሄድ መስሎን ነበር:: «ከድጡ ወደ ማጡ!» ስል አሰብኩ:: የተካ ፊት አሁንም የቅድሙን መልእክት ያስነብባል:: ኮሎኔሉ በድንገት ወደ ቀኝ በቀጭን መንገድ ታጠፈ:: ከዚያም ወደ ግራ:: ከዚያም በሁለት የቆርቆሮ አጥሮች መካከል ባለው ቀጭን መንገድ አለፈ:: ከመግቢያው ላይ ጠባቂ ወታደር ቆሟል:: ሌላ ወታደር ደግሞ ራቅ ብሎ ከብረት በሩ አጠገብ ቆሟል:: ስንደርስ በሩን ከፈተልን:: በግቢው ውስጥ ሌላም ፖሊስ ነበር:: ነገር ግን ቦታው እስር ቤት አልነበረም:: ይህ ቆንጆ የሆነ የኮሎኔሉ መኖሪያ ቤት ነበር:: ለቤት ሠራተኞችና ወታደሮች ትእዛዝ እየሰጠ እንድንገባ ሲነግረን ግራ ተጋብተን ከግድግዳው ጋ ቆምን::

ወደ ክፍሉ ስንገባ በሩ ተዘጋ:: እርሱም ቆሞ ይመለከተን ጀመር:: ከዚያም ወደ እኔ መጣ:: ፈገግ አለና ዝቅ ባለ ድምጽ፣ «የዮሐንስ አባት:: የዮሐንስ አባት ነዎት?» አለኝ:: እኔም በደረቀ



ጉሮሮ፣ «አዎ፣ የዮሐንስ አባት ነኝ:: ግን» አልኩት:: እርሱም እቀ ረጠና እንድንቀመጥ ነገረን:: ተቀመጥን:: ወደ ተካና ናና እየተ መለከተ፣ «ስለ እናንተም ቢሆን አውቃለሁ:: የቦዲን ጎሳዎች እያስተማራችሁ መሆኑን አውቃለሁ:: ያ ደግሞ ጥሩ ነገር ነው» አለ:: ወደ እኔ በመዞር፣ «የዮሐንስ አባት፣ አያውቁኝም አይደለም? ስሜ ተፈራ ይባላል:: ከብዙ ዓመት በፊት በሚንደራ የሚሲዮን ክሊኒክና ትምህርት ቤት በሚገነቡበት ጊዜ እኔ በቡልቂ ተማሪ ነበርኩ:: ከሰዓት ከሰዓት ወደ ግቢያችሁ መጥተን ከዮሐንስ ጋር እንጫወት ነበር:: የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ይነግሩን ነበር» አለ:: በርግጥ ልጆች ከዮሐንስ ጋር ኳስ ለመጫወት ይመጡ እንደ ነበ ረ አስታውሳለሁ:: እኔም ለልጆቹ ስለ ኢየሱስ እነግራቸው ነበር:: በዚያን ጊዜ ልጄ ዮሐንስ የሦስት ወይም አራት ዓመት ልጅ ነበር:: ለኮሎኔሉ አሁን ዮሐንስ የዩኒቨርስቲ ተማሪ መሆኑን ስነግረው፣ «ጥሩ ነው:: በጣም ጥሩ:: እግዚአብሔር ይመስገን» አለ::

ኮሎኔሉ እጆቹን ሲያጨበጭብ፣ በሩ ተከፈተና አገልጋዮች እጆቻችንን ለማስታጠብ ውኃና ፎጣ ይዘው ገቡ:: ቅመማ ቅመም የበዛበት ጣፋጭ ምግብና ብርዝ ቀረበልን:: በመጨረሻም፣ ቡና ተ ፈላልን:: ናና ለምግቡ እንዲጸልይ ተጠየቀ:: ኮሎኔል ተፈራም ከትንሽዋ ጠረጴዛ ዙሪያ ከእኛ ጋር አብሮ ተመገበ:: ምግቡን በልተን ስንጨርስ፣ እንደገና እጆቻችንን አስታጠቡን:: ብቻችንን ስንሆን ኮ ሎኔል ተፈራ፣ «ውጭ አሁን ጨለማ ነው:: ነገር ግን አሁኑኑ ብትሄዱ ነው የሚሻለው:: እስከ ከተማው ጫፍ ድረስ እንዲያደርሳችሁ ወታደር እሰጣችኋለሁ:: በተቻለ መጠን ራቅ ብላችሁ ሄዱ:: ካድሬዎቹ ባለጌዎች ናቸው:: አገራችንን እያጠፏት ነው:: ሌላ ጊዜ በዚህ መንገድ አትምጡ:: ካድሬዎቹ አዲስ አበባ ሄደው ጸረ-አብዮተኛ ነው ብለው ከሰውኛል:: የደርግ ባለሥልጣናት በቅርቡ ይጠሩኛል ብዬ እጠብቃሁ:: ምናልባትም ወደ ሰሜኑ ጦር ግንባር ይልኩኝ ይሆናል:: ለእኔ ጸልዩልኝ:: በሰላም ሂዱ:: ተ ጠንቀቁ» አለን::

አብረን ከጸለይን በኋላ ስላደረገልን ርዳታ በጣም አመስግነን ተ ጨባብጠን ተለያየን:: በጸጥታ ወጥተን ወታደሩን እየተከተልን

ከከተማይቱ ወጣን:: ወታደሩን ተሰናብተን መንገዳችንን ስንቀጥል፣ ጨረቃ ወጣች:: ተካ ፊት ፊት ሲቀድም፣ ናናም ኋላ ሳይቀር አብሮን ተጓዘ:: በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ኢሪጊኒ ወንዝ ደረስን:: እዛ ታጥበን አረፍ አልን:: ጌታ ስላዳነን አብረን አመሰገንነው::

በጨረቃ ብርሃን እየተረዳን፣ ወደ ቡልቂ ስንጓዝ፣ ተካ የመጨረሻውን ማስጠንቀቂያ ሰጠን፣ «እንዳልኩት፣ ላስካ ሁልጊዜም ችግር አያጣም - ሁልጊዜም!» አለን::



# 9

# ዋጃ

## የጌታ እስረኛ

*«እንግዲህ በጌታችን ምስክርነት ወይም በእስረኛው በእኔ አትፈር:: ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ኃይል መጠን በወንጌል አብረኸኝ መከራን ተቀበል::»*

2ኛ ጢሞቴዎስ 1:8

ዋጃ በሳውላ የፍርድ ችሎት ፊት ቆሞ እጁን ከፍ አደርጎ አነሣ:: እጅና እግሮቹን በካቴናና በሰንሰለት ጥፍር ተደርጎ ታስሯል:: «እግዚአብሔር ይመስገን፣» ሲል ጮክ ብሎ መናገር ጀመረ:: «ለኢየሱስ ጌጥ ሆኜአለሁ:: ይህ ለእኔ የጀግና ሜዳሊያ እንደ ማግኘት ነው:: ለኢየሱስ ጌጥ አግኝቻለሁ!»

ዋጃ ወደ ከሳሾቹ ዘወር ብሎ በድፍረት ንግግሩን ቀጠለ:: «ይህን ሰንሰለት በመሸከሜ የማፍር መስሎአችሁ ነበር:: ነገሩ እንዲህ አይደለም:: ዛሬ እዚህ የተገኘሁት የክርስቶስ ተከታይ በመሆኔ ምክንያት ነው:: ለጌታዬ ይህንን ሰንሰለት ማጥለቄን እንደ መታደል እቆጥረዋለሁ:: እንዲህ ስላስጌጣችሁኝ አመሰግናችኋለሁ::»

ጊዜው በኢትዮጵያ «ቀይ ሽብር» የተጧጧፈበት ወቅት ነበር:: የኮሚኒስት ካድሬዎች የደርግ ተቃዋሚዎችን ሁሉ በማውደምና ለሕዝቡ የማርክሲስት/ሌኒኒስት አስተምህሮ በመጋት አገሪቱን የሚያሸብሩበት ጊዜ ነበር:: በዚህ ወቅት አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተዋል:: መጽሐፍ ቅዱሶች ተወግደዋል:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ታስረዋል ወይም ተገድለዋል:: ነጋዴዎችና ሀብታሞች ንብረታቸውንና መሬታቸውን ተነጠቁ:: ንብረቴን አልሰጥም

ያሉት ተገደሉ። በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ጎረቤት አገሮች ተሰደዱ። በአሁኑ ሰዓት ከሁለት ሚሊዮን የሚበልጡ ኢትዮጵያውያን በሌሎች አገሮች (በአብዛኛው በአሜሪካ፣ ካናዳና አውሮፓ) ውስጥ ይኖራሉ።

እነዚያ የቀይ ሽብር ዓመታት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ከፍተ ኛ ሥቃይን አስከትለዋል። እንዲሁም ደግሞ ጥቂት ሰዎች «ቡና ለመጠጣት» የሚሰባሰቡባቸው «የቤት ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት» እንዲመሠረቱ አድርገዋል። ሰዎች ቡና እየጠጡ አብ ረው ለመጸለይና እርስ በርስ ለመበረታታት፣ እንዲሁም ቡና ተ ጠርተው ለሚመጡት ሰዎች ለመመስከር ይችሉ ነበር። በዚህ ዓይነት በ17ቱ የደርግ ዘመን የአማኞች ቁጥር በእጥፍ አድጎ ነበር። ከዚያ በኋላም እንዲሁ ቁጥሩ በእጥፍ አድጎአል! አብዛኞቹ መጋቢ ዎች «ሁለት ሥራ» ያላቸው ነበሩ። ባለቻቸው ትንሽ መሬት ላይ የእርሻ ተግባራትን በማከናወን ቤተሰቦቻቸውን የሚመግቡና በዚያ አስከፊ የደርግ የመከራ ጊዜያት አማኞችን የሚያበረታቱ ነበሩ። ወንጌላውያን አማኞች ንብረታቸውን ሁሉ ቢያጡም፣ በእርሻ ወይም በንግድ አማካኝነት ራሳቸውን ለመደገፍ ይጥሩ ነበር።

እንደ ሌሎቹ ሁሉ ዋጃም «ሁለት ሥራ» ያለው ወንጌላዊ ነበር። በኤስ አይ ኤም የሶዶ ሆስፒታል ከሠለጠኑት ድሬሰሮች (የሕክምና ባለሙያዎች) አንዱ በመሆኑ፣ በሳውላ የራሱን ፋርማሲ ለመክፈት ችሎ ነበር። ችሎታና ልምድ ያለው ሰው በመሆኑ፣ መልካም ስም አትራፊ ንግድ ለማካሄድና ለማትረፍ ችሎ ነበር። ጥበቡና ታማኝነቱ በከተማይቱ ውስጥ ሰፊ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሲያደርግ፣ ክርስቲያናዊ ምስክርነቱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሆን አስቻለው። በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ የሚያቀርባቸው ታላላቅ ስብከቶቹ ብዙዎች ለክርስቶስ ራሳቸውን እንዲሰጡ አደረጉ። በተጨማሪም ዋጃ ወደ ሩቅ ቦታ ዎች የሚሄዱትን ወንጌላውያን ይደግፍ ነበር። ደርግ በመጣ ጊዜ ግን እንደ ሌሎች ስኬታማ ነጋዴዎች ሁሉ ዋጃ ጸረ-አብዮተኛ ነው ተብሎ ተጠረጠረ። ለደርግ ባለሥልጣናት ዋጃ፣ «ሀብታም»፣ ተወዳጅና ክርስቲያን ስለሆነ አደገኛና መወገድ ያለበት



ሰው ነበር።

ወደ እስር ቤቱ በፊት በር ለመግባት ባለመቻሌ፣ ዋጃን ለማግኘ ት ሌላ ዘዴ ሞከርኩ። የጎፋን አካባቢ ከመልቀቄ በፊት ወዳጄን ለመጎብኘት ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ጠባቂዎቹ ወደ ሳውላ እስር ቤ ት እንድገባ አልፈቀዱልኝም። በአቅራቢያው ባለው ኮረብታ ላይ በመውጣት ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ እስረኞች በእስር ቤቱ ግቢ ውስጥ ፀሐይ ሲሞቁ ለመመልከት ቻልኩ። ይህም ሆኖ ዋጃን ለማየት አልቻልኩም።

ኮረብታው ላይ ከአንድ ሰዓት በላይ ጠበቅሁ። ልሄድ በምዘጋጅበት ሰዓት ላይ ሌሎች እስረኞች ከክፍላቸው ወደ ሜዳው ወጡ። እነዚህ ነፍሰ-ገዳዮችና የአብዮቱ ተቃዋሚዎች በመሆናቸው፣ አደገኛ ወንጀለኞች ናቸው ተብለው የተለዩ ነበሩ። እጆቻቸውንና ቁርጭምጭሚታቸውን በሰንሰለት የታሰሩ ሲሆን፣ በታጠቁ ወታደሮች ይጠበቁ ነበር። አንዱ ከሌላው እስረኛ ጸጉርና ልብስ ላይ ቅማል ይለቅማል።

ዋጃን ከነፍሰ-ገዳዮች መካከል አየሁት። ሌሎች የማውቃቸው ክርስቲያኖችም በሰንሰለት ታስረው አየሁ። ሁሉም የታሰሩት ከዋጃ ጋር ሲጸልዩ በመገኘታቸው «ጸረ-አብዮተኞች» ተብለው ነበር። ይህ ክስ ደግሞ የረዥም ዓመታት ወይም የሞት ቅጣት የሚያስበይን ነበር።

ዋጃ ወደ ኮረብታው ቀና ብሎ ተመለከተኝ። በሰልፉ ላይ ላሉት እስረኞች ይህንኑ መረጃ በመስጠቱ ክርስቲያኖች ሁሉ ቀና ብለው አዩኝ። ዋጃ በሰንሰለት የታሰረ እጁን ወደ ላይ ከፍ አደረገ። ወደ ላይ በማመልከት ፊቱን ወደ ሰማይ አነሣ። መልእክቱ ስለ ገባኝ፣ እኔም ፊቴን ወደ ሰማይ በማንሣት በእጄ ወደ ሰማይ ጠቆምኩ። «ከእንግዲህ እዚህ ምድር ላይ ላይህ የምችል አይመስለኝም ዋጃ። ነገር ግን በሰማይ በአዳኙ እግር ሥር አገኝሃለሁ» ነበር ያልኩት።

ዋጃ ለእምነቱ ከሞት ጋር የተጋፈጠው አሁን ብቻ አልነበረም። የአርባ ምንጭ አስተዳዳሪ የነበረው አሊ. ሙሳ ብዙ ክርስቲያኖችን ለእስርና ለሞት የዳረገ ጨካኝ ሰው ነበር። አሊ ሙሳ ሌሎች

የሕዝባዊ ማኅበራት መሪዎችንም በመግደል ንብረታቸውን ለመቆጣጠር የቻለ በሁሉ የተፈራ ሰው ነበር። አሊ ሙሳ «ከስታሊን የከፋ ጨካኝ፣ ከሌኒን የባሰ ኮሚኒስት፣ ከማርክስ የበለጠ አደገኛ» የሚል ስያሜ የተሰጠው ሰው ነበር።

አሊ ሙሳ ሳውላ የሚገኘው ዋጃ የኢየሱስ ተከታዮች ዋንኛው መሪ መሆኑን ሰማ። በመሆኑም፣ ከአርባ ምንጭ እርሱን የሚገድሉትን ወታደሮች ላከ። ወታደሮቹ ወደ ሳውላ በሚሄዱበት ጊዜ፣ ያልታሰበ ኃይለኛ ዝናብ ዘንቦ መንገዱን ማጥ ስላደረገው መኪናቸው በተደጋጋሚ ተይዞ አዘገያቸው። ዘንቴ ወንዝ ላይ ሲደርሱ ወንዙ ሞልቶ አላሻግር አላቸው። ሳያቋርጥ በሚጥል ዝናብ ውስጥ ሆነው ለሦስት ቀናት ከቆዩ በኋላ፣ የያዙት ስንቅ በማለቁ፣ የአሊ ሙሳን ቁጣ ለመጋፈጥ ወስነው ወደ አርባ ምንጭ ተመለሱ።

ለዋጃ በሰንሰለት ታስሮ ለአራት ቀናት ተጉዞ ወደ ክፍለ ሀገሩ ዋና እስር ቤት መሄዱ ከባድ ነገር ነበር። ነገር ግን ክርስቲያን ወንድሞቹን በማጽናናት በመንገድ ላይ ለወንጀለኞች፣ ለፖለቲካ እስ ረኞችና ለጠባቂ ወታደሮች ይመሰክር ነበር። ይህ ሁሉ ፍትሕ-አልበኝነት ለመቀበል የሚከብድ ነበር። ዋጃ ስለ ሚስቱ ኤልሣቤጥና ስለ ቤተሰቡ አሰበ። እንዴት ይኖሩ ይሆን? ምግብ ከየት ያገኙ ይሆን? በቤታቸው የተወሰኑ ሲሆኑ፣ ወደ ገበያ ለመሄድ አይችሉም ነበር። የማርክሲስት ካድሬዎች ቤቱንና ፋርማሲውን ወርረው ገንዘቡን፣ መድኃኒቶቹንና ወረቀቶቹን ሁሉ ወስደውበታል። ዋጃ መድኃኒቶቹን ለመንግሥት ክሊኒክ አስረክቦ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ እንዲያደርግ እንኳን አልተፈቀደለትም። ተጥለው የአገልግሎት እድሜያቸው እንዲያልፍ በመደረጉ ከንቱ ሆነው ቀሩ። የተፈጸመው ክፋት ለማመን የሚያዳግት ነበር።

እኔም ስለ ዋጃ ሚስትና ቤተሰብ ማሰብ ጀመርኩ። ጥቂት የአካባቢው ክርስቲያኖች እንክብካቤ ያደርጉላቸው ነበር። ማንም ከቤተሰቡ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳያደርግ የተጣለውን ገደብ በማለፍ ማታ ማታ ምግብ ይሰጧቸው ነበር። እኔም ለምግብ መግዣ የሚሆን ትንሽ ገንዘብ ሰጠኋቸው። በእነዚያ ፈታኝ ጊዜያት



ጌታ በታማኝነት የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አሟላላቸው።

በአርባ ምንጭ እስር ቤት መጀመሪያ አካባቢ ዋጃ እንደ ሌሎቹ እስረኞች ጉድጓድ እንዲቆፍር፣ እንዲሁም ድንጋይና ለጣውላ የሚሆን ግንድ እንዲሸከም ይገደድ ነበር። ከዚያ በኋላ የሕክምና እውቀት የሌለው የክሊኒኩ ሠራተኛ ከዋጃ ጋር ተገናኘ። ዋጃ የሕክምና እውቀት እንዳለው ስለ ተረዳ፣ በሽታን በመመርመርና ሕክምና በመስጠት ዙሪያ ምክሩን ይጠይቅ ጀመር። «እዚህ ዶክተር የለንም። ነገር ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ በሽተኞች አሉ። ብዙም መድኃኒት የለንም። እኔ ደግሞ ብቻዬን ስለ ሆንኩ፣ ሁሉንም በሽተ ኛ ልከታተል አልችልም። አንተ ከእኔ የተሻለ እውቀት አለህ። ከተ ስማማህ ይህንን ሥራ የማከናወኑ ኃላፊነት ያንተ ይሆናል፣» አለው። ዋጃ በዚህም ውስጥ የጌታን እጅ አየ።

ዋጃ በፍጥነት ውጭ የነበረውን ያህል አክብሮት በእስር ቤቱ ውስጥ አገኘ። ከአንድ ወር በኋላ የክሊኒኩ ሠራተኛ ለሥልጠና በመላኩ ሌላ ሰው ሳይተካ ቀረ። የእስር ቤቱ አስተዳዳሪ ለዋጃ ኃላፊነቱን በመስጠት የክፍሉን ቁልፍ አስረከበው። በዚህ ስፍራ ዋጃ ለርዳታ ከሚመጡ ሰዎች ሁሉ ጋር በግል የመገናኘት ዕድል ነበረው። ወደ መድኃኒት ክፍሉም መግባት ይችል ነበር። በመድኃኒት ማከማቻው ውስጥ የተቀዳደዱ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሶችን አገኘ። እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሶች አሊ ሙሳ አብያተ ክርስቲያናትን ባዘጋ ጊዜ የዘረፋቸው ነበሩ። ገጾቹ ለሽንት ቤት እየተቀደዱ ያገለግሉ ነበር። ዋጃ አንድ ምንም ያልተነካ መጽሐፍ ቅዱስ በማግኘቱ ደስ ብሎት ይጠቀምበት ጀመር። ለዚህ ብርቅ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማማኝ የመደበቂያ ስፍራ አዘጋጀ።

አሁን ከሰዎች ጋር የሚገናኝበት ስፍራ፣ መጽሐፍ ቅዱስና ለሕሙማን መኀብኛ የሚያገለግል ኩራዝ አገኘ። ዋጃ ጥቂት አማኞችን ለጸሎት ሰበሰበ። እነዚህን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በማስተማር ወደ ክርስቶስ መለሳቸው። እነርሱም በበኩላቸው አብ ረዋቸው የሚተኙትን ሰዎች በማስተማር ወደ ክርስቶስ መመለስ ጀመሩ። ብዙም ሳይቆይ በሁሉም ሕንጻዎች ውጥ አማኞች ሊኖሩ በመቻላቸው፣ በየማታው የመዝሙር ድምጾች ይሰሙ ጀመር።

ወራቱ ቀስ በቀስ ሲያልፉ፣ ዋጃ ስለ ቤተሰቡ አዘወትሮ ማሰብ ጀመረ:: ኤልሣቤጥ ደህና ትሆን? ልጆቹስ? የሚበሉት ነገር ይኖራቸው ይሆን? ከመጸለይና እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው ከመለመን በቀር ሊያደርግ የሚችለው ነገር አልነበረም::

አንድ ቀን አዳዲስ እስረኞች ከሳውላ ተይዘው መጡ:: ዋጃ እጆቹና እግሮቹ የታሰሩበትንና ከመቆሳሰላቸውም የተነሣ ሕክምና የሚያስፈልጋቸውን አንድ እስረኛ እንዲረዳ ተጠየቀ:: ይህ ሰው ዋጃን በውሸት የከሰሰውና በሰንሰለት እንዲታሰር ያደረገው መሆኑን ሲመለከት ተገረመ:: አሁን ከማርክሲስቶች ጋር በመጣላቱ በድርብ ሰንሰለት ታስሮ መጣ:: ዋጃን ሲያይ ደነገጠ::

ዋጃ የግለሰቡ ሰንሰለቶች እንዲወልቁ ካደረገ በኋላ፣ ቁስሎቹን አጣጥቦ የሕክምና ርዳታ አደረገለት:: ለጥቂት ሳምንታት ዋጃ መልካም አገልግሎት ሲሰጠው ከቆየ በኋላ፣ ግለሰቡ ልቡ ተሰብሮ ይቅርታ ጠየቀው:: ዋጃም ለሥቃይ ያጋለጠውን ይህን ሰው ይቅር አለው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቀደም ሲል ለፈጸመበት በደል ማካካሻ እንዲሆንለት ዋጃ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ ጀመረ:: አብረው የእስረኞችን ሕይወት ለማሻሻል ጥረት አደረጉ:: መሐይማን እስረኞችን ማስተማር ጀመሩ:: ከዚያም የሽመናና የአትክልት ፕሮጀክቶች ተጀመሩ:: እነዚህ ሥራዎች ከባለሥልጣናት ጥሩ አስተያየቶችን አተረፉላቸው:: አንዳንድ እስረኞች የልብስ ስፌት ተማሩ:: ሌሎች ደግሞ የእንጨት ሥራዎችን ተማሩ:: የእስር ቤቱ ኃላፊዎች የበላይ ባለሥልጣናትን በማምጣት እነዚህን ሥራዎች አስጎበኙአቸው:: ዋጃ ለእስረኞችና ለጠባቂዎች ምስክርነት በመስጠቱና ክርስቲያኖችን በማበረታታቱ ሥራ ገፋበት:: ወራቱ እያዘገሙ መጓዛቸውን ቀጠሉ::

በመጨረሻም፣ ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ፣ የሚፈታበት ቀን ደረሰ:: ዋጃና አብረውት የታሰሩት ወገኖች ያሏቸውን ጥቂት ነገሮች በማሰባሰብ የቀሩትን እስረኞች ተሰናብተው ወጡ:: የእስር ቤቱ አስተዳዳሪ የሚፈቱትን ሰዎች ስም በሚጠራበት ጊዜ እስረኞቹ ሁሉ ተሰብስበው ነበር:: ከዋጃ ጋር ከጎፋ የታሰሩ የስምንት ክርስቲያኖች ስም ተጠራ:: ነገር ግን ዋጃ ወደ ጠሪዎቹ ፊት



ሲቀርብ፣ «ስምህ እዚህ ዝርዝር ውስጥ የለም:: መቆየት አለብህ» አሉት::

«ግን እኮ የተፈረደብኝን ጊዜ ጨርሻለሁ:: እዚህ ልታቆዩኝ አትችሉም፣» ሲል ተከራከረ::

ስምንቱ የጎፋ አማኞች፣ «የገባነው አብረን ስለሆነ የምንወጣውም አብረን ነው፣» በማለት አንወጣም አሉ::

ቀደም ሲል ዋጃን የከሰሰው ሰውዬ ይህ ኢ-ፍትሐዊነት ነው በማለት እስረኞቹ እንዲነሣሡ ቅስቀሳ አደረገ:: ቀስ በቀስ የተጀመረው ጉምጉምታ ወደ ጩኸት፣ ከዚያም «ዋጃ ይለቀቅ፣ ዋጃ ይለቀቅ» ወደሚል ሁካታ አመራ:: ቀጥሎ ከሺህ የሚበልጡ ድምፆች በአንድነት፣ «ዋጃ ይለቀቅ፣ ዋጃ ይለቀቅ፣» እያሉ መሬቱን በእግሮቻቸው ይደበድቡ ነበር:: እስረኞቹ ተቃውሞአቸውን በጨመሩ ልክ፣ ሁካታውም እያሸቀበ ሄደ:: በእስር ቤቱ ታሪክ እንዲህ ዓይነት ነገር ተደርጎ አያውቅም ነበር:: እስረኞቹ ሰንሰለቶቻቸውን ያቃጭሉ ወይም ስብርባሪ እንጨቶችን በማጋጨት እስር ቤቱን ቀውጢ አደረጉ!

እስረኞቹ፣ «ዋጃ ይለቀቅ፣» እያሉ እየጮሁ ግድግዳዎችን ሲደበድቡና መዝጊያዎችን ሲቀጠቅጡ፣ ብጥብጥ ይነሣል ብሎ የሰጋው የእስር ቤቱ አስተዳዳሪ ተጨማሪ ወታደሮች እንዲመጡ ጥሪ አደረገ:: መልእክተኞች ወደ አስተዳዳሪው አሲ ሙሳ ተላኩ:: እርሱም በአዲስ አበባ ያሉትን ባለሥልጣናት አነጋገረ:: በዚህ ጊዜ የአብዮቱ ማዕበል እየሞተ ስለ ነበር ብዙዎች የደርግ እድሜ እያጠረ ነው የሚል ግምት ነበራቸው:: ከኃላፊዎቹ ማናቸውም ውሳኔ ለመስጠት ወይም ኃላፊነት ለመውሰድ አልፈለጉም ነበር:: እስረኞቹ አድማ በማድረግ ሥራ አንሠራም አሉ::

ዋጃ ሰዎች ለእርሱ ባደረጉት ነገር ተገረመ:: ሕይወቱና ምስክርነቱ ብዙዎችን ወደ አዳኛችን መልሷል:: በእርሱ ላይ የተፈጸመው ፍትሕ-አልበኝነት ሁሉንም ሰው የዘገነነ ነበር:: ይህ የመጨረሻው ሰዓት ነበር! ዋጃም መለስ ብሎ፣ «እኔ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ስለሆንኩ በጊዜው እንዲያስፈታኝ እጠብቀዋለሁ፣» አለ::

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ፣ «ዋጃን ልቀቁት፣» የሚል ትእዛዝ መጣ:: እስረኞቹ በሙሉ በደስታ ፈነደቁ! ዋጃ እስር ቤቱን ለቅቆ ሲወጣ፣ እስረኞችና ጠባቂዎች ተሰልፈው አጨበጨቡለት:: መጀመሪያ ያሳሰረው ሰውዬ እያለቀሰ የዋጃን አነስተኛ እስር ዕቃ ተሸክሞ እስከ በር ሸኘው:: ዋጃ ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ እስር ቤቱን ለቅቆ ወጣ:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱን በእስር ቤቱ ውስጥ ጥሩ ቦታ እንደ ደበቀ ረስቶት ነበር የወጣው::

«አሁን ባለው የአገራችን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱሴ ያስፈልገኝ ነበር፣» አለ ዋጃ::

ዋጃ በተፈታ ሰሞን አግኝቼው፣ «በእስር ቤት ውስጥ በምትሠቃይበት ጊዜ፣ በብዛት የምታስበው የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነበር?» አልኩት:: ዋጃ ፈገግ አለና፣ «ኢየሱስ፣ 'በፍጹም አልተውህም አልጥልህምም' ብሏል:: ይህንን የተስፋ ቃል የሰጠው ኢየሱስ ትናንት፣ ዛሬ፣ እስከ ዘላለምም ያው ነው:: እርሱ ሁልጊዜም ታማኝ በመሆኑ ይጠብቀናል» አለ::

## ድኅረ ታሪክ

ዋጃ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ሶዶ ተመልሶ ሌላ ፋርማሲ ከፈተ:: ፋርማሲውም በጣም ስኬታማ ሆነለት:: የሕይወትና የወንጌል ምስክርነቱም ቀጠለ:: ጌታ ለወንጌል ምስክርነትና ለቤተ ክርስቲያን ተከላ እንዲህ ዓይነት ልብ ያለውን ሰው እንዳውቅ ስለ ረዳኝ አመሰግነዋለሁ:: ዋጃ የወላይታ አብያተ ክርስቲያናት መሪ ሆኖ በመመረጥ በታማኝነት ለብዙ ዓመታት አገልግሏል:: በመሪነት ዘመኑ ብዙ ወንጌላውያን ወንጌል ወዳልደረሰባቸው ቦታዎች ተልከዋል:: የእርሱ ታሪክ ቀጣይነት ያለው ነው::

አንድ ቀን የሕይወት ታሪኩ ተጽፎ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች፣ በአሳዛኝ ገጠመኞችና ኀዘኖች ውስጥ የሚገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ የቱን ያህል ብቁ መሆኑንና የእምነትንም አሸናፊነት እንደሚያሳይና ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚውል ተስፋ አደርጋለሁ::



# 10

# ደሳለኝ

## ለሕይወት ዘመን ልጅ ሆኖ መመረጥ

*«በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በሰማያዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ:: በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን::»*

ኤፌሶን 1:3-5

*«አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ::»*

ሮሜ 8:15

ትንሹ ልጅ እያለቀሰ ከአቧራማ መንገድ ላይ ተቀምጦአል:: ጥቂት ጎረቤቶቿ እናቱ የነበረችውን ወጣት ሴት ቀብረው መመለሳቸው ነበር:: ከቀብሩ በኋላ መሣሪያዎቻቸውንና ልብሶቻቸውን ሰብስበው እየተቻኮሉ ሄዱ:: ከዚያ ያለፈ ምንም ነገር የማድረግ ፍላጎት አልነበራቸውም:: ምክንያቱም የራሳቸው የሆኑ በቂ ችግሮች ነበሯቸው::

ወጣቷ ሴት ራሷ ልጅ ነበረች:: በትኩሳት በሽታ ነበር የሞተችው:: ምንም ዓይነት የሕክምና ድጋፍ ሳታገኝ ብቻዋን ታማ ሞተች:: በዚያ አካባቢ የምታልፍ ሴት አስከሬኗ ከበሩ ላይ ተኝቶ በመመልከትዋ ነበር ለጎረቤቶቿ የሞተ ሰው መኖሩን የተናገረችው:: ስለ ልጁ የተጨነቀ ሰው አልነበረም:: ማንም ሰው አልፈለገውም:: ሁሉም ተዉት:: ከእናቱ ጋር ይኖርበት የነበረው ደሳሳ ጎጆም ቢሆን ሊወድቅ ተቃርቦ ነበር::

ልጁና እናቱ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አልነበራቸውም:: ስለማይታወቀው አባት የሚነገር አንድ ታሪክ ነበር:: ልጁ የተረገዘው እናቱ ላይ በደረሰው አስገድዶ የመድፈር ተግባር ሳይሆን እንዳልቀረ ይነገራል:: እናቱ ለልጁ ስም ሳትሰጥ ነበር የሞተችው:: ስም የምትሰጥበት ምክንያት አልነበራትም:: ከዚያም ብቻዋን በድንገት ታማ ሞተች::

እንደ አብዛኞቹ ጎረቤቶቹ ሁሉ ታኬ የተወሰነ መሬት ያለው ታታሪ ገበሬ ነበር:: አንድ ወንጌላዊ ወደ አካባቢያቸው መጥቶ ስለ ክርስቶስ ወንጌል በሰበከ ጊዜ መጀመሪያ አምነው ከተቀበሉት ሰዎች አንዱ ታኬ ነበር:: ለእርሱ ከወንጌሉ አስገራሚ እውነታዎች አንዱ እግዚአብሔር ልጁ አድርጎ የመረጠው መሆኑ ነበር::

ወንጌላዊው እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ልጆቹ እንዳደረገን የሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አነበበ:: በተጨማሪም የእግዚአብሔርን የልጅነት መንፈስ በመቀበላችንና የቤተሰቡ አባል በመሆናችን ከእንግዲህ ነጻ ሰዎች እንጂ ባሪያዎች አለመሆናችንን የሚገልጽ ክፍል አነበበ:: እንዲሁም ልጆቹ ሊያደርገን በልጁ ደም እንደ ዋጀን አመለከተ:: «አባ አባት» ብለን የምንጮህበትን የልጁን መንፈስ እንደ ሰጠንም አብራራ:: ሁሉም ነገር እጅግ አስገራሚና አስደሳች ሆነለት:: እናም የታኬ ልብና አእምሮ ተማረከ:: ታኬ ደስ ብሎት ይህንን መልካም የምስራች ለሚስቱና ለጎረቤቶቹ አካፈለ:: አንዳንዶቹ በክርስቶስ በማመናቸው በመሬቱ ላይ የጸሎት ቤት ሠሩ::

የሌላን ሰው ልጅ የራስ ማድረግ (ማደጎ) ለወላይታ ሕዝብ እንግዳ አሳብ ነበር:: እነዚህ አረማውያን ሰይጣንን፣ ስጦታዎችንና መሥዋዕቶችን የሚጠይቁትን በርካታ ጠንቋዮችና ከሁሉም በላይ የአያት ቅድማያቶቻቸውን መንፈስ ይፈሩ ነበር:: የአያት ቅድማያቶቻቸው መናፍስት ከመንደሩ ርቀው እንዳልሄዱና ካልታዘዙአቸው መጥፎ ዕድል እንደሚያመጡባቸው ያምኑ ነበር:: አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ወንድሙ ሚስቱን እንዲያገባና ለወንድሙ ልጆችን እንዲወልድለት ይደረጋል:: ልጆቹ የሚጠሩት በሞተው ሰው ስም ይሆናል::



አንዳንድ ጊዜ አንድ ቤተሰብ ወላጆቹ የሞቱበትን የዘመድ ልጅ ወስደው ያሳድጋሉ:: ነገር ግን ያ ልጅ ሁልጊዜም የአባቱን ስም እንዲጠብቅ ይደረጋል:: የአባቱን ውርስ ይይዛል:: ብዙውን ጊዜ ለነገሩ የሚወረስ ነገር አይኖርም::

አንድ ቀን ታኬ በቅሎው ላይ ተቀምጦ ከሩቅ የገበያ ቦታ እየመጣ ነበር:: ከፊት ፊቱ ሁለት አህዮቹን እየነዳ ነበር:: በመንደሩ ውስጥ ሲያልፍ ድንገት ስለ ሞተችው ወጣት ሴት ሰዎች ሲነጋገሩ ሰማ:: ከዚያም ትንሽዬ ጥቁር ልጅ ከመንገድ ላይ ተመለከተ:: ልጁ ራቁቱን በቆሻሻ እንደ ተሸፈነ ርቦት ያለቅስ ነበር:: ሕጻኑ የአንድ ዓመት ልጅ ሲሆን፣ በጣም ቀጭን ነበር:: ማንም ሰው ለቅሶውን ሰምቶ ሊመጣለት አልፈለገም:: የተጨነቀለትም ሰው ያለ አይመስልም::

ታኬ ማንም ሰው ልጁን እንደማይፈልግ ተገነዘበ:: አንድ ሰውዬ፣ «በቅርቡ በረሃብ መሞቱ አይቀርም:: ወይም የጅብ እራት ይሆናል፣» አለና ትከሻውን እየሰበቀ ሄደ::

ታኬ ከበቅሎው ላይ ሆኖ ሕጻኑን ሲያይ ቆየ:: ሁለት ሴት ልጆችና ሦስት ወንድ ልጆች ስላሉት የራሱ ቤተሰብ አሰበ:: «ማንም የማይፈልገው ከሆነ እኔ እወስደዋለሁ፣» ሲል አሰበ:: ከበቅሎው ወርዶ ልጁን በነጠላው ጠቅልሎ ይዞት ወደ በቅሎው ወጣ:: ከዚያም ወደ ቤቱ ገሰገሰ:: የመንደሩ ሰዎች ታኬ ልጁን ይዞት በመሄዱ ደስ አላቸው:: ከእንግዲህ ልጁ ሲሞት ለመቅበር የሚጨነቁበት ምክንያት አይኖራቸውም::

ታኬ ሕፃን ልጅ ይዞ ከገበየ ሲመለስ በመመልከቷ ባለቤቱ ግራ ተጋባች:: ይሁን እንጂ፣ ልጁን ተቀብላ ጡት ማጥባት ጀመረች:: ከጠነበ በኋላ አጥባ ልብስ አለበሰችው:: አቅፋው ከእሳት ዳር በርጩማ አስጠግታ ቁጭ አለች:: ከዚያ በኋላ ነበር ከባሏ ማብራሪያ የጠየቀችው::

ተካ የልጁን አሳዛኝ ታሪክ ነገራት::

ሚስቱም፣ «እግዚአብሔር በት ;ክለኛው ሰዓት ከቦታው እንድትደርስ እንዳደረገህ አምናለሁ:: ልጃችን አድርገን

እናሳድገዋለን:: እንደ ሌሎች ልጆቻችን ጠየም ባይልም፣ ከእኛ እንደ አንዱ ይሆናል:: ደስታ እንደሚያመጣልን ጥርጥር የለውም:: ስለዚህ ደሳለኝ ብለን እንጥራው» አለች:: ለሌሎች ልጆችም ደሳለኝ አዲሱ ወንድማቸው እንደ ሆነ በዚያን ሌሊት ተነገራቸው:: ሁሉም እንዲወድዱት፣ እንዲንከባከቡትና ጥሩ ጥሩ ነገሮችን እንዲያስተ ምሩት ተነገራቸው:: ሴቶች በትከሻቸው ያዝሉት ነበር:: ወንዶችም ይጠብቁት ነበር::

ትንሹ ልጅ በዚህ ዓይነት የታኬ ልጅ ሆኖ አደገ:: ተገቢው ፍቅርና እንክብካቤ፣ ምግብና ንጽሕናና ልብስ ተሟልቶለት በሥርዓት እንዲያድግ ተደረገ:: ደሳለኝ ሌሎች ልጆች የሚያደርጉትን ነገር ያደርግ ነበር:: እየሮጠና እየዘለለ ይጫወት ነበር:: በየዓመቱ ገና በመጣ ቁጥር ደሳለኝ እንደ ሌሎች ልጆች ሁሉ አዲስ ልብስ ይገዛለታል:: ይህ ሁልጊዜም አስደሳች ጊዜ ነበር::

ሲያድግ ደሳለኝ ከሌሎች ልጆች ጋር ትምህርት ቤት ገባ:: ስሙም ደሳለኝ ታኬ ተብሎ ተመዘገበ:: ወንድሞቹ ትንሹን ልጅ «ባሪያ» ወይም «ባእድ» እያሉ ወይም ሌላ መጥፎ ቃል እየጠሩ ከሚሳደቡ ልጆች ይጠብቁት ነበር:: ታላቁ ወንድማቸው ጉሾ በጣም ጠንካራ ልጅ ስለ ነበረ፣ እርሱ እያለ ማንም ደሳለኝን ለመንካት አይደፍርም::

በቤት ደሳለኝ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር በጎች ይጠብቃል:: እያደገ ሲሄድ ከብቶችንና አህዮችንም መጠበቅ ቻለ:: በበሬ ማረስ፣ መዝራትና ማጨድ ተማረ:: ከወንድሞቹ ጋር ቡና መልቀም፣ ስኳር ድንች መቆፈር፣ አቾሎኒና ዝንጅብል መሰብሰብ ተማረ:: ለእናቱ የማገዶ እንጨት ማምጣት፣ ከብቶች ማታ የሚመገቡትን ሣር መሰብሰብ ቻለ:: ታኬ አንዳንድ ጊዜ ገበያ ይዞት ስለሚሄድ ደሳለኝ ዕቃ መሸጥና መግዛት ተማረ::

ገና ታዳጊ ወጣት እያለ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ተቀበለ:: ቤተሰቡ በየማታው መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነብና ሲጸልይ የተማራቸው ትምህርቶች ከልቡ ውስጥ ዘልቀው ገቡ::



ደሳለኝ ከመጠመቁ በፊት ጥያቄዎች ያቀረቡለት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ደሳለኝ እምነቱን በሚገባ እንደሚያውቅና ጌታን ለመከተል ዝግጁ እንደ ሆነ መሰከሩ:: ወደ 500 ከሚሆኑ ሌሎች አማኞች ጋር ከመንደሩ አቅራቢያ ባለው ወንዝ ውስጥ ተጠመቀ:: ከወንዙ ዳር ሆነው የጥምቀቱን ሥነ-ሥርዓት ከሚከታተሉ ሺ ዎች ከሚቆጠሩ ሰዎች እኔና ባለቤቴ እንገኝ ነበር::

ብዙም ሳይቆይ ከሌሎች ወጣት ልጆች ጋር ደሳለኝ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መሳተፍ ጀመረ:: ሁሉም ሰው አዲስና ትልቅ የጸሎት ቤት ለመገንባትና ለ«ጌታ ማሳ» የሚሆን መሬት ለመግዛት ጥረት ያደርግ ነበር:: ክርስቲያኖቹ ይህን የጌታ ማሳ አብ ረው ነበር የሚያርሱት:: በማሳው ላይ እህል፣ የስኳር ድንችና ዝንጅብል ይተክላሉ:: አርሰው የሚያገኙትን ምርት በመጠቀም ድሆችን ይመግባሉ፣ መጋቢያቸውን ይደግፋሉ፣ ወንጌላውያንን ወንጌል ወዳልደረሰባቸው አካባቢዎች ይልኩበታል::

ጊዜው እየገፋ ሲሄድ፣ ሴት ልጆች እያገቡ ወጡ:: ትልልቆቹ ወንዶች ልጆችም በቤተሰባቸው መሬት ላይ ቤቶችን ሠርተው ትዳር መሠረቱ:: ታኬ ለሁሉም እኩል እንክብካቤ ነበር የሚያደርግላቸው:: የቤተሰቡ ቁጥር እያደገ ሲሄድ፣ ታኬ ተጨማሪ መሬት ገዝቶ ቤተሰቡ አርሶ እንዲጠቀም አደረገ::

ጉሾ በአካባቢው ካሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ ሊሆን ቻለ:: ደሳለኝ በሎሶ በሚገኘው የኤስ አይ ኤም መጽሐፍ ቅዱስ ት/ ቤት ውስጥ ለሁለት ዓመታት ሠልጥኖ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆነ:: ደሳለኝና እኔ ጥሩ ጓደኛሞች በመሆን በስብሰባዎችና በአውራጃ ጉባኤዎች አገልግሎት እንጋራ ነበር:: ደሳለኝ አንዲት ግሩም ክርስቲያን ልጅ አግብቶ ከሌሎች ልጆች ጋር በታኬ መሬት ላይ እያረሰ መኖር ጀመረ:: ለተወሰነ ጊዜ በክርስቲያኖች ላይ ስደት ተነሣ:: ደሳለኝ፣ ጉሾና ተካ ለብዙ ወራት እስር ቤት ውስጥ ቆዩ:: ተቃውሞውና መከራው አማኞችን ከማጠናከርና ከማብዛት በቀር ወደ ኋላ እንዲመለሱ አላደረጋቸውም::

የታኬ ሚስት ስትሞት ደሳለኝ አለቀሰላት:: የሚያውቃት ብቸኛ

እናቱ እርሷው ነበረች። ታኬ እያረጀ ሲሄድ አራቱን ልጆች በአንድነት ጠርቶ፣ «ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ። ጌታን በርትታችሁ ተከተሉት። እኔ እንዳስተማርኩአችሁ ልጆቻችሁን አስተምሩ። ደሳለኝ እንደ ልጄ አሳድጌሃለሁ። ስሜን ሰጥቼሃለሁ። ስመግብህና ሳለብስህ ኖሬአለሁ። አስተምሬሃለሁ። አንተ የእኔ ነህ። አሁን ደግሞ አንተና ሌሎች ልጆቼ ያለኝን ሀብት እኩል እንድትካፈሉ እፈልጋለሁ። እኔ በቅርቡ እሞታለሁ፣ ልጁ ወዳደረገኝ አባቴም እሄዳለሁ። ሀብቴን እኩል እንደምትካፈሉ ቃል ግቡልኝ» አላቸው። አራቱ ልጆች አባታቸው ያላቸውን ለማድረግ ቃል ገቡለት። በባህሉ መሠረት ቀኝ እጆቻቸውን ከታኬ ጉልበት ላይ አድርገው መሃላቸውን አጸኑ።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ታኬ ሲሞት ቤተሰቡ ክርስቲያኖችን ሁሉ ለቀብር ጠሩ። ብዙ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች አክብሮታቸውንና የመጨረሻ ስንብታቸውን ለመግለጽ በዚህ ታላቅ ቀብር ላይ ተገኙ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተሰብስበው ነበር። በቀብር ስፍራው ጉሸና ደሳለኝ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ በመስበካቸው ብዙ ሰዎች ንስሐ ገብተው በክርስቶስ አመኑ።

በዚያን ማታ በመቶዎች በሚቆጠሩ ቤቶች ቤተሰቦች ቅቤና ጨው የገባበት ቡና እየጠጡና ቆሎአቸውን እየበሉ ስለ ታኬና ስለ ልጆቹ ተነጋገሩ። ልዩ፣ እንግዳና መብት ያልነበረው ደሳለኝ የተካ የማደጎ ልጅ እንደ ሆነና አሁን ግን አዲስ ስም፣ አዲስ ቤተሰብ፣ አዲስ ግንኙነት፣ አዲስ አባት፣ ልብሶች፣ ምግብና ትምህርት እንዳገኘ ተነጋገሩ። ከሁሉም በላይ በዚያን ዕለት ስላዩት አዲስ ነገር ተነጋገሩ። ይህ በወላይታ ተሰምቶ የማይታወቅ ነበር። ይህ አዲስ፣ እንግዳና የተለየ ነገር ነበር። ይህም የማደጎው ልጅ ከተወለዱት ልጆች እኩል ሀብት መካፈሉ ነበር። ያ አስገራሚ ነገር ነበር። ይህ ደግሞ ነጻ ስጦታ ነበር - ሰባኪው እንዳለው ጸጋ ነበር - የማይገባ፣ የጥረት ውጤት ያልሆነና ዝም ብለው የሚቀበሉት ስጦታ!

በቀጣይ ቀናት ብዙ ሰዎች ስለዚህ ጉዳይ ለመጠየቅ ወደ ሰባኪው ዘንድ መጡ። ከእነዚህም ሰዎች አንዳንዶቹ ክርስቶስን



እንደ ግል አዳኛቸው በመቀበል ከአማኞች ጋር ይቀላቀሉ ነበር።

በወላይታ የገጠር አካባቢዎች እንዳሉት አብዛኞቹ መጋቢዎች ሁሉ ደሳለኝም ሁለት ሥራዎችን ነበር የሚሠራው። አገልግሎቱን የሚወጣው ከወንድሞቹ ጋር መሬቱን እያረሰ ነበር። ልጆቹም አብረውት ያርሱ ነበር። እየሰፋ ለመጣ የታኬ ቤተሰብ ተጨማሪ መሬት ገዙ። ደሳለኝ በየእሑዱ እየሰበከ፣ የታመሙትን እየጠየቀ፣ ለወጣቶች የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ፣ የጠፉትን እየፈለገ ማገልገሉን ቀጥሏል። ብዙ ጊዜ ወደ ሌሎች አካባቢዎች እየሄደ እንዲሰብክ ግብዣ ይቀርብለታል። በዚህ ጊዜ በአብዛኛው የትምህርቱ ርእስ-ጉዳይ የሚያደርገው «በማደጎ ልጅ የመሆንን መብት» ነበር።

ደሳለኝ ምስክርነቱን በሚናገርበት ጊዜ፣ ማንም ሳይፈልገውና ሳይወደው በሞት አፋፍ ላይ ሳለ ታኬ የራሱ ልጅና የቤተሰቡ አካል በማድረግ ርስትን ጨምሮ ሁሉንም ነገር እንደ ሰጠው ያወሳል። ገላትያ 4:7ን ማንበብ ደስ ይለዋል። ከዚያም በመቀጠል «እኔ የኃጢአት፣ የሰይጣን፣ የሞትም ባሪያ ነበርሁ። ነገር ግን ስለ ዳንሁ ልጅና ወራሽ ሆንሁ። ኢየሱስ ለእኛ ደሙን ስላፈሰሰ፣ ሁላችንም ከሰይጣንና ከዘላለም ሞት ነፃ መሆን የምንችለው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው። በእምነት የእግዚአብሔር ልጆች መሆንና የእርሱን ባለጸግነት በክርስቶስ መውረስ እንችላለን።» እያለ ይሰብክ ነበር።

## ድኅረ ታሪክ

ለመጨረሻ ጊዜ በቦሎሶ ገጠራማ አካባቢ ሳልፍ ደሳለኝን ከመንገድ ዳር አግኝቼው ነበር። በጣም አስደሳች ዳግም ተገናኝቶ መተያየት ሆነልን! ደሳለኝ የታመመና፣ «ወደ ጌታ ለመሄድ ተስፋ የሚያደርግ» አንድ አዛውንት ክርስቲያን ለመጠየቅ እየሄደ ነበር። ደሳለኝ አሁንም የእርሻውን ሥራና የወንጌል ስብከቱን አጣምሮ ያካሂዳል። ደሳለኝና ባለቤቱ ስድስት ልጆችን የወለዱ ሲሆን፣ ሌሎች አያሌ ልጆችንም በማደጎነት ያሳድጋል።



*«ጌታ ሆይ፣ እኔ ማሄ ነኝ:: ዛሬ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?»*





ቡዝዲ
*ለምርከኞች ነጻነትን ማወጅ*



ደፈርሻ
*ከእስር ቤት ነፃ መውጣት*



ማሄ፣ ዲክ እና ናና

*በኦሞ ሸለቆ ውስጥ- የእግዚአብሔር መንግሥት ሠራተኞች*



ላሊሶ
በራእይ አንድ ሰው አይቶአል




ዳንጎ
ጠንካራ ስለሆንክ እና የእግዚአብሔር
ቃል በልብህ ውስጥ ስለሚኖር



ናና
«የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶቹ
አፍ ሊያድንህ ችሏልን?»





ፉንታ
. . . የተዋረደውን ነገር እግዚአብሔር መርጦአል::




ጀማሪ

ድል ለነሣው፣ በአምላኬ
ቤት መታሰቢያ
አደርግለታለሁ



ተካ

እስከ ሞት ድረስ የታመንህ
ሁን፣ የሕይወትን አክሊል
እሰጥሃለሁ



ማሄ

ተካ በሞተበት ጉራ በሚባል መንደር የመታሰቢያ ጸሎት ሲመሩ






የቦዲ ከብት መንጋዎች
ንጉሥ




የቦዲ ጦረኛ
ግዳዮቹን ከሚያመለክቱ ጠባሳዎች
ጋር



የተካ ገዳዮች፡- ከንሺማ
እና ልጁ ዳኩባ

ከእግዚአብሔር ጋር ታ
ረቁ ብለን በክርስቶስ ስም
እንለምናችኋለን።
ኃጢአት የማያውቀውን
ለእኛ ሲል ኃጢአት አደ
ረገው፣ ይኸውም በእርሱ
የእግዚአብሔር ጽድቅ
እንሆን ዘንድ ነው።




የኦሞ ሽለቆ ጦረኛ



የሐመር ጦረኛ





*ሁለት እጅ ወደ ላይ! ሙሉ በሙሉ መማረክ! እጄን ወደ ላይ በማድረግ ሰይጣንን እክዳለሁ! እጄን ወደ ላይ በማድረግ ለኢየሱስ ክርስቶስ እማረካለሁ!*

የኅብረት መተቃቀፍ-
በክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱሳን
ወደ ሆኑት ኅብረት መቀበል





መመሪያ - ሳታቋርጡ ጸልዩ!
ማስጠንቀቂያ - በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፣ አይዞአችሁ
እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ!





ግምባታ
የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚጠብቅ



አልዳቦ
ማንም በክርስቶስ ቢሆን፣ አዲስ ፍጥረት ነው



ዋጋሶ

ውጊያችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም፣ ይልቁንም ከአለቆችና ከሥልጣናት፣ ከዚህ ዓለም የጨለማው ገዢዎች ጋር ነው



ኤካሶ

እናንተ በእኔ ብትኖሩ እና ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፣ የሚያስፈልጋችሁን ጠይቁ ይደረግላችኋል።



ዮሐንስ

በሰላም ዝማሬ ትከብበኛለህ



ኦኒሳ

በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ





በላይነሽ እና ማሔ

ወደምትሄድበት ሁሉ እሄዳለሁ



ርብቃ እና ልጆቿ

ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ያ ደቀ መዝሙር ወደ ቤቱ ወሰዳት



ብርሐኑ እና ተጥላ የተገኘችው ልጁ፣ ቱቲ

*እንግዲህ ወዲህ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፣ ነገር ግን ከቅዱሳን እና ከእግዚአብሔር ቤተሰቦች ጋር ወራሾች ናችሁ*



ሉሺንዳ

*የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ*





የጨለማ ተራራ



ማቴዎስ

*የሚያስተራርቁ ብፁአን ናቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና*




ዋኜ

*እናንተ ለክፉ ያደረጋችሁትን፣*
*እግዚአብሔር ግን ለበጎ አደረገው*



ጣሰው እና የተለወጠ «ዝናብ አምጪ» ጠንቋይ
*ማንም ለሁለት ጌቶች መገዛት አይችልም*





በቦዲ ምድር የእግዚኦብሔር ቃል
*ሲሰበክ በጥሞና የምታዳምጥ ወጣት ኢትዮጵያዊት ሴት*

# ፲፩

# ግምባታ

## የሸባው ሕልም

*«በዚያም ቀን፣ እነሆ፣ አምላካችን ይህ ነው:: ተስፋ አድርገነዋል፣ ያድነንማል:: እግዚአብሔር ይህ ነው፣ ጠብቀነዋል:: በማዳኑ ደስ ይለናል፣ ሐሴትም እናደርጋለን ይባላል::»*

ኢሳይያስ 25:9

*«እግዚአብሔር ሆይ፣ መድኃኒትህን እጠብቃለሁ::»*

ዘፍጥረት 49:18

በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ባለው ኮረብታማ አካባቢ ደስታ፣ ናና እና ማቱሴል የሚባሉ ወንጌላውያን አብረውን በመንዝ ላይ ነበሩ:: ይህ በተራሮችና በዛፎች የተከበበ ወና አነስተኛ ሸለቆአማ አካባቢ ነበር:: እልም ያለ ጫካ ነበር:: ማናችንም ወደዚህ አካባቢ መጥተን አናውቅም ነበር:: ነገር ግን ከብዙ ጸሎት በኋላ ወንጌሉን ወደዚያ ለማድረስ ጊዜው እንደ ሆነ ተገነዘብን:: ከአካባቢው ሰዎች አብዛኞቹ ከዚያ ባፊት ፈረንጅ አይተው አያውቁም ነበር:: ነገር ግን ትንሽዬ ጎጆ ቤት እንድናርፍበት ጠራርገው በማዘጋጀት የፍቅር መስተንግዶ አደረጉልን:: ሴቶቹ ቆሎ ቆልተውና በጨው፣ በቅቤና በበርበሬ ከተቀመመ የቡና ቅጠል የተዘጋጀ ልዩ ቡና አፍልተው አቀረቡልን::

ምሽቱን በቤቱ ውስጥ ለተሰባሰቡት የመንደሩ ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል ስናካፍል አመሸን:: እነርሱም አብረናቸው በመቆየት የጌታን ቃል እንድናስተምራቸው ጠየቁን:: በቀጣዩ ዕለት ማታ



እንደምንመለስ በመግለጽ ወደ ጎረቤት መንደር ሄድን:: ወደተፈለገው መንደር ታደርሰናለች የተባለችውን ቀጭን መንገድ ይዘን ፊትና ኋላ እየተከታተልን ሄድን::

«የሕይወት ቃል አላችሁ? የሕይወት ቃል አላችሁ?» ሲል አንድ ሰውዬ ከመንገድ ዳር ቁጭ ብሎ ይሆን ጥያቄ አቀረበልን:: እኔም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሴን ወደ ላይ አንሥቼ እያወዛወዝሁ፣ «አዎን፣ የሕይወት ቃል አለን» ስል መለስኩለት:: ከፊታችን ከ200 ሜትር በላይ ርቆ ያለው ሰውዬ በተናገርኩት ቃል ደስ ተሰኝቶ ወደ እርሱ እንድንመጣ በእጁ ምልክት አሳየን:: ወደ እርሱ እየፈጠንን ስንጠጋ፣ ሰውዬው በመደጋገም «የሕይወት ቃል አላችሁ» ይል ጀመር::

በኢትዮጵያ ?ቡና ዛፍ በየዱሩ ከሚበቅልባቸው ቦታዎች ይህ አንዱ ነበር:: ለብዙ ዘመናት በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የቡና ፍሬን ጥቅም አያውቁም ነበር:: ጠንቋዮቹ ሰዎቹ የቡና ፍሬዎችን እንዳይለቅሙ ስለ ከለከሏቸው፣ ፍሬዎቹ ከመሬት ላይ ወድቀው ይበሰብሱ ነበር:: ሰዎቹ የቡና ቅጠሎችን በማፍላት ጨውና ቅመማ ቅመም ጨምረው ይጠጡ ነበር::

ከዚያም አንድ ቀን ሁሉም ነገር ተቀየረ:: አንድ ከሰሜን ኢትዮጵያ የመጣ የቡና ነጋዴ በዱር ቡና የሚበቅልበትን ይህንኑ አካባቢ አገኘ:: ነጋዴው በቅሎዎችን ይዞ በመምጣት የአካባቢው ሰዎች የቡና ፍሬዎችን እንዲያመጡለት ጠየቀ:: ቡናውን እንዲያመጡለት ጆኒያዎችን ሰጣቸው:: ሰብስበው ሲያመጡም ልብሶችን፣ ጨው፣ ስኳርና ብዙ ጨሌዎችን ሰጣቸው:: ነጋዴው የቡና ፍሬዎቹን መሬት ላይ አስጥቶ አደረቀ:: የደረቁትን የቡና ፍሬዎች ጭኖ በመውሰድ ሸጦ ከፍተኛ ትርፍ አገኘ:: በዚህ ዓይነት በየዓመቱ ተጨማሪ በቅሎዎችን እየያዘ በመምጣት በአካባቢው ሁለት ወይም ሦስት ወራት ተቀምጦ የሚፈልገውን ያህል ቡና ጭኖ ይሄድ ነበር:: ቀስ በቀስ የአካባቢውን ሕዝብ ቋንቋም አጠና:: ከውጭ መጥተው እንደ እርሱ የአካባቢውን ቋንቋ የለመዱ ጥቂቶች

ብቻ ነበሩ።

አንድ ቀን፣ ነጋዴው ቡናውን ጭኖ ከሄደ ከብዙ ሳምንታት በኋላ፣ አንድ ወጣት ይህ ነጋዴ እንዴት ሀብታም ሊሆን እንደ ቻለ አባቱን ጠየቀ። በየዓመቱ እንዴት ተጨማሪ አገልጋዮችንና በቅሎ ዎችን እንዳገኘና፣ እንዲሁም ከእጁ ላይ የወርቅ ቀለበቶችንና ውድ ልብሶችን እንዴት ሊለብስ እንደ ቻለ አባቱን ጠየቀው። ወጣቱ ከበደ ነጋዴውን በመከተል ለራሱ የተወሰነ ሀብት ለማፍራት ፈለገ። አባቱ፣ አባቱ አትሂድ ቢሉትም፣ ከበደ ፈቃደኛ አልሆነም። አያቱም «አትሂድ፣ አባቴ ይህን ሸለቆ ትቶ አልሄደም ነበር። አያቴም እንደዚሁ። እኔም ብሆን ከዚህ ስፍራ ፈቀቅ አላልኩም። ልጄ፣ እባክህን ትተኸን አትሂድ። ስለ ሚስትህና ስለ ቤተሰቦችህ አስብ» አሉት። ከበደ የሁለት ዓመት ተኩል ሴት ልጅ ነበረችው። በዚህ ላይ ሚስቱ ሁለተኛ ልጅ አርግዛ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ከበደ የጉዞውን አሳብ ለመሰረዝ አልፈለገም። አባቱ እስከ ኮረብታው አፋፍ እየተከተሉ ቢለምኑትም፣ ከበደ አሻፈረኝ ብሎ መንገዱን ወደፊት ቀጠለ። «ከሄድክ መቼም አትመለስም፣» ሲሉ ጮሁ አባቱ።

ከበደ ለአያሌ ቀናት በሸለቆው አካባቢ መጓዙን ቀጠለ። የሚፈራቸው የቦዲና የሙርሲ ሰዎች እንዳይገጥሙት በማሰብ እነርሱ በማይኖሩበት አካባቢ መጓዙን መረጠ። የአሪ ሰዎችን አያሌ መንደሮች አልፎ ሄደ። ሰዎቹ ተግባቢዎች ቢሆኑም፣ እርሱ ግን ቋንቋቸውን አያውቅም ነበር። በምልክት ቋንቋ እየተጠቀመ ምግብ፣ ውኃ እና መኝታ የሚሉትን አሳቦች ይነግራቸዋል። ነገር ግን በሆዱ ውስጥ ያለውን ሕመም ሰዎች እንዲረዱለት ለማድረግ ተቸገረ። በፍጥነት እርዳታ ማግኘት ቢኖርበትም፣ ማንም ቋንቋውን የሚያውቅ ሰው አልነበረም! ወደ ከተማይቱ ለመድረስ ቢፈልግም አቅቶት መንገድ ላይ ወደቀ።

በመጨረሻም፣ አንድ ደግ ሰውዬ አህያ እየነዳ መጣ። ሰውዬው ከበደን አንሥቶ አህያው ላይ በማስቀመጥ ከዚህ በፊት ራሱ ወደታከመበት ባኮ ወደሚገኘው የኤስ አይ ኤም ክሊኒክ አደረሰው። የክሊኒኩ ነርስ ቋንቋውን የማታውቀው ሰውዬ በሽታ ምን እንደ



ሆነ ለማወቅ አልቻለችም። የተቻላትን ያህል እንክብካቤ በማድረግ በርካታ ዓይነት ፀረ-ተሐዋሲያን መድኃኒቶችን ሰጠችው። ነገር ግን ከበደ እየበሳበት ሄደ። በመሆኑም ከባኮ ርቆ ወደሚገኘው ሶዶ የኤስ አይ ኤም ሆስፒታል ተላከ።

ወደ መኪና መንገድ እስኪወጣ ድረስ ሰዎች በቃሬዛ ተ ሸክመውት ሄዱ። መንገዱ ላይ ሲወጣ በጭነት መኪና ላይ ተጭኖ ወደ ሶዶ ተወሰደ። ጉዞው ብዙ ቀናት ፈጀ። ይህ ከዚህ ቀደም መኪና አይቶ ለማያውቀውና የአካባቢውን ቋንቋ ለማያውቀው ከበደ አስፈሪ ገጠመኝ ነበር። በሆስፒታሉ ውስጥ ሐኪም ሆነው በመሥራት ላይ የነበሩት ዶ/ር ናታን ባርሎው እንደ ነርሷ የከበደ በሽታ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ አልቻሉም። ብዙ ከጸለዩ በኋላ በሽታውን ለማወቅ ቀዶ ሕክምና ማካሄድ እንዳለባቸው ወሰኑ። ከበደ በሆስፒታሉ ውስጥ ያሉትን ደጋግ ሰዎች ወደዳቸው። ዶ/ር ባርሎውን ግን በመገረም ነበር የሚያያቸው።

ዶ/ር ባርሎው የከበደን ሰውነት በመቅደድ እንደ ገመቱት ወደ በርካታ ዋነኛ ክፍሎች የተሰራጨ ካንሰር በሰውነቱ ውስጥ አገኙ። ዶክተሩ ከከበደ ሰውነት ውስጥ የቻሉትን ያህል ካንሰር በማስወገድ ከሥቃዩ በመጠኑ እንዲያርፍ አደረጉ። በሆስፒታሉ ውስጥ አልጋ ተሰጥቶት ለአያሌ ቀናት ታከመ። ነገር ግን ዶክተሩ ሞት እንደሚጠብቀው አልነገሩትም። ከዚህ የሚከፋው ደግሞ ስለ አዳኙ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊመሰክሩለት አለመቻላቸው ነበር። በየቀኑ አንድ የወላይታ ወንጌላዊ እየመጣ በወንዶቹ መኝታ አካባቢ ስለ ክርስቶስ ይመሰክር ነበር። ከበደ ግን የሚናገሩትን አይረዳም ነበር። ወንጌላዊው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕሎችን ባሳየ ጊዜ ከዚህ በፊት ሥዕል አይቶ የማያውቀው ከበደ ምንም ሊገባው አልቻለም። ቀስ በቀስ ከበደ እየደከመ ሄደ። ጽዳት፣ ምግብና እንክብካቤ ይደረግለት ነበር።

በዚህ መሀል ቡና የሚለቀምበት ወቅት ደረሰ። ቡና ነጋዴው በቅሎዎቹንና አገልጋዮቹን ይዞ ከሰሜን መጣ። በየዓመቱ የሶዶ ሆስፒታልን በሃያ ኪሎ ሜትሮች ወደ ጎን እየጣለ ቢያልፍም፣ ሶዶ ውስጥ አርፎ አያውቅም ነበር። በዚያን ዓመት ግን ሶዶ ሲደርስ

የጥርስ ሕመም ገጠመው:: በሽታውም ሰውነቱ ሁሉ እንዲያብጥ አደረገው:: ጆሮዎቹ፣ መንጋጋውና ፊቱ በመታመማቸው ነጋዴው ለሥቃይ ተጋለጠ:: ከርቀት አብረቅራቂ ቆርቆሮዎች ያሉበትን የሚሲዮን ሆስፒታል በመመልከቱ የሆነ ሰው እዚያ ቢሄድ የሕክምና ድጋፍ ሊያገኝ እንደሚችል ገለጸለት::

ዶ/ር ባርሎው ነጋዴውን በመመርመር ድዱ ተሰንጥቆ መግሉ ከተወገደ በኋላ ጥርሱን ነቅለው መልሰው ድዱን እንደሚሰፉ ገለጹለት:: ከዚያም የፔንሲሊን መርፌ እየተወጋ ለአያሌ ቀናት በሆስፒታሉ ውስጥ መቆየት እንዳለበት ነገሩት:: በዚሁ መሠረት ህክምና ተደርጎለት ነጋዴው ከሥቃዩ እፎይታ ስላገኘ ደስ አለው:: በወንዶች ክፍል ውስጥ እንዲተኛም ተደረገ:: በአጋጣሚ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ተጉዞ ከሰሜን የመጣው ሰውዬ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ተጉዞ ከደቡብ ከመጣው ሰውዬ አጠገብ ተኛ:: የከበደን ቋንቋ የሚያውቅ ብቸኛ ሰው ከአጠገቡ መተኛቱ ምንኛ አስገራሚ ገጠመኝ ነበር!

በተመሳሳይ ጊዜ፣ በሎስ አንጀለስ አሜሪካ ሪደርሆፍ የጽሞና ጊዜ ዋን ታደርግ ነበር:: በምትጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ኢትዮጵያ እንድትሄድ የሚፈልግ መሆኑን በመረዳቷ ተገረመች:: በጣም ደስ ብሏት ወዲያው ለመምጣት ተዘጋጀች:: ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ሁልጊዜ ፍላጎቷ ነበር:: ጆይ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት በማሰብ የሚሲዮናዊነት ሥልጠና የወሰደች ብትሆንም፣ ተግባራዊ አላደረገችውም ነበር:: መጀመሪያ በ1935 የተከሰተው የኢጣሊያ ወረራ፣ በኋላ ደግሞ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መንገዷን አደናቀፈባት:: በመሆኑም፣ ወደ ሆንዱራስ በመሄድ ለአምስት ዓመታት ስትሠራ ቆይታ በወባ ታማ ወደ አገር ቤት ተመለሰች:: ጆይ ወደ መስክ ሥራ ልትመለስ አልቻለችም ነበር:: ነገር ግን ጌታ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ስለማይችሉ ሰዎች ራእይ አሳያት:: ስለዚህ ጆይ ወንጌላትን በተለያዩ ቋንቋዎች በካሴት መቅረጽ ጀመረች:: ከ6000 በሚበልጡ የዓለም ቋንቋዎች ካሴቶችን እያባዛች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቅጂዎችን ለሚሲዮናውያን ታቀርብ



ጀመር::

አን ሸርውድ እና ሳና ባርሎው ከተባሉት ሁለት አጋሮቿ ጋር ጆይ ወደ ኢትዮጵያ በመድረስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ዘንድ ቀረበች:: እርሳቸውም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች የወንጌል ሸክላዎችን እንድታዘጋጅ ፈቃድ ሰጧት:: ይህ ስራም በብዙ ሚሲዮናውያን ትብብር የተጀመረ ነበር:: ጆይና ጓደኞቿ ወደ ሶዶ ሆስፒታል በመሄድ በተለያዩ ቋንቋዎች ቀረጻዎችን ማድረግ ጀመሩ::

ሌላ የሚያስደንቅ ገጠመኝ ጆይ በሶዶ ሆስፒታል ውስጥ ከበደንና ቡና ነጋዴውን አገኘች:: ዶክተሩ፣ ነርሶቹና ወንጌላዊው ከበደ እንዴት ከኃጢአቱ ሊድን እንደሚችል ለማስረዳት የቡና ነጋዴው እንዲተረጉምላቸው ያደርጉ ነበር:: ከበደ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ · አድርጎ በተቀበለ ጊዜ፣ ሁሉም ደስ አላቸው:: ጆይ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ወደ ከበደ ቋንቋ ለመተርጎም የኤስ አይ ኤም ሚሲዮናውያንን፣ ወንጌላዊውንና የቡና ነጋዴውን ተጠቀመች:: በዚህ ዓይነት ዓረፍተ ነገር በዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ በሀረግ እና ቃል በቃል አስተርጉማ የወንጌል ሸክላዎችን አዘጋጀች::

የቡና ነጋዴው፣ ከሕመሙ ከዳነ በኋላ ወደ ሥራው ተሰማራ:: ከከበደ አገር ሲደርስ በሶዶ ሆስፒታል እንዳገኘው ይህ ርጉም ሰው ለማንም ትንፍሽ አላለም:: ሲጠባበቁ የነበሩት ቤተሰቦቹ የሞቱን ዜና የሰሙት ከ10 ዓመታት በኋላ ነበር:: ከበደ ሶዶ ውስጥ አርፎ ከሆስፒታሉ አጠገብ ባለች አነስተኛ መካነ መቃብር ውስጥ ተቀበረ:: ልክ አባቱ እንደ ተነበዩት ከበደ ወደ ቤተሰቡ ተመልሶ አልመጣም!

የተቀረጹት መልእክቶች ወደ አሜሪካ ተልከው ተባዙ:: ከዚያም ወደ ሶዶ ሆስፒታልና በመቀጠልም እኛ ወዳለንበት ወደ ባኮ ተላኩ:: መልእክቶቹን በገበያ ቦታ፣ በክሊኒክና በመንደሮች ውስጥ ስናጫውት ቋንቋውን የሚያውቅ ሰው ጠፋ:: ስለዚህ ዝም ብለን አስቀመጥናቸው:: ወደ ቡልቂ በሄድን ጊዜ እዚያም መልእክቶቹን ለሰዎች አሰማን:: በዚህ ጊዜ ይህ በስተ ምዕራብ የሚገኘው የዲማ

አዘነ! ሁሉም ነገር ወደመ:: ተስፋ በመቁረጥ ለርዳታ አለቀሰ::

በ1970 ተካ አንድ አስገራሚ ዜና ሰማ! ይኸውም የዲማ ዋንኛ ጠንቋይ አካባቢውን ለቅቆ የሚሄዱ ጉዳይ ነበር! ዋንኛው ጠንቋይ ዳኖ ወደ ማሎ በመሄድ በኢየሱስ እንዳመነ ይወራ ጀመር:: ሰይጣንን በመካድ ሕይወቱ ተለውጦ፣ ንጹሕና ደስተኛ አዲስ ሰው ሆኗል:: ከተወሰኑ ወራት በኋላ ዳኖ ዳንኤል ጮራሞ ከተባለ ሰባኪ (የማሄ ወንድም) ጋር ወደ አካባቢው ተመለሰ:: በአንድነት በሁሉም ስፍራ እየዞሩ ሰዎችን ከኃጢአት ሊያድንና የልብን ሰላም ሊሰጥ ስለሚችል አዳኝ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስበክ ጀመሩ::

የመጀመሪያው አማኝ ተካ ነበር! ለኃጢአት፣ ለሰይጣንና ለሰዎች ባርነት የሰለቸው ተካ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት አገኘ:: በሙሉ ልቡ ወደ ጌታ መጣ! ወዲያውኑ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀመረ:: ጥምቀትም ወሰደ:: በኋላም ቡልቂ ወደሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ገብቶ ለአንድ ዓመት ተማረ:: የመሬት ከበርቴውንም ትቶ ሄደ:: የመሬት ከበርቴውም በአገሪቱ ላይ በተከሰተው ለውጥ ሳቢያ ንብረቱ ሁሉ ተወስዶበት በወኅኒ ተጣለ:: ተካ አካባቢውን ለቅቆ በመሄዱ፣ መሬቱን፣ ቤቱንና የአትክልት ቦታውን አጣ:: ነገር ግን ጥቂት እንስሳቱን በመሸጥ ገንዘቡን እናቱ ዘንድ ደበቀ::

ተካ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ ለክርስቶስ «ተሸጦ» ነበር:: እግዚአብሔር ለዚህ ብቸኛ ሰው ብዙ ዕቅዶች እንዳሉት ወዲያው መታየት ጀመረ:: ስለሚበላው፣ ስለሚለብሰውና ስለሚተኛበት ስፍራ ብዙም ግድ አልነበረውም:: የእግዚአብሔርን ቃል በመማር አብዛኛውን ጊዜ በጸሎት ያሳልፍ ነበር:: በክርስቶስ የሚገኘውን አዲስ ሕይወት በዲማ መንደሮች ሁሉ መስበክ ጀመረ:: ይህን የምስክርነት ሥራ በአብዛኛው የሚያከናውነው ከዳኖና ከጥቂት የአካባቢው አማኞች ጋር በመሆን ነበር:: የተካ አባት የሞቱት ከ20 ዓመታት በፊት ቢሆንም፣ ነገር ግን ተካ እናቱን፣ ታናሽ ወንድንሙንና እኅቱ ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ቻለ::

ተካ በየቀኑ አዳዲስ ነገሮችን በመማር በክርስቶስ እያደገ መሄዱን ቀጠለ:: ብቸኛ የነበረው ተካ ለጌታ ሙሉ በሙሉ ራስን



ከመስጠትና ከሙሉ ታዛዥነት ያነሰ ነገር ለመቀበል ትዕግሥት አልነበረውም:: ይህ መከራ ያደነደነው ባተሌ የምስራቹን ላልሰሙት ሰዎች ከባድ ሸክም ነበረበት:: ወንጌል ወዳልደረሰባቸው ቦታዎች ያላንዳች መታከት የመሄድ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው::

ከዚያም በ1975 የቦዲ ተዋጊዎች በቦሮዳ ኮንታ ከፍተኛ ጥቃት ሰነዘሩ:: ባለቤቴና እኔ ከወላይታ ወንጌላውያን ጋር በመሆን በአካባቢው የወንጌል ስብከት እናካሂድ ነበር:: በዚያን ዓመት ከተ ገደሉት 3000 ሰዎች መካከል በመቶዎች የሚቆጠሩት ክርስቲያኖች ነበሩ:: 15ቱ የጸሎት ቤቶች ወደሙ:: በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ወደተለያዩ ቦታዎች በመሄዳቸው፣ አያሌ መንደሮች ባድማ ሆኑ:: የግድያው ዜና እየበረከተ ሲመጣ፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ለቦዲ ጎሳ መጸለይ ጀመሩ::

በነሐሴ 1975 የመጀመሪያው የጉብኝት ሥራ ሲጀመር ከናና፣ ከካሳና ከእኔ ጋር ተካም አብሮ ነበር:: አብዛኞቹን መንገዶችንና የቦዲን ቋንቋ ስለሚያውቅ፣ ስለ አዳኙ ለቦዲ ሰዎች ለመመስከር በደስታ ተነሣሥቶ ነበር:: ከዚሁ የአሥር ቀናት ጉብኝት ስንመለስ፣ ተካ እግዚአብሔር ለቦዲ ጎሳ ወንጌሉን እንዳካፍል ጠርቶኛል ሲል ገለጸልኝ:: ራሱን ሙሉ በሙሉ ለዚህ ሥራ ለጌታ አሳልፎ ሰጠ::

ተካና ናና ወደጎበኘነው የቦንኬ መንደር ተመለሱ:: በየትኛውም ጊዜ በጨካኝ የቦዲ ወጣቶች ሊገደሉ እንደሚችሉ እያወቁ በአስጊ አደጋ ውስጥ ነበር በዚያ የኖሩት:: በቦዲ ባህል መሠረት ወጣቶች ጋብቻ ሊፈጽሙ የሚችሉት የሌላ ጎሳ አባላትን ሲገድሉ ብቻ ነበር:: ለተወሰነ ጊዜ ወንጌላውያኑ በመንደሩ ውስጥ እንደ እስረኛ ሆነው ቆዩ::: የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለማምጣት ተካ ወደ ዲማ ወይም ቡልቂ በሚሄድበት ጊዜ ናና እዚያው መቆየት ያስፈልገው ነበር:: ከስድስት ወራት በኋላ አካባቢውን ለቅቀው ለመሄድ ቻሉ:: ይህም የሆነው የቦዲ ተዋጊዎች እንደገና ጥቃት ከመጀመራቸው በፊት ነበር:: በ1976 ዓ.ም 500 ሰዎች በማሎና በዲማ ሲገደሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ከብቶች ተዘረፉ:: ሰዎች እንደገና በየቦታው ተበታተኑ::

ጎሳ ቋንቋ ሳይሆን አይቀርም የሚሉ ሰዎች አጋጠሙን:: በዚህ ጊዜ የተቀረጹትን መልእክቶች በሳጥን ውስጥ አድርገን ከአልጋ ሥር አስቀመጥን:: በዚህ ጊዜ ብል የሸፋን ጽሑፉን እንክት አድርጎ በላው:: ሌላ የሚሲዮን ጣቢያ ለመመስረት ስንሄድ እነዚህን መልእክቶች ይዘን ለመሄድ አልቻልንም:: ብዙ ዓመታት አለፉ::

በመጨረሻም፣ ሌሎች ሚሲዮናውያን እነዚህን የሸክላ መልእክቶች በካሴቶች ቀዱ:: የካሴቶቹን የሽፋን ላይ ጽሑፎች ለማንበብ ባለመቻላቸው «የማይታወቅ ቋንቋ» የሚል ሐረግ ከተቀ ረጹት ካሴቶች ላይ ጻፉ:: ሚሲዮናውያን በደርግ መንግስት ተባር ረው ከቡልቂ ሲወጡ፣ አንዳንድ ነገሮችን ጥሎ መሄድ ግድ ሆነባቸው:: እኔም ወደ በዲ ጎሳ በምሄድበት ጊዜ ወደ ቡልቂ ስደርስ ካሴቶቹን አግኝቼ ወሰድኩአቸው:: ቋንቋውን የሚናገሩትን ሰዎች አገኝ ይሆናል የሚል ግምት ነበረኝ::

«የሕይወት ቃል አላችሁ?» ሲል ሰውዬው እንደገና ጮኸ:: እየቀረብን ስንመጣ፣ ሰውዬው ሁለት እግሮቹ ሽባ የሆኑበት አዛውንት መሆኑን ለመረዳት ቻልን:: መቆም አይችልም:: እግሮቹ በአደጋ ምክንያት ከተሰበሩ ብዙ ዓመታት አልፈዋል:: ተገቢውን ሕክምና ባለማግኘቱ ምክንያት ሽባ ሆኖ ቀረ:: ከመንገዱ ዳር ቁጭ ብሎ ነበር:: ሊንቀሳቀስ የሚችለው በሁለት እጆቹ በመሳብ ብቻ ነበር:: አራት አገልጋዮች ለአንድ ማኅበረ ምእመን ወንጌሉን አብራርንለት:: ለቀጣይ ሁለት ሰዓታት «ጥንታዊውን» የእግዚአብሔር ጸጋና ፍቅር «ታሪክ» ተረክንለት::

ግምባታ ከዚህ በፊት ሚሲዮናዊም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አይቶ አያውቅም:: ነገር ግን ልክ ውኃ እንደሚመጥ ስፖንጅ በዚሁ ስፍራ ተቀምጦ አፉን ከፍቶ ያዳምጠን ጀመር! ሁኔታውን ስናይ በጣም አስደሰተን:: ስለ ኢየሱስ ብዙ በነገርነው መጠን እርሱም ብዙ ጥያቄዎችን ያነሣ ጀመር:: ጉዞአችንን መቀጠል ስለ ነበረብን፣ ስለ ክርስቶስ የበለጠ እንዲያብራራ ወንጌላዊ ደስታን እርሱ ዘንድ ትተን ሄድን:: ስንሄድ አነስተኛ የካሴት ማጫወቻና ሁለት ካሴቶችን



ለደስታ ሰጠነው:: ከሁለቱ ካሴቶች አንደኛው የያዘው የንግድ ቋንቋን ሲሆን፣ ግምባታ ቋንቋውን አያውቀውም ነበር:: ሌላኛው ካሴት «የማይታወቅ ቋንቋ» የሚል ጽሑፍ የሰፈረበት ነበር::

ማምሻውን ከሄድንበት ተመልሰን መጣን:: ስንመለስ ብዙ ሰዎች በግምባታ ዙሪያ ተሰብስበዋል:: ደስታ ከዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጦ በማረፍ ላይ ሲሆን፣ ግምባታ አሁንም ካሴቱን በማዳመጥ ላይ ነበር:: የቴፑ ባትሪ ወደ ማለቁ የተቃረበ ቢሆንም፣ ግምባታ ወደ ጆሮው አስጠግቶ በመስማት ላይ ነበር:: አንዳንድ የግምባታ ጎ ረቤቶችና ቤተሰቦች መጥተው ነበር::

ደስታ ግምባታ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ዝግጁ መሆኑን ገለጸ:: ተነሥቶ መቆም ባይችልም፣ ሁለት እጆቹን በማንሣት ሰይጣንን፣ የመናፍስት አምልኮንና የደም መሥዋዕትን ተቃወመ:: ከዚያም ግምባታ ሁለት እጆቹን በማንሳት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ተቀበለ:: ይህ ያለ ምንም ማመንታት ሙሉ በሙሉ መሰጠትን የሚያመለክት ነበር:: እኛም ደስ ብሎን ከእርሱ ጋር አብ ረን ጸለይን:: ከዚያ በኋላ ግምባታ ቤተሰቡና ወዳጆቹም ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲቀበሉ የሚፈልግ መሆኑን አስታወቀ:: በካሴቱ ውስጥ ያለው ድምጽ ከብዙ ጊዜ በፊት የሄደውና ተመልሶ ያልመጣው የልጁ ድምጽ እንደ ሆነ ተናገረ:: በዚያን ዕለት የከበደን ሚስትና ሁለት ሴት ልጆቹን አገኘናቸው:: ሚስቱ ሌላ ሰው አግብታለች:: ልጆቹም አድገው አግብተዋል:: እነርሱንም ወደ ክርስቶስ የመምራት ዕድል አገኘን:: ይህ ምንኛ አስደሳች ቀን ነበር!

ስናልፍ ለምን እንደ ተጣራ ግምባታን ጠየቅኩት:: አንድ ማታ በአነስተኛ የጎጆ ቤቱ ላይ ሳለ ሕልም እንዳየ ነገረኝ:: በሕልሙ ውስጥ አንድ ሰው፣ «የሕይወት ቃል እየመጣ ነው! የሕይወት ቃል እየመጣ ነው! የሕይወትን ቃል ስማና ለዘላለም ኑር!» ሲል እየተናገረ በሩጫ ሲያሽቆለቁል ተመለከተ:: በዚያ አካባቢ ዘንዶ ዎች፣ መርዛማ እባቦችና ሌሎችም የዱር አራዊት ስላሉ፣ ሰዎች ማታ ማታ አይንንዙም ነበር::

ነገር ግን ሕልሙ ጥርት ብሎ ስለ ታየው፣ ግምባታ በቀጣዩ

ጠዋት እየተሳበ ወጥቶ መንገዱ ላይ ቁጭ አለ:: የሚመጣውን ሰው የሕይወት ቃል አላችሁ ወይ? እያለ ሲጠይቅ ዋለ:: ምን እንደሚል ስለማይገባቸው ዝም ብለው አልፈውት ይሄዱ ነበር:: ግ ምባታ ቀኑን ሁሉ ጠበቀ::

እያንዳንዱን መንገደኛ ቢጠይቅም፣ የሚረዳው ሰው አላገኘም:: ምሽት ላይ ቤተሰቦቹ መጥተው ተሸክመው ወሰዱት:: አሁንም ነገ ጠዋት ተነሥቶ ወደ መንገዱ ዳር በመቀመጥ ያንኑ ጥያቄ መጠየቁን ቀጠለ:: ነገ፣ ከነገ ወዲያ፣ ከዚያ ወዲያ...

ስምን ያህል ጊዜ በመንገድ ላይ ተቀምጦ የሕይወትን ቃል ሲጠብቅ እንደ ኖረ ጠየቅኩት:: «ለሃያ ዓመታት» አለኝ:: ስለሆነም የሕይወት ቃል እንዳለን ስንነግረው ደስ መሰኘቱ የሚያስገርም አልነበረም:: በዚያን ዕለት አንድ ሰው የሕይወትን ቃል ለመስማት 20 ዓመታት መጠበቁን በማሰብ አለቀስኩ:: ዛሬም ይህንኑ ግሩም የደኅንነት፣ የይቅርታና የዘላለም ሕይወት መልእክት ለመስማት የሚጠባበቁ እጅግ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን ስለማውቅ በልቤ አለቅሳለሁ::

## ድኅረ ታሪክ

ከግምባታ ጋር ከተገናኘን ከሁለት ወራት ያህል በኋላ የደርግ መንግሥት የውጭ አገርም ሆነ ኢትዮጵያውያን የወንጌል መልእክተኞችን ሁሉ ከኦሞ ወንዝ ሸለቆ አካባቢ አባረረን:: ወደዚያ አካባቢ ተመልሼ የሄድኩት ከአሥራ አምስት ዓመታት በኋዋላ ነበር:: በዚህ ጊዜ ከወንጌላዊ ግርማ ደብዳቤ አገኘሁ:: ወንጌላዊው እግዚአብሔር ጥቂት ክርስቲያኖች ወደነበሩበት ወደዚሁ አካባቢ እንዴት እንደ መራው መሰከረልኝ:: እነዚህን ሰዎች በማስተማርና ለጥምቀት በማዘጋጀት ስድስት ወራት አሳልፎ ነበር:: ግርማ ለዕ ጩ ተጠማቂዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳካፍል ጠየቀኝ:: እኔም እግዚአብሔር በዚያ አካባቢ ያደረገውን ነገር ለመመልከት በጣም ጓጉቼ ነበር::

ከወንጌላዊ ማሄ ጋር ወደዚያው የቦዲ አካባቢ እንደገና በመኪና አመራን:: ሃና በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ አደርንና መኪናችንን



እዚያው ትተን ወደ ተራራውና ከዚያም ወደ ግምባታ መንደር አመራን:: መንገዱ ከስድስት እስከ ስምንት ሰዓት ይወስዳል ስለተ ባልን፣ እንደ ነጋ ቀደም ብለን ጉዞ ጀመርን:: ጊዜው በጣም ፀሐያማ ነበር:: ዳገቱ ደግሞ ከ15 ዓመታት በፊት ከነበረው በላይ ሽቅብ ሆነብን:: በመንገዱ ላይ ለማረፍ ብዙ ጊዜ ካሳለፍን በኋላ፣ 11 ሰዓት ተጉዘን ከቦታው ደረስን:: ነገር ግን ለሕዝቡ እንደገና የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈል ምንኛ አስደሳች ነገር ነበር! ግምባታ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት መሞቱን በመስማቴ አዘንኩ:: እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ ለጌታው ታማኝ ሆኖ በመኖሩ በክርስቲያናዊ ሥርዓት መቀበሩን አረማውያኑ የአካባቢው ሰ ዎች ተናገሩ:: በቀጣዩ ቀን መጀመሪያ የተጠመቀው የግምባታ ወንድም ነበር:: ከዚያም ሌሎች 25 ሰዎች ተከተሉት:: ከዚያ በኋላ ብዙ ሰዎች በማመናቸውና በመጠመቃቸው በብዙ መንደሮች ውስጥ የጸሎት ቤቶች ተሠርተዋል::

ለምሪቱና ለጸጋው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! ይህ ሁሉ ግጥምጥሞሽ የተፈጠረው አካል ጉዳተኛው አዛውንትና ብዙ የአካባቢው ሰዎች የሕይወትን ቃል ሰምተው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመጡ የእግዚአብሔር እጅ ውጤት ነው ብዬ አምናለሁ:: እናንተም እንደዚሁ እንደምታምኑ ተስፋ አደርጋለሁ!

# 12

# ተካ

## ሰማዕት ለክርስቶስ

*«ማንም እርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም።»*

ሉቃስ 9:62

ከ30 ዓመታት በፊት በመጋቢት 1977 የሚከተለውን ጽፌ ነበር። «ወንጌላዊ ተካ ሚካኤል ለቦዲ ሰዎች ወንጌልን በሚሰብክበት ጊዜ በቅርቡ በጉራ ለክርስቶስ ተሠውቷል። ለቦዲ ሰ ዎች የወንጌል ስብከት ለማድረግ በሚንዝበት ጊዜ እነዚህ ጨካኝ ሰ ዎች ገድለውታል። እኔን እየጠበቀ ለአንድ ሳምንት ያህል ጉዞውን አዘግይቶት ነበር። አብረን ለመሄድ ያቀድን ቢሆንም፣ ኃይለኛ የአንጎል ወባና ተቅማጥ ስላመመኝ ለመሄድ አልቻልኩም። ሌሎች ወንጌላውያን እኔን ለመተካት የሚፈልጉ መሆናቸውን ቢናገሩም፣ ተካ ብቻውን ለመሄድ ወሰነ።

ተካ ከገና በፊት ጉዞውን የጀመረው ለቦዲ ጦረኞችና በኦሞ ወንዝ አካባቢ ለሚኖሩ ዘላኖች የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ ሲል ነበር። በፍጥነት ተመልሶ የሚሲዮናውያንን የአየር ማረፊያ ለመመልከት ቃል ገብቶ ነበር። የአየር ማረፊያውን በመሥራቱ በኩል ተካ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጎ ነበር። የገናን በዓል ከናና፣ ካሳ እና ከእኔ ጋር በጊዩ ለማሳለፍና ለአካባቢው ሰዎች የገናን ትርጉም ለማሳየት ፈልጎ ነበር።

ተካ የተጓዘው ብዙ ንብረቶችን በመያዝ አልነበረም። በወቅቱ የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ፣ የአዲስ ሕይወትን ምንነት ለማብራራት



የሚጠቀምባቸው ሥዕሎች፣ የውኃ መያዣና ሸጠ ምግብ የሚገዛባቸው ምላጮች ብቻ ነበሩት። ከሸሚዙና ከቁምጣው ላይ ቀለል ያለ ልብስ ጣል አድርጎ ነበር የወጣው።

ቀናት በሳምንታት እየተተኩ ሲመጡ ተካን ልናገኝ እንዳልቻልን በመግለጽ ሰዎች እንዲጸልዩለት መጠየቅና ማፈላለግ ጀመርን። ሌ ሎች ወንጌላውያን በቡድን ፍለጋ ጀመሩ። የ«ወዳጅነት» መንፈስ ያላቸው የቦዲ ሰዎች የኦሞን ወንዝ አቋርጠው ከተመለከቱ በኋላ ተካ በዚያ በኩል እንዳላለፈ አስታወቁ። ከብዙ ሳምንታት በኋላ ተካ አንድ ምሽት በጉራ ከብት አርቢዎች ቤት ውስጥ እንዳደ ረና ከቤታቸው ወተት እንደ ጠጣ፣ ሲነጋ ግን ወደ ሌላ መንደር መሄዱን ለመረዳት ቻልን። በጫካው ውስጥ የነበረችውን ቀጭን መንገድ ተከትሎ ወደ ሌላ መንደር እንደ ሄደ ነገር ግን እንዳልደረሰ ታወቀ። እኛ የገናን በዓል በማክበር ስንደሰት፣ ተካ በሰማይ እጅግ ከወደደውና በትጋት ካገለገለው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነበረ።

ተካ ከ40 ዓመታት በፊት ድሀ በሆነች የዲማ መንደር ውስጥ ከገበሬ ቤተሰብ ተወለደ። ሞቃታማና ወባማ ሸለቆዎች ዲማን ከብበዋታል። መንደሪቱ ራሷ ያረፈችው አባጣ ጎባጣ ገጽ ባላቸው ተራሮች ላይ ነው። ጥቅጥቅ ያሉ ጫካዎች ሞልተዋታል። ቀዝቃዛ ጅረቶች በየቋጥኙ ላይ እየተንከባለሉ የቦዲን አገር አቋርጠው ወደ ኦሞ ወንዝ ይገባሉ። ከሦስት ሺህ ሜትር በላይ ከፍታ ያለውና ደመና የለበሰው ግዙፉ የስሚዝ ተራራ የዲማን መንደር ከበስተማዶ ይገላምጣታል። በአንድ ወቅት ወደ 25,000 ይጠጋ የነበረው የዲማ ሕዝብ ቁጥር፣ በበሽታና በእርስ በርስ ጦርነት ተመናምኖ አሁን ወደ 2000 ወርዶአል። ክብ የድንጋይ ቤቶች፣ የድንጋይ አጥሮችና አስደናቂ የእርከን ፍርስራሾች በሐ ረግና በዛፍ ተውጠው በየጫካው ውስጥ ፈስሰዋል። ወንዶች የብ ረት አፈር ከመሬት ቆፍረው ያወጣሉ። ከዚያም በአካባቢው ሸክላ በሠሩት እቶን ውስጥ ያቀልጡታል። ከስድስት የማያንሱ ሰዎች ላብ እያስመጣቸው ወናፍ በመንፋት ለእቶኑ ከፍተኛ ሙቀት ይፈጥራሉ። ለእርሻ ሥራ የሚያገለግሉ እንደ ማረሻ፣ መጥረቢያና

መኮትኮቻ ያሉትና ቢላዋ፣ ጦርና ቆንጨራ የመሳሰሉት የሚሠሩት በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር።

ልክ እንደ ወላጆቹ፣ ተካ ያደገው ጨለማን፣ አጋንንትንና ጠንቋዮችን በመፍራት ነበር። የዲማ ሰዎች የአያት ቅድማያቶቻቸውን መናፍስት የሚፈሩ፣ በጠንቋዮች አማካኝነት ለክፉ መናፍስትና ለሰይጣን መሥዋዕቶችን የሚያቀርቡ አረማውያን ነበሩ። ተካ በፍጥነት ጠንካራ ልጅ ሆነ። ማረስ፣ እንዲሁም የጨካኙን ባላባትና የእብሪተኛ ሚስቱን ከብቶች መጠበቅ ጀመረ። ይህች ሴት በገዛ ነፃ መሬታቸው የሚኖሩትን ሰዎች እንደ ባሪያ አድርጋ የምትገዛ ነበረች። ባላባቱ ለተካ ከባድ ጭንት ካሸከመው በኋላ፣ «አህያ» እያለ ይሳለቅበት ነበር። ድብደባዎች፣ ግርፋቶችና በደሎች የተለመዱ ድርጊቶች ሆኑ። ነገር ግን በሞቃታማው ሸለቆ ውስጥ ብዙ ጊዜ ማሳለፉ ሰውነቱን አደነደነው። ተካ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች በመጓዝ ለባላባቱ ሸክሞችን ያደርስለት ነበር። ይህም ሸክም ከሰዎች የተቀበላቸውን ግብሮች፣ ስጦታዎችና ጉቦዎች የሚጨምር ነበር። የባላባቱን ዕቃዎች እየተሸከመ በኦሞ ሸለቆ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር፣ ተካ አምስት ቋንቋዎች ለማወቅ ቻለ።

የተካ ታላቅ ወንድም የዲማን ባርነት ሸሽቶ ከ15 ዓመታት በፊት የወጣ ሲሆን፣ ወደዚያ አካባቢ ተመልሶ አያውቅም። የሕይወቱ አስከፊ ገጽታ ቢያሳዝናትም፣ እናቱ ተካ ከቤት እንዲሆን ፈለገች። ተካ ግላንጼ የምትባል የዲማ ልጃገረድ አግብቶ አንዲት ሴት ከወለደችለት ከሁለት ዓመታት በኋላ ከትኩሳት በሽታ የተነሣ ሕይወቷ አለፈ። ከዚህ በኋላ ተካ የሙት ወንድሙን ሚስት አገባ። እርሷም በተስቦ በሽታ ታማ ሞተች። አያሌ ሴቶች እየመጡ ቢሄዱም፣ ተካ ዕረፍትም ሆነ ሰላም አላገኘም። ሴት ልጁ ወባ ታማ ስትሞትበት፣ ተካ በጣም አዘነ። ከዚህ በኋላ ማረፊያ ያጣ ተቅበዝባዥ ሆነ።

በዚህ ወቅት የአካባቢው የቦዲ ጎሳ በዲማ ላይ ጥቃት ሰነዘረ። ሰዎች ቢፈሩም፣ ተካ ግን መልሶ የሚያጠቃበትን መንገድ ይፈልግ ነበር። በወቅቱ በርካታ የዲማ ሰዎች ተገደሉ። የቦዲ ተዋጊዎች ሰዎችን በመግደል፣ በመዝረፍና እንስሳትን ማርከው በመውሰድ ተወዳዳሪ እንደሌላቸው የዲማ ሰዎች ተገነዘቡ። ባላባቱም ሳይቀር ከብቶቹን ለመነጠቅ ተገደደ። ከዚያ በኋላ አባሰንጋ የተባለው የከብት በሽታ በመነሣቱ ተካ የቀሩት ከብቶቹ ሞቱበት። ቤተሰቡ፣ ሀብቱና ተስፋውም ሳይቀር ከዱት።



ከወደ ተራሮች አካባቢ አዲስ ትምህርት እንደ መጣ የሚያስረዱ ወሬዎች በየሳምንቱ በሚቆመው ገበያ ላይ ይናፈሱ ጀመር። ስለ አዲስ ሕይወት፣ ከሰይጣንና ከሞት በላይ ጠንካራ ስለሆነ አዳኝ፣ አዲሱን ሃይማኖት ይዘው ስለ መጡት የውጭ አገር ሰዎች፣ ስለ ሕይወት መጽሐፍና ባለሥልጣናት ስለሚቃወሙአቸው፣ ስለሚያስደበድቡአቸውና ስሚያሳስሩአቸው ወንጌላውያን የሚናገሩ ዜናዎች ተበራከቱ። ሰዎች ይህንን አዲስ የምስራች መስማት እንደሌለባቸው ማስጠንቀቂዎች ይሰጡ ጀመር። ተካ ነጻነት፣ አዲስ ሕይወት፣ ሰላም እውነት ይሆን? ሲል አሰበ! በሆነ ብሎም ተስፋ አደረገ።

በመሬት ከበርቴው ሥር ከባዱን ሕይወት መግፋት ከዓመት ወደ ዓመት ቀጠለ። ጠንቋዮቹም ቢሆኑ ብዙ ነገሮችን ይፈልጋሉ። ተካ ብዙውን ጊዜ ስለ ጉዳዩ ከጓደኞቹ ጋር በመነጋገር የተሻለ ሕይወት ይኖር ይሆን? እያለ መላ ይፈላልግ ነበር። አዲሱ ትምህርት በአቅራቢያቸው ወዳሉት የማሎና ገሊላ ጎሳዎች እንደ መጣ ወሬ ሰሙ። አንዳንድ ሰዎች ይህ ትምህርት እውነት ሊሆን ይችላል ብለው አሰቡ! ተካ በጎፋ «የኢየሱስ ተከታዮች» መታሰራቸውንና «የጸሎት ቤቶቻቸውም» መቃጠላቸውን ሰማ። በዚህ ጊዜ በባስኬቶና በአሪ ጎሳዎች መካከል ወንጌላውያን ነበሩ። እነዚህ ለዲማ የቅርብ አካባቢዎች ስለሆኑ ተካ ምናልባት ወደ ዲማም ሊመጡ ይችላሉ ሲል አሰበ።

በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ አዲስ የቢጫ ወባ ወረርሽኝ የኦሞን ሸለቆ ያምስ ገባ! በሽታው በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ የማይታወቅ በመሆኑ፣ ወደ ብዙ ጎሳዎች በቀላሉ ተዛመተ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም ሞቱ። በየቦታው ዘመዶች፣ ጓደኞችና ጎረቤቶች ሞቱ። መንደሮች እንዳሉ ባዶአቸውን ቀሩ! ተካ ለአያሌ ሳምንታት ታሞ ዳነ። ይሁን እንጂ፣ ከጎሳው አባላት ብዙ ሰዎች በመሞታቸው ተካ

በ1976 ተካ፣ ናና፣ ካሳና ጀማሪ ከእኔ ጋር ጊዩ ወደተባለው የቦዲ መንደር መጡ፡ ይህ የሸርም ጎሳ ማዕከል ሲሆን፣ በቦጋ ወራት የሚደርቅ አንድ አነስተኛ ወንዝ ነበር። ከዚያ ተነሥተን ወደ ቦዲ መንደሮች አካባቢ ደረስን። ተካ እና እኔ የኢየሱስን ታሪክ ደግመን ደጋግመን ለመናገር በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ተጓዝን። ብዙውን ጊዜ የምንተኛው ሜዳ ላይ ወይም በቦዲዎች ጎጆ ውስጥ ነበር። አናት የምትበሳ ፀሐይ፣ በእሾሃማ ቁጥቋጦዎች መካከል የሚያልፉ ሸካራ መንገዶች፣ ዝንቦችና የወባ ትንኞች ፈታኞቻችን ነበሩ። ለተካ እነዚህ ነገሮች ትዝ የሚሉት አይመስሉም - ስለ ለመዳቸው። ነገር ግን እኔ ሳማርር ወይም እ ረፍት ስፈልግ ችግሬን የመረዳት ብቃት ነበረው።

የተካ ጸሎቶች እውነተኛና አንዳንድ ጊዜም ያልተለመዱ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ እውነተኛነቱንና ለክርስቶስ መስጠቱን የሚክድ ሰው አልነበረም። ሁልጊዜም ጸሎቱን የሚጀምረው፣ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ይኸው በፊትህ ነኝ። ተካ ነኝ። እየጸለይኩ ነኝ» በማለት ነበር። ከቶውንም ማባበል የሚችል አልነበረም። ልቡን ከፍቶ የሚያሳይ ሰው ሲሆን፣ የሚናገረው እንደ መጣለት ነበር። ብልጣብልጥ ባይሆንም፣ ታማኝ ነበር። ምሁር ባይሆንም፣ ለመማር የሚጓጓና እምነት የሚጥል ሰው ነበር- የሚያምንና የሚታመኑበት። ነፍሰ ገዳይ በሆኑ ወንዶችና ሴቶች መካከል የኖ ረው ያለ ፍርሃት ነበር። ተካ ለመጨረሻ ጊዜ ሲጸልይ የሰማሁት፣ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ መቼ ነው የማይህ? በፊትህ ለመቆም እፈልጋለሁ። አንተ ሕይወቴ ነህ፣ ብቸኛው ደስታዬም አንተው ነህ» የሚል ነበር።

አንድ ጊዜ አብረን ከቦዲ ወደ ዲማ ስንሄድ በተራራ ላይ ቁጭ ብለን አረፍ አልን። በዚያ ሆነን በኦሞ ወንዝ ሸለቆ በብዙ ኪሎ ሜትሮች ላይ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተዘናፈለ በነፋስ የሚወዛወዘውን ሰንበሌጥ ማየት ቻልን። ተካ በአገጩ በቀጣዩ ተ ራራ ላይ ያለውን መንገድ አሳየንና፣ «እግዚአብሔር ቦዲዎችን እንዳልፈራ ያደረገኝ እዛ ተራራ ላይ ነበር» አለ። «እንዴት?» ስል ጠየቅኩት።



«ቦዲዎች በማሉ፣ በባስኬቶ፣ በዲማና በካፋ ሁሉንም ነገር እያተራመሱ ወረራ ሲያካሄዱ ነበር። ወዳጄ ናናን በቦዲ መንደር ከያዙት በኋላ እኔን ግን ወደ ቡልቂ ሄጄ መድኃኒትና ምግብ እንዳመጣ ፈቀዱልኝ። ስሄድ ሳለሁ ጠመንጃ የያዙ ሦስት የቦዲ ሰ ዎችን አለፍሁኝ። ስለሚያውቁኝ እንዳልፍ ፈቀዱልኝ። ወዲያውኑ ከፍተኛ ጩኸትና ብጥብጥ ሰማሁ። ከፊቴ ባለው መንገድ ላይ ጠመንጃዎችን የያዙ ዘጠኝ የቦዲ ሰዎች አንድ የዲማ ሰው ይዘው ክፉኛ በመደብደብ ላይ ነበሩ። ሰውዬው ክርስቲያን ወዳጄ ቢሆንም፣ ምንም ነገር ላደርግለት አልቻልኩም። አጥንቶቹ ተሰባብረዋል። ደሙ በየቦታው ተዘርቶአል። ከመድረሴ በፊት ብዙ ካሠቃዩት በኋላ ገድለውታል» አለ።

ተካ ትእይንቱን አስታውሶ አለቀሰ። «እጅግ ፈርቼ እንቀጠቀጥ ጀመር። ዛሬ የመሞቻዬ ቀን ነው ብዬ በማሰብ መንገዱን ትቼ ወደ ሰንበሌጡ ዘልዬ ገባሁ። እጅግ ከመፍራቴ የተነሣ መንቀጥቀጤን ለማቆም አልቻልኩም። በእጆቼና በጉልበቶቼ በመሬት ላይ በመንበርከክ ወደ ጌታ ጸለይኩ። አፌ ይከፈታል፣ ይዘጋል። ድምጼን ግን መስማት አልቻልኩም። መተንፈስ አቃተኝ። እጆቼ እዚያና እዚህ ይዘረጋሉ። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ይህን ፍርሃት ከእኔ ውሰድና ሰውነቴን አረጋጋው። ለአንተ ታማኝ በመሆን ዛሬም ሆነ ወደፊት ወንጌልህን እሰብካለሁ። ቢገድሉኝ እንኳ ወደ አንተ በመሄድ ፊት ለፊት አይሃለሁ። የማጣው ነገር አይኖርም ብዬ ጸለይኩ።»

በዚህ ጊዜ ጌታ ፍርሃቴን በማስወገዱ ሰላም ልክ እንደ ወንዝ ወደ ሕይወቴ ፈሰሰ። በአዲስ ጉልበት ከመሬት ተነሥቼ ወደ ሞት ስፍራ ሄድኩ። ዘጠኙ ሰዎች በእጆቻቸው ዱላዎችን፣ ጠመንጃ ዎችንና ጩቤዎችን ይዘዋል። ነገር ግን እኔን ሲያዩኝ፣ እነዚያ ሁሉ የቦዲ ተዋጊዎች ፊታቸውን አዞሩ። ሀፍረት ተሰማቸው። እኔም ስለ ድንቁ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ አዲስ የሕይወት መንገድ ነገርኳቸው። ከዚያም የወዳጄን አስከሬን አንሥቼ ወደ ቤቱ በመውሰድ ቀበርኩ። ቦዲዎች ለምን እንዳልፈሩኋቸው በማሰብ ተገ ረሙ። እኔ ግን ያን ዕለት ለዚህ ዓለም ሞቼ ነበር። ቤት፣ መሬት፣

ቤተሰብ፣ ሀብት የለኝም:: እኔ የኢየሱስ ብቻ ነኝ:: ወደፊት ለቦዲዎች ስለ እርሱ በመናገር ብቻ አገለግለዋለሁ::»

አሁን ተካ ትልቅ ሸክም ተሸክሞ በሰንበሌጡ ውስጥ በፍጥነት ይራመዳል:: ከእርሱ እርምጃ ለመስተካከል ቁና ቁና መተንፈስ ነበረብን:: ተካ በጊዩ አዲስ ተሠርቶ በተጠናቀቀው የአውሮፕላን ማረፊያ ላይ የቦዲ ተዋጊዎችን ተወዳድሮ ያሸነፈና በእንቁራሪት ዝላያ በአንዱ እናት ላይ ያለፈ ሰው መሆኑን አስታውሳለሁ:: ሕይወትን የማጣጣም ችሎታው ከፍተኛ ነበር:: ተካ በመሬት ላይ ቁጢጥ ብሎ በቀስታ አዲሱን የሕይወት መንገድ ሲያብራራ ወይም ወደ ቦዲዎች ቤት ሲገባ መመልከቴን አስታውሳለሁ:: ልክ እንደ ነቢዩ ሕዝቅኤል የጌታ እጅ በእርሱ ላይ ስለ በረታች በተቀመጡበት ይቀመጥ ነበር:: ራእዩ ወንጌል ላልደረሳቸው ጎሳዎች ወንጌሉን ማድረስ ነበር:: እነዚህ ወገኖች እርሱ በቅርቡ ሸሽቶ ከወጣበት መንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ነበሩ:: ተካ ስለ ኢየሱስ ለሰዎች ለመናገር የትም ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛ ነበር:: በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ወዳሉት ሌሎች የቦዲ ጎሳዎችም ሄዶ ወንጌሉን የመመስከር ምኞት ነበረው:: ከጉራ ተነሥቶ ያመራውም ወደዚያው ነበር::

ተካ የሞተው እንዴት ነበር? በዚያን ጠዋት ወተት ሲጠጣ ሳለ ዳኩባ የተባለ አንድ ወጣት ጫካ ውስጥ ሸምቆ ነበር የገደለው:: ተካ መንገድ ላይ ሳለ ይህ ወጣት በጥይት ደብድቦ ከገደለው በኋላ ልብሶቹን ገፍፎ ወሰደ:: የተካ ገዳይ ሰውነቱን በመተልተል ከልቡ የተወሰነውን ክፍል በላ:: ከደሙም የተወሰነውን ያህል ጠጣ:: በተካ ልብሶችና ደም ራሱን አጊያጊጦ የገዳይነት ክብር አገኘ:: አሟሟቱ ምን እንደሚመስል ዝርዝር መረጃ የለንም:: ተሠቃይቶ እንዳልሞተ ግን ተስፋ እናደርጋለን:: ነገር ግን ተካ በመንፈሳዊ ጨለማና በኃጢአት ውስጥ ላሉት ሰዎች ወንጌሉን ለመወሰድ ሲሞክር እንደ ተገደለ በእርግጠኝነት እናውቃለን::

ይህንን የምጽፈው በጊዩ ቦዲ በምትገኘው የጎጆ ቤቴ የአፈር ወለል ላይ ቁጭ ብዬ ነው:: ነገ ወደ ዲማ በመሄድ ተካ ወደ ጌታ እንደ ሄደ ለእናቱ፣ ለእኅቱና ለወንድሙ መናገር አለብኝ:: ይህ ቀላል ተግባር እንደማይሆንም አውቃለሁ:: ተራ አማኝ ሆኖ ከፍተ



ኛ የድፍረት ተግባራትን ላከናወነውና «ዓለም ላልተገባው» ወንድሜ ተካ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ:: ተካ የሚጸጸትበት ጉዳይ የለውም ብዬ አምናለሁ:: እጅግ የሚወደው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ «ከክርስቶስ ጋር መሆን የሚበልጥ» ነገር መሆኑን የሚናገረው ነው::

ለእነዚህ ምስኪን የቦዲ ሰዎች ወንጌሉን ለማዳረስ ራሳችንን ልንሰጥ ይገባል:: ጉራንና ሕዝቦቿን ለክርስቶስ እንዋጃቸው:: የተካ ደም ለእነዚህ የጠፉ ነፍሳት ምልክት በመሆን «የቤተ ክርስቲያን ዘር» እንዲሆንላቸው እንመኛለን:: ይህ እውን እንዲሆን የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለመክፈል ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እናድርግ::

*«እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ... አትረፉ፣ ለእርሱም እረፍት አትስጡ» (ኢሳይያስ 62:6-7)::*

## ድኅረ ታሪክ

አሁን ጊዜው ጥቅምት 2006 ነው:: ዛሬ አንዳንድ ነገሮች በቦዲ በጣም ተለውጠዋል:: ተካ ከተገደለ ከጥቂት ወራት በኋላ የደርግ መንግሥት ሚሲዮናውያንን ከኦሞ ወንዝ ሸለቆ አስወጣቸው:: ከዚያም ኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን አካባቢውን እንዲለቅቁ ተደረገ:: በዚህ ምክንያት ለ12 ዓመታት ያህል በቦዲ አካባቢ የምስክርነት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው አልነበረም - ምንም እንኳን ጀማሪና ናና በዲማ ገበያ አንዳንድ የቦዲ ሰዎችን ለመድረስ ቢጥሩም:: ከተለመዱት የወባና የሳንባ ነቀርሳ በሽታዎች በተጨማሪ የኮሌራ፣ የማጅራት ገትር እና የቢጫ ወባ በሽታዎች በመንሰራፋታቸው፣ አብዛኞቹ ከብቶች ሞቱ:: ይህ ደግሞ የቦዲ ጎሳዎች የአካባቢውን ጎሳዎች በበለጠ እንዲያጠቁ ገፋፋቸው::

የአካባቢውን ጦርነት ለማስቆም የታጠቁ ወታደሮች ወደ አካባቢው ተላኩ:: ወታደሮቹ ብዙ የቦዲ ታጣቂዎችን በመግደል የሸርም እና የጉራ ጎሳ መሪዎችን ይዘው አሰሩ:: በሃና የሚገኘው የፖሊስ ጣቢያ በሚገባ ተጠናከረ:: ሳምንታዊ ገበያ ተጀመረ:: አንዳንድ የውኃ ጉድጓዶች ተቆፈሩ:: ክሊኒክና የአንደኛ ደረጃ ት/ቤ

ትም ተከፈተ:: እያንዳንዱ በቦዲ ቤተሰብ ውስጥ የሚወለድ ሕጻን ወደ ትምህርት ቤት እንዲገባ መንግሥት ማስገደድ ጀመረ:: ቀስ በቀስ ነገሮች መሻሻል ጀመሩ:: ከሁለት ዓመት በፊት አሸዋ ለበስ የመኪና መንገድ ተሠራ:: ስለዚህ ዕቃዎች በመኪኖች ተጭነው መምጣት ጀመሩ:: ይህም ሀናን ጥሩ አነስተኛ ከተማ አደረጋት::

በ1991 የደርግ መንግሥት ሲወድቅ፣ ወንጌላውያን ከጎፋ፣ ማሎ፣ ባስኬቶና ዲማ ወደዚህ አካባቢ ተመልሰው ለመምጣት ቻሉ:: ሀናና ጊዩ ሲመጡ ብዙዎቹን ሰዎች ለማግኘት አልቻሉም:: አሁን ያለው አዲስ ትውልድ ነው:: አሁን «ጥንካሬ ለማግኘት ብሎ ትላልቅ ሰዎችን የመብላት» ዜና አይነሣም:: ከብት ለመዝረፍ ጦርነት ማካሄድም ቀረ:: የተወሰኑ የሸለቆው አካባቢዎች ከሩቅ አካባቢ ለመጡ ጎሳዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በቆሎ፣ የስኳር ድንችና ማሽላ አምራች ሆነዋል:: አንዳንድ የቦዲ ሰዎችም መሬት ማረስ እየተማሩ ናቸው:: የታጠቁ ወታደሮች ነፍሰ ገዳዮችን አድነው ሀና ለሚገኘው ፍርድ ቤት ያቀርባሉ::

ወንጌላውያን ተካ፣ ናና እና ጀማሪ ወደ ጌታ ሄደዋል:: ከመጀመሪዎቹ አገልጋዮች በጊዩ የቀረነው እኔ እና ካሳ ብቻ ነን:: ስድስት ጊዜያት ወደ ቦታው ተመላልሼ በመሄድ ወንጌላውያንን የማበረታታትና ወደ ሌሎች መንደሮች እንዲዘልቁ የማገዝ ሥራ ዎችን ሠርቻለሁ:: በጊዩ፣ በሃናና በሌሎች አያሌ ቦታዎች «የጸሎት ቤቶች» ተከፍተዋል:: የወጣቶች ቡድን አያሌ ታዳጊዎች በክርስቶስ አምነው የእግዚአብሔርን ቃል ሲከተሉ ለማየት ችሏል:: ወጣቶቹ ከሁሉም ጎሳዎች የተውጣጡ ቢሆኑም፣ አብዛኞቹ የጉራ ወጣቶች ናቸው::

በጥር 2005 አንድ የቆየና የተረሳ ጸሎቴ ተመለሰ:: ልጄ ጆን፣ ማሄና እኔ ተካ የተገደለበትን መንደር ለማወቅ ቻልን:: ተካ በሞተ በት ስፍራ ላይ ወደ ተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን አንድ ወንጌላዊ ይዞን ሄደ:: በጥይት እንደ ተመታ ምንም ሳይሠቃይ ሕይወቱ ወዲያው እንዳለፈ ለመረዳት ችለናል:: የቦዲ ሴቶች፣ «የሰ ዎችን ሥጋ ብዙ ጊዜ በልተናል:: እንደ ተካ የሚጣፍጥ ግን አላገኘ ንም» እያሉ የጨፈሩበትን ቦታ አየን::



የዚያ አካባቢ የመጀመሪያ አማኝ ጂንካ ወደሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተልኮአል:: እዚያ ሄደን ጎብኝተነዋል:: የሚገርም ነገር አየን! ቀደም ሲል ልክ እንደ ተያዩ ይገዳደሉ ከነበሩት አምስት የተለያዩ ጎሳዎች የተወጣጡ ተማሪዎች አሁን በክርስቶስ ወንድማማቾች ናቸው:: ማቤዩ በመካከላቸው ተ ቀምጧል:: የእግዚአብሔርን ቃል አብረው ይማራሉ:: አብረው ይጸልያሉ፣ አብረው ስፖርት ይሠራሉ:: በአንድ መኝታ ቤት ውስጥ አብረው ያድራሉ:: በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ሰላም ወረደ! ሰዎችን እንዲህ ሊቀይር የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው! ተካ በከንቱ አልሞተም!

*«ያልታወቁ ስንባል የታወቅን ነን፤ የምንሞት ስንመስል እነሆ ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ስንሆን አንገደልም፤ ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው::» 2ኛ ቆሮንቶስ 6:9-10*

# 13

# ጀማሪ

## የባህል ልዩነትና ቆራጥነት

*«እግዚአብሔርን ፈለግሁት፣ መለሰልኝም፣ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።»*

(መዝሙር 34:4)

*«እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፣ አብረኸኝ መከራ ተቀበል።»*

(2ኛ ጢሞቴዎስ 2:3)

*«መከራን ተቀበል፣ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፣ አገልግሎትህን ፈጽም።»*

(2ኛ ጢሞቴዎስ 4:5)

ጀማሪ የተወለደውና ያደገው ፍርሃት በነገሠበት ባህል ውስጥ ነበር። አባቱና ከእርሱ በፊት የነበሩት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ትውልዶች እንዲፈሩ ነበር የተነገራቸው። ሰይጣንን፣ የአያት ቅድማያቶችን መናፍስት፣ ክፉ መናፍስትን፣ ሞትንና በተለይም ጠንቋዮችን ይፈሩ ነበር። ጠንቋዮች ኃይለኞች፣ አደገኞችና ሁልጊዜም ለጨለማው ኃይላት የእንስሳት ደም መሥዋዕቶች እንዲቀርቡ ይጠይቁ ነበር።

አንድ ቀን ወንጌላዊ ናና ጀማሪ ወደሚኖርበት አካባቢ መጣ። ናና ለአካባቢው አዲስ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰብክ ጀመር። ጀማሪና ሌሎች ወጣቶች አዲሱን ትምህርት በጉጉት ከሰሙ በኋላ በአካባቢው ላሉት መንደሮች የምስራቹን



ያዳርሱ ጀመር። «ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰይጣን በላይ ብርቱ ስለሆነ ከፍርሃት ነጻ ሊያወጣንና አዲስ ሕይወት ሊሰጠን ይችላል» የሚለውን ዜና ለሕዝቡ ሁሉ አበሰሩ። አንዳንድ በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች ለወንጌሉ ምላሽ ሰጡ። ሁለት የሚሆኑ ቤተሰቦች አመኑ። ከዚያም አንድ ጠንቋይ በክርስቶስ አመነ። ኃይለኛው የማሎ አለቃም ወደ ክርስቶስ መጣ። ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስደት በመቀስቀሷ ብዙ ክርስቲያኖች ለሥቃይ ተዳረጉ። አንዳንድ የጸሎት ቤቶች ተቃጠሉ። ይህም ሆኖ የአማኞች ቁጥር እየጨመረ ሄደ። ናና እና ጀማሪ ሌሎችም ወጣት አማኞች ለወራት በተደጋጋሚ ታሰሩ። ከዚያም ጀማሪ ቡልቂ ወደሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ ከተማረ በኋላ ወንጌሉን መስበክ ጀመረ።

በ1975፣ በወንጌል ወዳልተደረሱ የቦዲ ሕዝቦች ለመጀመሪያ ጊዜ ባደረግነው የወንጌል አገልግሎት ጉዞ ላይ ናናም አብሮኝ ተሰማራ። በዚህ ጊዜ በታላቁ የኦሞ ወንዝ ሸለቆ ያሉትን ሰዎች ፍላጎቶችም ለመዳሰስ ሞክረን ነበር። ጀማሪና ወጣቱ የወላይታ ወንጌላዊ የሆነው ሙኔ በማሎ የወንጌሉን ተግባር ማከናወናቸውን ቀጠሉ። ናና በማሎ ቆይቶ አያሌ ወጣቶች «የክርስቶስ ወታደሮች» እንዲሆኑ አሠልጥኖአቸው ነበር። ከእነዚህም ውስጥ ጀማሪና ሙኔ ይገኙባቸው ነበር።

ከአንድ ዓመት በኋላ፣ ናና ቤተሰቡንና በማደግ ላይ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በማሎ ትቶ ለቦዲ ሰዎች ሊመሰክር ሄደ። ናና ጀማሪ አማኞችን በመጋቢነት እንዲያገለግል መረጠው። ወጣትና ዐይናፋር ቢሆንም፣ ጀማሪ ጠንካራ እምነትና ትልቅ የክርስቶስ ፍቅር ነበረው። ራሱ በመከራ የተፈተነ ሲሆን፣ ጀማሪ ለክርስቶስ ለሚሠቃዩ ሰዎች የእግዚአብሔርን የጸጋ መልእክት ይነግራቸው ነበር። ጀማሪ ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ መራ።

ብዙም ሳይቆይ ጀማሪ ከእኛ ጋር በጊዩ ላሉት ቦዲዎች ወንጌል ለመስበክ ስለ ፈለገ ተሰማራ። እዚያ ሲደርስ አብዛኞቹ የቦዲ ሰዎች በቁመት እንደሚበልጡት ሲያይ ተስፋው ቀዘቀዘ። ብዙ ሴቶችም በቁመት ይበልጡት ነበር። የቦዲ ሰዎች ቁጡዎችና አስፈሪዎች መሆናቸውን ተመለከተ። በአጭሩ ጀማሪ ላይ በመሳቅ በቅርቡ

«እንደሚበሉት» ይናገሩ ጀመር። ጀማሪ እንዲህ ዓይነት ጨካኝ ሰ ዎችን አይቶ ስለማያውቅ ፈራ። ተዋጊዎቹ ከከብቶቻቸው ላይ ትኩስ ደም ሲጠጡ ሲያይ በጣም ዘገነነው። ጀማሪ በዚህ ሁኔታ እውነተኛ ባህላዊ ቀውስ ሲደርስበት ያየሁት ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ሆነ።

ጀማሪ እንደ ተካ እና ናና በሆንሁ ኢያለ ይመኝ ነበር። እነርሱ እግዚአብሔር በቦዲ ሰዎች መካከል እንደሚሠራ የሚተማመኑ የማይፈሩ ቆራጥ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን ጀማሪ ከዕለት ዕለት የቦዲ ዎችን ዛቻ እየሰማ ሲሄድ ፍርሃቱ እየጨመረ ሄደ። ማታ መተኛት አቃተው። ምግብ አይመገብም። ለየት ያለ ድምጽ በሰማ ቁጥር ይበ ረግጋል። ከምንኖርበት ቤት አጠገብ ነበር የሚኖረው። የቦዲ ወጣቶች ጠመንጃ ተሸክመው ሲያልፉ በሚያይበት ጊዜ ሁሉ ጓዳ ውስጥ ይደበቅ ነበር። ጀማሪ እውነተኛ «የባህል ቀውስ» ያጋጠመው ሰው ነበር። በኢትዮጵያ ውስጥ ነው ወይ ያለሁት? ብሎ ያስብ ነበር።

ብዙም ሳይቆይ ጀማሪ አሞኛል አለ። ነገር ግን ምንም የሚታይ የሕመም ምልክት አልነበረውም። ናና፣ ተካ እና እኔ ብዙውን ጊዜ አብረን በመጸለይ ለደህንነቱ በእግዚአብሔር ላይ እንዲደገፍ መከርነው። ናናም በየቀኑ ይመክረውና ያጽናናው ነበር። ተካም በበኩሉ እርሱም እንዴት ቦዲዎችን ይፈራ እንደ ነበርና እንዴት እግዚአብሔር ከዚያ ፍርሃት ነፃ እንዳወጣው ነገረው። ነገር ግን ጀማሪ እየባሰበት ሄደ።

ፈሪነቱ ቢያሳፍረውም፣ ፍርሃቱን ሊቀበለውም ሆነ ሊያስወግደው ተሳነው። ሁላችንም አዘንንለት። ልንረዳው ስለ ፈለግን ጸለይንለት። እየከሳና እየተጎዳ ሲሄድ በመመልከታችን የበለጠ እንዳይታመም ፈራን። ጀማሪ ሁልጊዜም አንድ ሰው አብሮት እንዲሆን ስለሚፈልግ በቡድኑ ሥራ ላይ ጫና ፈጠረ። ከእኛ አንድ ሰው አብሮት ካልሄደ ውኃ የመቅዳት ወይም የማገዶ እንጨት የመሰብሰብ ተግባሩን ሁሉ ለመወጣት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ። ሁላችንም ልንረዳው ብንፈልግም፣ የምንናገረውም ሆነ የምናደርገው ነገር ለውጥ ሊያመጣለት አልቻለም።



ስለዚህ ወደ ቤት ልንልከው ወሰንን። ምናልባት ቤተሰቦቹና ወዳጆቹ ባሉበት ቦታ ጤንነቱ ይመለስለት ይሆናል ብለን አሰብን። ቀደም ሲል የነበረውን ያህል ጠቃሚ አገልጋይ እንዲሆን ነበር የፈለግነው። አንድ ማለዳ የቦዲ ሰዎች ምንም ሳያውቁ ጀማሪን ወደ ቤቱ ወደ ማሎ ላክን። ተካ እስከ ዲማ ድረስ ሲሸኘው፣ የዲማ አማኞች ደግሞ የቀረውን መንገድ አብረውት ተጓዙ።

ሁላችንም ከእንግዲህ ከጀማሪ ጋር አንገናኝም ብለን አስበን ነበር። ለብዙ ሳምንታት አንድ ሺህ ሜትር ርዝመት ያለውን የሚሲዮን የአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ለመሥራት ሰንበሌጡን በመመንጠርና ስፍራውን በማዘጋጀቱ ሥራ ላይ ተጠምደን ነበር። ይህ በከባድ የፀሐይ ንዳድ ውስጥ የሚካሄድ ከባድ ሥራ ነበር። ክሊኒክና ትምህርት ቤት ለመሥራት የሚያስችል ተጨማሪ ቦታም መንጥረን አዘጋጀን። ብዙ ሰዎች «የኢየሱስን ታሪክ» ንገሩን እያሉ ስለሚጠይቁን ለአካባቢው ሕዝብ የክርስቶስን ወንጌል ማካፈላችንን አላቋረጥንም ነበር።

አንድ ምሽት ከአምስት ወንጌላውያን ጋር እሳት ዳር ቁጭ ብዬ ስጫወትና ስጸልይ፣ ተካ ራቅ ብለው በጉራ ስለሚኖሩ የቦዲ ሰዎች ጠየቀ። እነዚህ እኛ ባለንበት የጊዩ አካባቢ ካለው የሽሪም ጎሳ ጋር አንድ ዓይነት ቢሆኑም፣ መጠነኛ ልዩነት ነበራቸው። ከኦሞ ወንዝ ሸለቆ በስተማዶ ካለው የኮንታ አካባቢ የሚሰረቁ ከብቶች ሁሉ የሚጠበቁት በጉራ መሆኑን ተረዳን። እንደ ሽሪም፣ ጉራ፣ ሀናና ጎልዲያ ላሉት የቦዲ ጎሳዎች ሁሉ ስንጸልይ ሳለ ተካ በተለይ ለጉራ ጎሳ በማሰብ ልቡን እያፈሰሰ ይጸልይላቸው ጀመር። እኛ ካለንበት ቀ ረብ ብለው ነበር የሚገኙት።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ ጉራ ሄዶ ስለ ክርስቶስ እንዲመሰክር ከእግዚአብሔር ጥሪ የደረሰው መሆኑን ነገረን። ቡድኑ እኔም ከእርሱ ጋር እንድሄድ ወሰነ። ጉዞው በጣም አደገኛ ሊሆን ይችል ነበር። ሌሎች ወንጌላውያን እዚያው ሆነው ለቦዲዎች መመስከራቸውንና ለእኛ መጸለያቸውን ይቀጥላሉ ።

መጀመሪያ ግን፣ በደቡብ በኩል ላለው የሙርሲ ጎሳ

ለሚያገለግሉ ወንጌላውያን ምግብ ማግኘት ነበረብን፡፡ ማሄ ሚስቶቻቸውንና ትንንሽ ልጆቻቸውን ይዘው ከመጡት ሁለት ወጣት የወላይታ ወንጌላውያን ጋር እዚያው ነበር፡፡ የሚሲዮን አውሮፕላኖች ምግብ ያቀርቡላቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የደርግ መንግሥት የትኛውም የሚሲዮን አውሮፕላን እንዳይንቀሳቀስ እገዳ ጣለ፡፡ አንዳንድ በሩቅ አካባቢዎች የሚገኙ ወንጌላውያን እገዳውን ሳያውቁ ምግብና መድኃኒት እንዲመጣላቸው ይጠባበቁ ነበር፡፡ ማሄና ጓደኞቹ የውኃ ሙላቱን ተቋቁመው ለማለፍ አልቻሉም፡፡ ሙሉ በሙሉ ተነጥለው ነበር የቀሩት፡፡ ያላቸውን ምግብ በሙሉ ጨረሱ፡፡ የሚበሉትን ሲያጡ ሕጻናት ማልቀስ ጀመሩ፡፡ አዋቂዎች ደግሞ ለርዳታ ወደ እግዚአብሔር መጮህ ያዙ፡፡ ማሄ አንዳንድ የጫካ ማር፣ ሥራ ሥሮችና ቅጠላ ቅጠሎች አመጣላቸው፡፡

እኔም ዙሪያ ጥምጥም መንገድ ተጉዤ በመሄድ ባርክ ፋንስቶክን በባኮ የሚሲዮን ጣቢያ አገኘሁ፡፡ መኪና እየነዳን በማኅ ሸለቆ በኩል ወደ ሙርሲ ለመድረስ ብንሞክርም፣ ሳይሳካልን ቀረ፡፡ መንገዱ ለብዙ ዓመታት ለመኪና ዝግ ሆኖ ስለ ቆየ፣ ትላልቅ ሰንበሌጦች ሸፍነውት ነበር፡፡ ወደ ጂንካ ከተማ ለመመለስ ተገደድን፡፡ ባርክ ባኮ ወደ ነበረው ቤቱ ተመለሰ፡፡ በሬዲዮ ለመገናኘት ተስማማን፡፡

ሁለት ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ይዤ እንደገና ለመሄድ ሞከርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ የያዝነው ቀለል ያለ ጭነት ነበር፡፡ መንገዱን አውቀዋለሁ ያለው በድሩ ወደ ሸለቆው ሲወርድ ጠፋበት፡፡ ለሁለት ቀናት በረዣዥም ሣሮች መካከል ስንቅበዘበዝ ከቆየን በኋላ ወደ ኋላ ለመመለስ ተገደድን፡፡ ሁሉም ነገር የሚያስጨንቅ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ውኃ አለቀብን፡፡ በመቀጠል ደግሞ ሬድዮአችን በአግባቡ አልሠራም አለ፡፡ ከዚያም እኔ በጠና ታመምኩ፡፡ በድሩም ከፍተኛ ትኩሳት አመመው፡፡ በመጨረሻው ላይ አጭር የሬድዮ መልእክት ወደ ባኮ ለማስተላለፍ ቻልን፡፡

በቀጣዩ ጠዋት ባርክ እኛን ለመርዳት በቅሎዎችን ይዞ መምጣት ጀመረ፡፡ ከፍተኛ ትኩሳትና የራስ ምታት እያሠቃየኝ እንደ ምንም ብዬ መኪናውን እየነዳሁ ሁለቱን ወጣቶች ይዤ ከሸለቆው ወጣሁ፡፡ ባርክ ያገኘን ጂንካ ከተማ ልንደርስ ስንል ነበር፡፡ በትልቅ ደስታ



ነበር የተቀበለን፡፡ መኪናውን ጂንካ በመተው በቅሎዎቹ ላይ ተቀምጠን ወደ ባኮ አመራን፡፡ በድሩና እኔ ወባ ታመን ተኛን፡፡ አውሮፕላናችን አዲስ አበባ እንዲያደርሰኝ አስቸኳይ የበረራ ፈቃድ ተሰጠው፡፡ ተሽሎኝ ምግብ ይዤ ወደ ጊዩ እስክመለስ ብዙ ሳምንታት አለፉ፡፡ አንዳንድ የዲማ አማኞች እህሉን በመሸከም ስለ ተባበሩ፣ ለማሄና ለሙርሲ አገልጋዮች አደረስን፡፡

አዲስ አበባ ሆኜ እያገገምኩ ሳለሁ ለጉራ ጉዞ የተሰጠው የቀጠሮ ቀን ደረሰ፡፡ በመሆኑም፣ ተካ ብቻውን ወደዚያው አመራ፡፡ ከዛ አልተመለሰም፡፡ ለእነዚያ በጨለማ ውስጥ ላሉት የቦዲ ሰዎች ወንጌሉን ይዞ እንደ ሄደ እዚያው ቀረ፡፡

ከዚያም ድንገት ጀማሪ ብቅ አለ፡፡ ማሎ ከሚገኘው ቤቱ ተነሥቶ ብቻውን በዲማና በቦዲ አልፎ ወደ ጊዩ መጣ፡፡ ስናየው ተገረምን፡፡ የተካን ቦታ ለመውሰድ መምጣቱን በትልቅ ፋከራ ነገረን፡፡ ጀማሪ በጣም ስለ ተለወጠ፣ ሁኔታው ሊገባን አልቻለም፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት «ፈሪ ጥንቸል» የነበረው ሰውዬ አሁን በጌታ ብርታት የሚደሰት ደፋር ሰው ሆነ፡፡ ለውጡን ያመጣው ምንድን ነው ብዬ ጠየቅኩት፡፡

በዚያን ምሽት በሚጤስ እሳት ዙሪያ ተቀምጠን ሳለ ጀማሪ ታሪኩን ነገረን፡፡ ምንኛ ታላቅ ምስክርነት ነው! የተካን መሞት ሲሰማ ጀማሪ መወራጨትና ማልቀስ ጀመረ፡፡ ብቻውን ከቤቱ አቅራቢያ ወዳለው ጫካ ሄደ፡፡ እዛ የሄደው ከጌታ ጋር ለመገናኘት ነበር፡፡ ስለ ፍርሃቱና ስለ ድክመቱ ንስሐ በመግባት ጌታ ፍርሃትን ከልቡ እንዲያስወጣ ጠየቀ፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሊቀጥል እንደማይችል በመግለጽ ጌታ ነጻ እንዲያወጣው ተማጸነ፡፡

ጀማሪ ፈገግ ብሎ፣ «ድንገት አይቼ የማላውቀው ሰላም ልቤን ሞላው፡፡ ሸክሙ ከእኔ ላይ ተነሣ፡፡ ትልቅ ደስታ ተሰማኝ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰላም ሕይወቴን ሞልቶታል፡፡ ጌታ ይመስገን፡፡ ፍርሃቱ ለቅቆኝ ሄዶአል» አለ፡፡ ጀማሪ በሚያንጸባርቅ ፈገግታ ሲፈካ፣ ሁላችንም አብረን ተደሰትን፡፡ በሚጸልይበት ጊዜ ሁሉ ሌላ ሰው ሆኖ ተገኘ፡፡ ዓላማውም ሁሉ ተቀይሮአል፡፡ በእግዚአብሔር እጆች

ውስጥ መሆኑንና ምንም የሚያጣው ነገር እንደሌለ አመነ::

ከዚያን ጊዜ ወዲህ ጀማሪ፣ ምንም ዓይነት ፍርሃት ፈጽሞ አይታይበትም:: በግልጽ ብቻውን ወደ ቦዲዎች ቤት ይሄዳል:: በዚህ አጭር ሰው ላይ የታየው ለውጥ ብዙዎችን አስደነቀ:: የቦዲ ሰዎች ሁልጊዜም ለድፍረት ትልቅ ክብር ይሰጣሉ:: ጀማሪ አንዳንዶቻችን ወደማንደፍራቸው ቦታዎች ብቻውን ይሄዳል:: ወደ ጉራና ሃናንም አልፎ ይሄዳል:: ስለ ተካ ሞት እውነተኛውን መረጃ ያገኘው ጀማሪ ነበር:: የገዳዩን ማንነትና የገደለበትን ስፍራ ለይቶ ለማወቅ የቻለውም እርሱ ነበር::

ጀማሪ የክርስቶስን ወንጌል በመቶዎች ለሚቆጠሩ የቦዲ ሰዎች አካፈለ:: ከአነስተኛ ጎጆአቸው ደጅ በመቀመጥ ወይም ከተዋጊዎቹ ጋር ጥላ ሥር በመሆን እግዚአብሔር ልጁ ኃጢአታችንን እንዲሸከምና እንዲሞትልን በማድረግ ስላሳየው ታላቅ ፍቅሩ ይነግራቸዋል:: በቤትና በጎረቤት ያሉት ሴቶች እንዲሰሙ ጭምር በማሰብ ድምጹን ከፍ አድርጎ ነበር የሚነግራቸው:: ከልጆች ጋር እየተጫወተ የክርስቶስን ታሪክ ይነግራቸዋል:: በሁሉም ነገር ጀማሪ የተካን ስፍራ ወሰደ::

ጀማሪ ከናና ጋር ተቀራርቦ ነበር የሚሠራው:: የደርግ መንግሥት የሚሲዮን ጣቢያዎችን ሲዘጋ፣ አብዛኞቹ ወንጌላውያን ከአካባቢው እንዲለቀቁ ተደረገ:: እኔ ጊዩን ለቅቄ ከወጣሁ በኋላ የደርግ ካድሬዎች ወንጌላውያንን ሁሉ ከቦዲ አካባቢ አስወጧቸው:: ጀማሪና ናና ወደ ማሎ ተመለሱ:: ይሁን እንጂ፣ በዲማ በሚውለው ወርሐዊ ገበያ ላይ እየተገኙ አንዳንድ የቦዲ አማኞችን ያበረታቱ ነበር::

አሁን ከ25 ዓመታት በኋላ፣ ጀማሪ የማሎ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አስተባባሪ ሲሆን፣ በቅርቡ አንዳንድ ወጣት ወንጌላውያንን ዲማና ቦዲ አካባቢዎች ወስዶአቸዋል:: ሠላሳ የዲማ አማኞችን ይዞ ወደ ሀና ከተማ በመሄድ ተትቶ የቆየውን የአየር ማረፊያ ጣቢያ እንዲጠርጉ አድርጓል:: ጀማሪ አሁንም በጠባብ የዲማና የቦዲ መንገዶች በመጓዝ ወንጌሉን ያካፍላል:: ሁልጊዜም



አዳዲስ አማኞችን በማበረታታት፣ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል፣ ስደት የደረሰባቸውን አማኞች በመርዳት የክርስቶስን መንግሥት ይገነባል:: እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር መከራን እየተቋቋመ ሲያገለግል፣ በማሎ የሚኖሩት ባለቤቱና ልጆቹ ያግዙታል::

## ድኅረ ታሪክ

ጥር 2005 እንደገና ወደ ዲማ ጌሮ ሄጄ ነበር:: ፊት ጀማሪን በዚህ ስፍራ አገኘዋለሁ የሚል እምነት ነበረኝ:: ነገር ግን ከመድረሴ ጥቂት ጊዜ በፊት ጀማሪ በትኩሳት በሽታ መሞቱ ተነገረኝ:: ወባ ነበር? መልሱን የነገረኝ ሰው አልነበረም:: ጀማሪ የተቀበረው ባለቤቱ ተሲሚቶ አሁንም በምትኖርበት በማሎ ነበር:: ከልጆቹ አንዳንዶቹ ገና ትምህርት ቤት ውስጥ ናቸው:: ነገር ግን ትልልቆቹ በክርስቲያናዊ አገልግሎት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ:: አንዱ በቡልቂ ከተማ ውስጥ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነው:: ተሲሚቶ ጀማሪን ያሳድድ ከነበረው ክፉ ጎረቤቷ እገድልሻለሁ የሚል ዛቻ ስለሚሰነዝርባት የጸሎት ድጋፍ ያስፈልጋታል:: አንድ ጊዜ ሊገድላት ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቶአል:: ይህንን የሚያደርገው ጀማሪና ናና ለመኖሪያ ቤትና ለእርሻ ማሳ እንዲሆን የመነጠሩትን መሬት ለመውሰድ ሲል ነው::

ሌላው ትሑትና ታማኝ ወንጌላዊ ወደ ሽልማቱ ሄዶአል ማለት ነው:: በእግዚአብሔር ጸጋ ለዘላለም አዳኙና ጌታው ባለበት በደስታ ሊኖር:: አጭሩ፣ ጉልበታሙና ኃይለኛው ወንጌላዊ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ በማገለገልግበት ጊዜ ከፍተኛ እገዛ አድርጎልኛል:: ስለ ተለየኝ በጣም አዝናለሁ:: ነገር ግን በክርስቶስ ወንጌል አብሬው ለመሥራት በመታደሌ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ:: የቦዲ ተዋጊዎች የእምነት ታሪክ ሲዘከር እግዚአብሔር ፍርሃቱን አስወግዶ የአንበሳን ልብ እንዲሰጠው የጠየቀውን የዚህን አጭር ሰው ስም ያህል አንጸባርቆ የሚታይ ሌላ ስም ሊኖር አይችልም!

14

# ናና

## ልዩ ጸሎት

*«እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም:: ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ... ይህ ችግረኛ ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው ከመከራውም ሁሉ አዳነው... ባለጠጎች ተራቡ፣ ደኸዩም:: እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ግን ከመልካም ነገር አይጎድሉም::»*

መዝሙር 34:4፣6፣10

ይህንን የምጠይቀው በልጅህ፣ በአዳኛችን፣ እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው:: አሜን::» ጸሎታችንን ጨርሰን መነሣት ስንጀምር ወንጌላዊ ናና በጸሎቱ ላይ ትንሽ ነገር ጨመረ:: «ጌታ ሆይ፣ ነገ ወደ ሸለቆው ስንወርድ፣ አንበሳን እንድናይ እርዳን:: አሜን» የሚል ነበር:: የስድስት ሰዎች ዓይኖች (የሌሎች ወንጌላውያንና የእኔ) በናና ላይ አረፉ::

በጊዩ እኔ እና ስድስቱ ወንጌላውያን እንደተለመደው የምሽት ጽሞናችን እናካፍላለን:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እናነብና ከግሩም የተስፋ ቃሎች አንዱን ወይም በምንባቡ ውስጥ የተመለከትነውን የጌታን ትእዛዝ እናነሣለን:: ከዚያም በቆሸሸው ወለል ላይ በጉልበታችንና በእጆቻችን ተንበርክከን እንጸልያለን:: ከዚያ በኋላ ናና ተጨማሪ ነገር ይናገራል:: «ይህ እንግዳ ጸሎት ነው:: ለምንድን ነው አንበሳ ለማየት የጸለይከው?» አልኩት:: ናና፣ «ከዚህ በፊት አንበሳ አይቼ ስለማላውቅና አንበሳ ለማየት ስለምፈልግ ነው» አለ::

በቀጣዩ ዕለት ናና፣ ደስታና እኔ ከሁለት ወራት በፊት



ወንድማችን ተካ ወደ ተገደለበት ወደ ጉራ ለመሄድ በማቀድ ላይ ነበርን:: የተገደለበትን ቦታና የገደለውን ወጣት ስም ገና መስማታችን ነበር:: በኦሞ ወንዝ ሸለቆ አካባቢ ወዳሉት የቦዲ የከብት ማጎሪያዎች ለመሄድና በሀና ከሚገኘው የፖሊስ ጣቢያ አልፈን ለመመለስ ፈለግን:: ወቅቱ ረኘም ጊዜ የቆየ የበጋ ወራት ማገባደጃ በመሆኑ በጣም ይሞቃል:: ነገር ግን ምቹ የሚባል ጊዜ መኖሩ ከቶ የማይመስል ነበር:: በጣም ሞቃት በመሆኑ ቢያንስ ብዙ የበረሃ ዝንቦችና የወባ ትንኞች አልነበሩም:: የከብት ግጦሽ ሣር በሙሉ ደርቀአል:: የውኃ ጉድጓዶችም እንደዚሁ:: የቦዲ ከብት አርቢዎች ከብቶቻቸውን የሚወስዱት ሣርና ቁጠማ ወዳለበት ኦሞ ወንዝ ዳርቻ ነበር:: የፀሐይዋ ግለት፣ ከየድንጋዩ ወደ ዓይናችን የሚወረወረው የፀሐይዋ ነጸብራቅ፣ አቧራው፣ በሰውነት ላይ የሚጣበቁ ዝንቦች፣ እሾሃማው ቁጥቋጦ፣ ድካሙና ቀጥሎ ስለሚከሰተው ነገር እርግጠኛ አለመሆኔ ተደምረው ያስጨንቁኝ ነበር:: አሁን ደግሞ ናና አንበሳን ለማየት ጸልዮአል!

«ግን አንበሳ አይተህ ታውቃለህ አይደል?» ስል ናናን ጠየቅኩት:: ብዙ ጊዜ በጊዩ በሚገኙት የሣር ጎጆዎቻችን አጠገብ አንበሶች ማታ ማታ የሜዳ አህያዎችን ሲያባርሩ እንሰማለን:: ጠዋት ስንነሣ በበራችን አልፈው መሄዳቸውን የሚሳይ ዱካ እናገኛለን:: ናና፣ «አንበሳ አይቼ አላውቅም:: ሲያጓራና ዜብራ ወይም አጋዘን ሲያባርር እሰማለሁ:: ሣሮችን እያተራመሰ ሲሄድ አይቼ አውቃለሁ:: ግን አንበሳ አይቼ አላውቅም» አለ::

ይህን ማመን ለእኔ ቀላል አልነበረም:: የምንሠራበት ክፍለ ሃገር ጋሙ ጎፋ ይባላል:: (ይህ «አንበሳ» እና «የአንበሳ ጎፈር» ማለት ነው::) ይሁን እንጂ፣ ናና አንበሳ ሊያይ አልቻለም:: እኔም በበቅሎ ከቦታ ቦታ ስንቀሳቀስ ብዙ ጊዜ አንበሶች መንገዱን አቋርጠው ሲሄዱ መመልከቴንና በዛላ ከእኔ 20 ሜትር ራቅ ብሎ አንድ አንበሳ ጥጃ ተሸክሞ ሲሄድ መመልከቴን ነገርኩት:: ከዚያም በባስኬቶና ዲማ በሰንበሌጥ ውስጥ ከተካ ጋር ስናድር፣ አንበሶች በቅሎዬን ለማስበርገግ መሞከራቸውን ሁሉ አጫወትኩት:: አንበሶቹን ከእኛ ለማራቅ ስንል ሌሊቱን ሁሉ እሳት ስናነድ በሥቃይ ነበር

ያደርነው:: ከናና በስተቀር ሁላችንም በጊዩ ሌሊት የእጅ ባትሪዎ ቻችንን በምናበራበት ጊዜ አንበሶችን አይተናል::

አንድ ቀን በማዚ ወንዝ አካባቢ አንበሶች ልጆችን ሚሚን ሊይዙብን ነበር:: ላንድሮቨር መኪናችንን ከጭቃ ውስጥ ለማውጣት እየታገልን ነበር:: ለሰዓታት በጭቃ ውስጥ ተይዘን ነበር የቆየነው:: በኋላ ላይ ሚሚ ወደ ወንዙ አቅጣጫ አመራች:: በዚህ ጊዜ አንበሶች ከሣር ውስጥ ሆነው ማጓራት ጀመሩ:: እኛም እየተ ጯጯህን ወደ እርሷ ሩጠን በመሄድ ይዘናት ወደ መኪናው ከነፍን:: የመኪናውን ሞተር በማስነሣት፣ መብራቶችን በማብራትና ጥሩንባ በመንፋት አንበሶቹን ለማስፈራራት ሞከርን! ይህም ሆኖ ናና አንበሳ ማየት ይፈልጋል:: እናም፣ «ጌታ ጸሎትህን ይስማ» አልኩትና ተኛን::

ከወራት በፊት ወንጌላዊ ማሄ ወደ ቦዲ የምወስደው በቅሎ ገዝቶልኝ ነበር:: ነገር ግን ከአደገኛ የበረሃ ዝንቦች የተነሣ ብዙ ጊዜ የመቆየት ዕድል አልነበረውም:: ከአውሮፓ የመጣልኝን መድኃኒት እየወጋሁት ለስድስት ወራት ያህል በቅሎውን በሕይወት አቆየሁት:: ወደ ተለያዩ ቦታዎች ስንሄድ በቅሎው ምግባችንን፣ መድኃኒት፣ ልብሶችና የውኃ ኮዳዎችን ይሸከምልን ነበር::

በመጀመሪያ ቀን ከጊዩ በሃና አጠገብ ወደሚገኘው የውኃ ጉድጓድ ለመድረስ 18 ኪሎ ሜትሮች ተጓዝን:: ከዚያም ዘንድ ስንደርስ መያዣዎቻችንን ሁሉ ውኃ ሞላን:: በአጠቃላይ በአሥራ ሦስት የቆርቆሮና በአምስት የባለ አንድ ሊትር ፕላስቲክ መያዣዎች ውኃ ሞላን:: የምናውቀው የመጨረሻው ውኃ ይሄ ነበር:: ነገር ግን በጉራ ሌላም ውኃ ይኖራል የሚል ግምት ነበረን:: ወቅቱ ቀንም ሆነ ማታ በጣም ይሞቃል:: ገና ከረፋዱ ላይ አብረን ለመጓዝ አልቻልንም:: ናና ቀስ እያለ ስለሚጓዝ ቆም እያልን መጠበቅ ነበ ረብን:: በሞቃታማው አየር አብዛኛው ውኃችን ተጠጥቶ አለቀ:: ወደ ማምሻው ሌላ የውኃ ጉድጓድ የግድ በፍጥነት ማግኘት ነበ ረብን:: በቅሎው ደክሞት አንገቱን ወደ መሬት ይደፋ ጀመር::

ያገኘነው የውኃ ጉድጓድ ሁሉ ደረቅ ነበር:: ሁሉም መንደርና



የከብቶች በረት ወና ሆነው ነበር:: ሰዎች ሁሉ ወደ ኦሞ ወንዝ የወ ረዱ መስሎን ነበር:: የምንከተለው መንገድ ስላልነበረ በጫካው ውስጥ ዝም ብለን መደናበር ጀመርን:: የሚቀረፍድ ሌሊት አሳለፍን:: ቀጣዩ ቀን ደግሞ ከዛ የከፋ ነበር:: ይህ ከሕይወቴ እጅግ አስከፊ ቀናት አንዱ ነበር:: ውኃችን በሙሉ አልቆ ነበር:: በሃና ወደ ነበረው የውኃ ጉድጓድ እንዳንመለስ ደግሞ በጣም ሩቅ ነበር:: በጣም ስለ ተጨነቅን ጌታ እንዲረዳን ጸለይን::

ከዚያም ናና ራሱን ሳተ:: ከእግሬ ሥር ተወላክፎ ሲወድቅ ነፍስ እንዲዘራ ለማስቻል ብዙ ደቂቃዎችን ወሰደብን:: እንደ ምንም ደጋግፌን ይዘነው ስንሄድ እንደገና ወደቀ:: የምትነድደው የቀትር ፀሐይ ለሁላችንም ከብዳ ነበር:: በቅሎው እንኳን በጣም ተዳክሞ እየተወላገደ ነበር የሚሄደው:: ከዚያም ብዙ ጥላ በሌለበት ቁጥቋጦ ሥር ቁጭ ብለን ለጥቂት ሰዓቶች አረፍን:: በዚህ ጊዜ በቅሎአችንም እንደ ተገነደሰ ግንድ መሬት ላይ ተከምሮ ተኛ:: ናና በጣም እንደ ደከመውና እዛ ትተነው መሄድ እንዳለብን፣ ውኃ ባገኘ ን ጊዜ ወደ እርሱ ተመልሰን ብንመጣ እንደሚሻል አሳሰበን:: ማናችንም በዚህ አሳብ አልተስማማንም:: አብረን እስካልቆየን ድ ረስ ተመልሰን ልናገኘው እንደማንችል ገለጽንለት:: ናናን ሱሪውን ከመቀመጫው በኩል ይዤ እየደገፍሁት የተወሰነ ርቀት አብረን ጉዞአችንን ቀጠልን:: አሁንም ናና ወደቀ:: መልሰን ለማስነሣት ብዙ ጊዜ ወሰደብን::

ቀጥሎ ያለው መጠነኛ ኮረብታ ነበር:: ደስታ በአገጩ እያመለከተ ወደዚያው ኮረብታ ብንወጣ ውኃ ወይም መንደር ልናይ እንደምንችል ነገረን:: በዚህ ጊዜ ሁላችንም ዝለን ነበር:: እኔ ያንን ዳገት ለመውጣት የሚያስችል ጥንካሬ እንዳልነበረኝና ሌሎችም ይችሉት እንደ ሆነ እጠራጠር ነበር:: ከንፈሮቻችን ስለ ተሰነጣጠቁና አፋችን ሁሉ ስለ ደረቀ መነጋገር ቀርቶ መተንፈሱም ከባድ ነበር:: በዚህ ላይ እንዳለን ናና እንደገና ራሱን ሳተ:: መሬቱ ላይ አጋደምሁትና መጸለይ ጀመርኩ:: ጌታ ምን ያህል እንደ ተጨነቅን ያውቅ ነበር:: ናና ነፍሱን ሲያውቅ ደግፌን አነሣነው:: ከኋላው ሆኜ በእጄ ደግፌው እኔም እየተጎተትሁ መሄድ ጀመርን::

ትንሽ ተጉዘን ወደ አንበሶች መናኸሪያ ደረስን:: በጣም የደነገጡት አንበሶቹ ይሆኑ እኛ የማውቀው የለኝም:: አንበሶቹ ከፀሐይ ሸሽተው ከቁጥቋጦው ሥር ተኝተዋል:: አሥር አንበሶች ነበሩ:: ሁለት ትላልቅ ወንዶች፣ ሁለት ትናንሽ ደቦሎችና ሴት አናብስት:: ሁለቱ ደቦሎች እየሮጡ ወደ እኛ መጡና በቅሎአችንን ማሽተት እና ማነፍነፍ ያዙ:: በዚህ ጊዜ በቅሎው ፈዝዞ ቀረ:: ዓይኖቹ ፈጠጡ፣ አፉ ተከፈተ፣ እግሮቹ ደረቁ፣ ጅራቱ ወደ ኋላ ተቀሰረ፣ ጆሮዎቹም እንደ ቀስት ተገተሩ:: ከዚህ በፊት አንበሶችን አይቶ አያውቅም ነበር:: አንበሶችም በቅሎ አይተው አያውቁም ነበር::

ናና በድንጋጤ አፉን ከፍቶ ቆመ:: ትልልቆቹ አንበሶች ደቦሎቻቸውን ከበቅሎው አጠገብ ሲመለከቱ የመከላከል አዝማሚያ አሳዩ:: ብድግ ብለው ካንሩ በኋላ ከሦስት አቅጣጫዎች ተነሡብን:: ናና አንድ እግሩን አየር ላይ እንዳኖረ ነፍሱ የለም! እኔም ብሆን በጣም ደንግጬ ነበር! እግሮቼ መሬቱ ላይ ተተክለው ቀሩ:: በድንገት ሁለት ትላልቅ ድንጋዮች እጄ ላይ መኖራቸውን አየሁ:: እንዴት እጄ ላይ እንደ ገቡ እግዜር ይወቀው:: ድንጋዮቹን ይዤ ግራ እንደ ተጋባች ሰጎን ጎንበስ ቀና፣ ወዲያ ወዲህ ብልም እግሮቼ ሊንቀሳቀሱልኝ አልቻሉም:: ሌሎቹ ወንጌላውያን በመጯጯህ በበቅሎው ላይ የነበረውን ቆንጨራ ለማውረድ ታገሉ:: አንበሶቹ አሁን ዘልለው እኛን ለመቦጫጨቅ አየር ላይ ነበሩ:: እኛ ደግሞ መንቀሳቀስ አልቻልንም!

የሚገርመው እጅግ የደነገጠው በቅሎ እኛን ማዳኑ ነው! ፈርከክ ብለው ደርቀው የነበሩ እግሮቹ ድንገት መወርወር ጀመሩ:: በድንጋጤ ዘልሎ አንድ ሜትር ያህል ወደ ላይ ተነሣ:: ከዚያ ሲመለስ ባዶዎቹ የውኃ መያዣዎች የሚያስፈራ ከፍተኛ ድምፅ አሰሙ:: ደቦሎቹ ፈርተው ትልልቆቹን አንበሶች አልፈው መሮጥ ጀመሩ:: በቅሎው የፈጠረው ከፍተኛ ድምፅና የደቦሎቹ መፈርጠጥ አንበሶቹ ለመሸሽ እንዲከጅሉ አደረጋቸው:: አንዳንዶቹ በአየር ላይ እንዳሉ አቅጣጫቸውን ሲቀለብሱ፣ ሌሎቹ በአየሩ ላይ ዘልለው እያጓሩና ሹሎቹ ጥፍሮቻቸው እያፏጩብን አልፈውን ሄዱ::



በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት በጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ ተተውን ጫካው ውስጥ ተሰወሩ::

ለጥቂት ሰኮንዶች እዚያው ቆመን ቀረን:: ናና አሁንም ክንዶቹ በአየር ላይ እንደ ተዘሩ ናቸው:: ዓይኖቹ ፈጥጠዋል:: የእኔም እግሮች አሁንም ከመሬቱ ላይ እንደ ተተከሉ ናቸው:: ነገር ግን ድንጋዮቹን ጥዬአቸዋለሁ:: ከዚያ በኋላ ያ ሁሉ ግራ መጋባት ተወገደ:: መንቀሳቀስ አቅቶት የነበረው ናና በሚገባ መራመድ ጀመረ:: በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ከሁላችንም ቀድሞ ከተራራው ጫፍ ላይ ደረሰ:: እኔ ከእርሱ ኋላ ነበርኩ! በቅሎው ሁለታችንንም አልፎ ሄደ:: ሌሎቹ ወንጌላውያን በአንድነት በርብርብ መጨረሻ ደረሱ::

ሁላችንም በመሬቱ ላይ ተዘረርን:: «ናና ጌታ አለጥርጥር ጸሎትህን መልሶልሃል» አልኩት:: «አዎን፣ ጌታ ጸሎቴን ሰምቶ መልሶአል» አለ:: ከዚያ በኋላ ትእይንቱ ወደ ሳቅ ተቀየረ፡ ለ10 ደቂቃዎች ያህል ስንሳሳቅ ቆየን:: መሳቅ ብቻ ሳይሆን እናለቅስም ጀመር:: ይህ ከአደጋው የመዳናችን እፎይታ የፈጠረብን ስሜት ሳይሆን አይቀርም:: ናና እየዘለለ «አንበሳ!» ይላል:: ሌሎች ወንጌላውያን ቀጥ ብለው ተቀመጡ:: እንደገና መሳቅ ጀመርን! ከዚያ በኋላ ለቀናት ስለ አንበሶች ስናወራ ቆየን!

በአሾሃማ ቁጥቋጦዎች ውስጥ ስናልፍ የምንመለከተው ባዶ በረቶችንና ወና መንደሮችን ብቻ ነበር:: ምንም ውኃ የለም፣ ከእኛ ርቆ ከሚገኘው የኦሞ ወንዝ በስተቀር:: በቅሎው እያነፈነፈ ነጎደ:: ከ50 ሜትር ርቀት ያህል አካባቢ አንድ ኩሬ አገኘ:: ይህ የውኃ ኩሬ ነበረ ማለት አይቻልም:: በጠፍጣፋ ድንጋይ ውስጥ በአረንጓዴ ነገሮች የተሸፈነ ፈሳሽ ነገር ነበር፣ ውኃ ነው ማለት ግን አይቻልም:: ከብዙ ጊዜ በፊት ዝንጀሮዎችና ነብሮች በዚህ ስፍራ እንደ ነበሩ የሚያሳዩ ምልክቶች ነበሩ:: ከ20 በመቶው የሚበልጥ ውኃ እንደሌለው ግልጽ ቢሆንም፣ ለእኛ ግን ይህ እንደ ማር ምንጭ ነበር:: በጉጉት ከጠጣን በኋላ፣ ውኃ አጋር ክኒን ዋጥንበት:: ይህ የጌታ ስጦታ እንደ ሆነና ነፍሳችንን እንዳዳነልን ግልጽ ነበር:: ደስ ብሎን እግዚአብሔርን በአንድነት አመሰገንን:: በቅሎአችንም በጣም ጠምቶት ስለ ነበር ጥቂት ውኃ ጨምሮ ጠጣ::

ድካም ቢሰማንም፣ ከዳገቱ ደስ እያለን ወረድን:: ወደ ምሽቱ አካባቢ አንድ የቦዲ ተዋጊ አደን ሲያድን አገኘን:: ሰውዬውም አንበሶች ሲያገሱ ሰምቼ ነበር፣ በመንገዳችሁ አይታችኋቸዋል ሲል ደስታን ጠየቀው:: እንደ ዋዛ ማየት ብቻ ይባል! አዳኙ ወደ አንድ የውኃ ምንጭ ወሰደን:: ምንጩ በገደል ቋጥኝ መካከል ተደብቆ የሚፈስስ ነበር:: ውኃውን ስንጠጣ፣ ሻይ ስናፈላ፣ ሰውነታችንን ስንታጠብ፣ ኮዳችንን ስንሞላና አሁንም ጨምረን ስንጠጣ በዚያ ያሳለፍነው ጊዜ የፍጹም ደስታ ጊዜ ነበር:: እግዚአብሔርን ለቸርነቱ አመሰገንን:: ሌሊቱን በውኃው አጠገብ ባለው ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተኝተን አደርን:: ማንም ሰው ከውኃው ለመራቅ አልፈለገም:: ከመተኛታችን በፊት ናና እግዚአብሐርን ስለ አንበሶቹ አመሰገነ:: የተቀረነው ደግሞ በከረብታው ስላገኘነው የኩሬ ድፍድፍ ውኃና በምንጩ ስላገኘነው ንጹሕ ውኃ ጌታን አመሰገንን!



# 15

# ደስታ

## ስምም ቦታ አለው

*«እርሱም በመከራቸው ጊዜ ረዳታቸው ነው:: ስምህን የሚውቁ ሁሉ በአንተ ይታመናሉ :: አቤቱ የሚሹህን አትተዋቸውምና::»*

**መዝሙር 9:10**

*«እነርሱም ስሜን ይጠራሉ:: እኔም እሰማቸዋለሁ: እኔም ይህ ሕዝቤ ነው እላለሁ:: እርሱም እግዚአብሔር አምላኬ ነው ይላል::»*

**ዘካርያስ 13:9**

በጉራ ከነበረው ዳገት ላይ ደስታ፣ ናና፣ ማቱሴል እና እኔ የወረድነው በታላቅ የምስጋናና የእፎይታ ስሜት ነበር:: ከዚያ በኋላ አደን ላይ ያለ አንድ የቦዲ ጠረኛ አገኘን:: ግማሽ ሰዓት ከእኛ ጋር አብሮ ተጉዞ ከድንጋይ ወደሚፈልቅ ግሩም የምንጭ ውኃ አደረሰን:: በዚህ ስፍራ የፈለግነውን ያህል ውኃ ለመጠጣት ቻልን:: ሁላችንም በጣም ሞቆንና ተጠምተን ነበር:: ፀሐይ ስለ ጠለቀችና ስለ መሸ አዳኙ የቦዲ ሰው በፍጥነት ትቶን ጫካ ውስጥ ተሰወረ:: የት እንደ ገባ ቢገርመኝም፣ በጣም ስለ ዛልኩ በትክክል ለማሰብ እንኳን አልቻልም ነበር:: የፈለግኩት ነገር ቢኖር ቀዝቃዛውን ውኃ መጠጣትና አሁንም መጨመር ነበር:: የሁሉም ወንጌላውያን ስሜት ልክ እንደ እኔው ነበር::

ጠጥተን ከጠገብንና ሰውነታችንን ከታጠብን በኋላ፣ በጉልበታችን ተንበርክከን አብረን ጸለይን:: ናና ወደ ዳገቱ ሮጠን እንድንወጣ ስላስቻሉን አንበሶች እግዚአብሔርን አመሰገነ:: ደስታ

መጀመሪያ ስላገኘነው የኵሬ ውኃና ንጹሑን ምንጩን ስላሳየን የቦዲ አዳኝ አመሰገን:: ምንጩን ራሳችን ልናገኝ አንችልም ነበር::

በዚያን ሌሊት ከእሳት ዳር ተቀምጠን ሳለ አብዛኛው ጭውውታችን ያተኮረው በአንበሶቹ ላይ ነበር:: እንደገና እንዳይመጡብን ስለ ፈራን ሌሊቱን ሁለ እሳት ስናነድ አደርን:: በዚህ አስጨናቂ ጉዞ ወቅት ተካ የተገደለበትን ቦታ አላገኘንም:: መፈለጉም አስፈላጊ አልነበረም:: ቦታውን ያገኘነው ቆይቶ ከብዙ ጊዜ በኋላ ነበር:: ነገር ግን ተካ የፈለገውን ማለትም በጨለማ፣ በኃጢአትና በፍርሃት እስራት ውስጥ ያሉትን ክርስቶስ የሞተ ላቸውን ነፍሳት የማዳን ተግባር ለመፈጸም እንድንችል ጸለይን:: ከዚህ ዓለም ሥልጣናት፣ ከጨለማው ዓለም ኃይላትና ከክፉ መንፈስ ኃይላት ጋር እንደምንፋለም በግልጽ ታየን:: ልክ እንደ ተካ የክርስቶስን የማዳን ዜናና ስለ የሕይወት ውኃ ለአንዳንድ የቦዲ ሰ ዎች ለማካፈል ፈለግን:: ጌታ ወደ እነርሱ እንዲመራን ጸለይን::

ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ የቦዲው አዳኝ ተመልሶ ብቅ አለ:: ወደ መንደሩ እንድንመጣና ቦታውም ቅርብ እንደ ሆነ ጠየቀን:: ከቦታው ስንደርስ ሰዎች ዙሪያችንን ከበቡ:: ቀደም ሲል ያየነው በእድሜ ትልቁ የቦዲ አዛውንት ሉሺንዳም እዚያው ነበር:: ቀደም ሲል የጎሳው አለቃ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ግን እድሜው ገፍቶ ሰውነቱም በበሽታ ተሳስሮ ነበር:: ሌሎች ጎሳዎች ላይ ውጊያ በሚያካሂድበት ጊዜ ያጋጠመውን ጉዳት የሚጠቁሙ ጠባሳዎች በሰውነቱ ላይ እንደ ብጉር ያጎበጎቡ ነገሮች ያሉባቸው መስመሮች በረድፍ ይታያሉ:: እነዚህ ቆዳን እየበጡ ጥቃቅን ከሰሎች ከውስጥ በመቅበር የተፈጠሩ ምልክቶች ናቸው:: እያንዳንዱ ምልክቶች በጦርነት የተገደሉትን የሌላ ጎሳ አባላት ያሳያሉ:: እስከ መቶ ምልክቶች ከቆጠርኩ በኋላ ለመቀጠል ሳልችል ቀረሁ:: ሉሺንዳ በማርጀቱ ምክንያት ጦርነት ለመምራት ባለመቻሉ ልጁ በቦታው ተተክቶ ጎሳውን መምራት ጀመረ:: «ደሙን በመጠጣት የሉሺንዳን ጉልበትና ድፍረት ለማግኘት» ከሚፈልጉ ወጣቶች ልጁ ይጠብቀዋል::

ሉሺንዳ የወንጌሉን መልእክት ስንናገር በጥሞና አዳመጠን::



የኢየሱስን ምሳሌዎች ስንናገር ደስታ ያስተረጉም ነበር:: አንዳንድ የፈጸማቸውን የፈውስ ተአምራት ከተናገርን በኋላ፣ ሁልጊዜ እንደምናደርገው በትልቁ የሞቱና የትንሣኤው ታሪክ ደመደምን:: ሉሺንዳና ሕዝቡ ከዚህ በፊት የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ሰምተው አያውቁም ነበር:: ለጥቂት ሰዓታት ሉሺንዳ ስለ ኃጢአትና ንስሐ፣ የእግዚአብሔር ፍቅርና ይቅርታ፣ ስለ ሰላምና የዘላለም ሕይወት የተነገረውን መልእክት በጽሞና አዳመጠ:: ከዚያም ብዙ ጥያቄ ዎችን ጠየቀን:: በቦዲ ባህል መሠረት ስለ እያንዳንዱ ጉዳይ ከጎሳው አባላት ጋር ተወያየ::

ከዚያም ሉሺንዳ በኢየሱስ መንገድ ስለ መጓዝ ለቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሰጠ:: ኃጢአቱን በመናዘዝ ሰይጣንን፣ የደም መሥዋዕትንና የመናፍስት አምልኮን ካደ:: ሁለት እጆቹን ወደ ላይ በማንሣት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ተቀበለ:: ሞት ሳይቀድመን ስላገኘነው እግዚአብሔርን አመሰገንን:: ነገር ግን ሉሺንዳ ስለ ክርስቶስ ምን ያህል ገብቶት ይሆን? ብዬ አሰብ ጀመር:: ሁሉም ነገር በጣም አዲስ ነበር:: ነገር ግን ጌታ የሰውን ልብ ስለሚመለከት ስሙ ይመስገን:: የእግዚአብሔርን ግሩም የመዳን ስጦታ ለማግኘት የሚበቃው ትንሽ እምነት ብቻ ነው::

ከመሰናበታችን በፊት ለሉሺንዳ ጸሎት አስተማርን:: መጽሐፍ ቅዱስ የጌታን ስም የሚጠራ ይድናል ስለሚል በየቀኑ እንዲጸልይ መከርነው:: በመንደሩ ብዙ ብንቆይ ደስ ይለን እንደ ነበርና ዳሩ ግን ወደ ሌሎች አካባቢዎች መሄድ እንዳለብን ገለጽንለት:: ሉሺንዳን ለጌታ አሳልፈን በመስጠት አንድ ቀን ሁለት ወንጌላውያን መጥተ ው በመንደሩ ውስጥ በመኖር የበለጠ እንደሚያስተምሩት ተስፋ አደረግን::

በረዣዥም ሣሮችና እሾሃማ ቁጥቋጦዎች ውስጥ ፊትና ኋላ እየተራመድን ከኮረብታው ጫፍ ላይ ወጣን:: በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ሲጣራ ሰማን:: ሰውዬው የሚጣራው አሁን ትተን ከመጣነው የቦዲ መንደር ነበር:: የሚጣራው አዛውንቱ ሉሺንዳ ነበር:: «ስሙን እንደገና ንገሩኝ:: ስሙን ልረሳው እችላለሁ» አለ::

ደስታና እኔ አብረን ቆመን በአንድ ድምጽ፣ «ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ስሙ ኢየሱስ ነው። ወደ ኢየሱስ ጸልይ» አልን።

ከመንደሩ ውስጥ ወደ እኛ የሚነፍሰው ነፋስ «አዎ፣ ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱን እጣራለሁ። አሁን አልረሳም።» ሲል በጩኸት የተናገረውን የሉሺንዳን ምላሽ አስተጋባ።

ያ መንገድ እጅግ አድካሚ ከሆኑት ጉዞዎች አንዱ ሲሆን፣ በአደጋ ሊጠናቀቅ ነበር። ነገር ግን እጅግ ውጤታማ ከሆኑ ጉዞዎች አንዱ ሊሆን በቃ። ከዚያ በኋላ ለብዙ ጊዜያት ናና ስለ አንበሶች ያልም ነበር። እኔ ደግሞ፣ «ስሙን ንገሩኝ» ስላለው ሽማግሌ አልም ነበር።

> *«የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና። እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምስራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተ ብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?» (ሮሜ 10:13-15)።*



# 16

# ፋንታ

## ያልታሰበ ዕጩ

> *«ወንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁን ተመልከቱ። እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፣ ኃያላን የሆኑ ብዙዎች፣ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም። ነገር ግን እግዚአብሔ ር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ። ብርቱዎችን እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ። እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ።»*

> 1ኛ ቆሮንቶስ 1:26-28

ተቀመጥ፣ ጎረምሳው። ተቀመጥ። ልትሄድ አትችልም። ተቀመጥ።» ጉባኤውን የሚመራው መጋቢ ወጣቱ እንዲቀመጥ እንደገና እጁን በማወዛወዝ አሳሰበው። ነገር ግን ግራ ተጋብቶ ዙሪያውን እያየ ምርኩዙን እንደ ተደገፈ ቆሞ ቀረ። በዚህ ጊዜ አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ አዛውንት «ፋንታ፣ ቆይ። አሁን ዝም ብለህ ቁጭ በል» አሉ። ወጣቱ በሕዝቡ መሐል ተቀመጠ።

ይህ የሆነው በወላይታ ነው። ብዙ ሺህ ሕዝብ ለዓመታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፍረንስ ተሰብስቦ ነበር። ለአምስት ቀናት የእግዚአብሔርን ቃል አብረን በማጥናት፣ በመዝሙሮችና በምስክርነቶች ጌታን በማመስገን ግሩም ጊዜ አሳለፍን። በስብሰባዎቹ ወቅት ብዙ ስብከቶችን የማቅረብ ዕድል ነበረኝ። ከእነዚህ ስብከቶች አንዱ ወጣቶች አካባቢያቸውን ለቅቀው ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንደ ብሔራዊ የወንጌል መልእክተኛ በመሆን ወንጌሉን

እንዲወስዱ ጥሪ ያቀረብኩበት ነበር።

አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ዓይነቶቹን አገልጋዮች ወንጌላውያን ብለው ይጠራሉ። በእርግጥ ወንጌላውያን ናቸው። ነገር ግን ከምዕራቡ ዓለም እንደ መጣነው ሰዎች ሁሉ ሚሲዮናውያን መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። የራሳቸውን ጎሳ ወደ ኋላ ጥለው ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮችን በመጓዝ ከተለያዩ ሕዝቦች ጋር የሚኖሩ ናቸው።

አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በማይመቹ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ፣ ቋንቋዎችን ይማራሉ። ከዚህም በላይ፣ አንዳንድ ያልለመዷቸውን ምግቦች በመመገብ፣ ከእንግዳ ባህሎችና ልማዶች ጋር በመላመድ ደስታ የሞላበትን ሰላማዊ ሕይወት ይመራሉ። ይህም ሌሎች ለምን ይህን ዓይነት ሕይወት እንደሚኖሩና እንደ እነርሱ እንደማይፈሩ እንዲጠይቁ ያደርጋቸዋል። የወዳጅነት የወንጌል ስርጭት የምስራቹን ለማካፈል ከብዙ ሰዎች ጋር መተዋወቅን ያስችላል።

በሰዎች መሐል ቆሜ ወጣቶች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ አገልግሎት እንዲሰጡ ጥሪ አደረግሁላቸው። ከፊት የተቀመጡት ሽማግሌዎች፣ መጋቢዎችና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ነበሩ። ለሚሲዮናዊነት አገልግሎት ራሳቸውን ለሚሰጡት ሰዎች ቃል መጠይቅ የሚያደርጉት እነዚህ መሪዎች ነበሩ። ለወንጌል መልእክተኝነት ዕጩ በመመልመል አንዳንዶች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት እንዲገቡ፣ ሌሎች ደግሞ ተጨማሪ የስብከት ልምድ እንዲያገኙ ይመክሩአቸዋል። ለሚጠብቃቸው መከራ ዝግጁ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ደግሞ በቀጥታ በሥራው ላይ ያሰማሯቸዋል።

የባህል-ዘለል የወንጌል መልእክተኛ ለመሆን እንደሚፈልጉ በመግለጽ ወደ 20 የሚሆኑ ወጣቶች ወደ መድረኩ መጡ። ፋንታም ተነሥቶ ቆመ። መሪዎች ግን ቁጭ በል አሉት። በትሩን እንደ ያዘ ቆሞ ቀረ። በኋላ መሪዎቹ ለምን ሊቀበሉት እንዳልፈለጉ ተረድቼአለሁ። ፋንታ ሽባ ነበር። በስድስት ዓመቱ ነበር ለዚህ በሽታ የተጋለጠው። ይህ የሆነው ምናልባት ከፖሊዮ፣



ከማጅራት ገትር፣ ከአንጎል ወባ ወይም ከሌላ በሽታ የተነሣ ይሆናል። ከዚህም የተነሣ ግራ ጎኑ ሙሉ በሙሉ ሽባ፣ አቋሙም የተጣመመ ሆኖ ቀረ።

ለፋንታ የሚያስፈልገውን የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ ሰው አልነበረም። ቤተሰቡ እርሱን ወደ ከተማ ለመውሰድ የሚያስችል ገንዘብ አልነበረውም። ስለዚህ አንድ ክንዱና አንድ እግሩ ለምንም እንዳይሆኑ ደርቀው የአካል ጉዳተኛ ሆኖ አደገ። እነዚህ አካሎቹ ከጎኑ እንዲሁ የተንጠለጠሉ ነበሩ። ደግነቱ ፊቱ ደህና ነበር። የመናገርና ግሩም አድርጎ የመዘመርም ችሎታ ነበረው። ግራ እግሩን ግን እየጎተተ ነበር የሚሄደው። ስለዚህ ያውከው ነበር። ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ሲፈልግ ጠንካራ በሆነው ቀኝ እግሩ ቆሞ በትሩን ወደፊት አንድ ርምጃ ያክል ያንቀሳቅሳል። ከዚያም ግራ እግሩን እየጎተተ ወደፊት ይዘላል። ሚዛኑን መጠበቅ ሲችል፣ አሁንም ይህንኑ ያደርጋል። እንዲህ እያለ ይሄዳል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከአንድ ቦታ ለመድረስ የሚፈጅበት በጣም ረዥም ጊዜ ነበር። ስለዚህ ለአገልግሎቱ ብቁ ዕጩ ነው ማለቱ አስቸጋሪ ነበር። በአባጣ ጎባጣ የተራራ መንገዶች ላይ ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች በፍጥነት የሚራመዱትን ጠንካራ ሰዎች ነበር የምንፈልገው።

ለማሰብ ወይም ለመጸለይ ቆም ሳልል ፈጠን ብዬ ወደ ወጣቱ ልጅ በመሄድ ሽማግሌዎቹ የተናሩትን ደገምኩለት። ይህም ፋንታ የወንጌል መልእክተኛ ለመሆን እንደማይችል ነበር። በጸሎት ሊያገለግል እንደሚችል ነገርኩት። ፋንታ ግን ንግግሬን አቋረጠና እንዲህ አለኝ። «ከሁለት ዓመታት በፊት ስጠይቃቸው ሽማግሌዎቹ የነገሩኝ ይህንን ነበር። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንድገባ ነበር የነገሩኝ። ስለዚህ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቼ ትምህርቴን አጠናቀቅኩ። አሁን ለመሄድ ዝግጁ ነኝ። የእግዚአብሔር ቃል በልቤ ውስጥ ይቀጣጠላል። በብላቴ ወንዝና በአባያ ሐይቅ አካባቢ ወዳሉት አርብቶ አደሮች ለመሄድ እፈልጋለሁ። እነዚህ የወላይታ ሰዎች ጠላቶች መሆናቸውን አውቃለሁ። ይሁን እንጂ፣ ለእነርሱም ኢየሱስ ያስፈልጋቸዋል። እግዚአብሔር ወደ እነርሱ እንድሄድ ጠርቶኛል። እባክህን ሽማግሌ

ዎቹ እንዲልኩኝ ጠይቃቸው፣» ሲል ለመነኝ።

በኋላ እንደ ተረዳሁት ፋንታ ትምህርቱን የጨረሰው በከፍተኛ ውጤት ነበር። አሁንም በአገጩ ወደ ቆላማው አካባቢ እያመለከተ እግዚአብሔር የክርስቶስን ወንጌል ለአርብቶ አደሮች እንዲወስድ የሚፈልግ መሆኑን ነገረኝ። በአካባቢው የሚኖሩ የኦሮሞ ጎሳዎች የሌላ ጎሳ አባላትንና በሴቶች ኮንፍረንስ ውስጥ ከባለቤቴ ጋር የምትሠራውን የባሎቲን ባለቤት አሞቺን እንደ ገደሉ ስነግረው፣ ፋንታ ምንም ፍንክች አላለም። መሸሽም ሆነ ቆሞ መከላከል የሚችል አልነበረም። «እግዚአብሔር ሂድ ስላለኝ መታዘዝ አለብኝ! » አለ። እንድጸልይለትና ለሽማግሌዎች እንዳማልድለት ጠየቀኝ። ከዚያም በበትሩ እየዘለለ ሄደ።

ሁልጊዜም የጌታ ጸጋና ትዕግሥቱ ይገርመኛል። የእርሱ መንገዶች ከእኔ እጅግ የተለዩ ናቸው። እርሱ አይሳሳትም። በትክክለኛው ጊዜ ለእኛ የሚበጀንን ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ በእኔ አለማወቅና የእምነት ጉደለት ያዝናል። ከአንድ ዓመት በኋላ ለሚሲዮናዊነት ብቁ አይደለህም ካልነው ፋንታ ጋር እንደገና ተ ገናኘሁ።

ፋንታ እግዚአብሔር እንደ ጠራው እርግጠኛ ስለ ነበረ በአባያ ሐይቅ አካባቢ ወዳለው ቆላማ ስፍራ ብቻውን ሄደ። ከሌሎቹ ዕጩ ዎች ማንም ወደዚህ ስፍራ ለመሄድ አልደፈረም። ላለፉት ዓመታት እነዚህ አርብቶ አደር ዘላኖች በሐይቁ አካባቢ ያገኙአቸውን የሌሎች ጎሳዎች አባላትን ሲገድሉ ነበር የኖሩት። ፋንታ የሄደበት አካባቢ ለመድረስ ለጤነኛ ሰው የሁለት ቀን መንገድ ይሆናል። ለፋንታ ግን አምስት ቀናት ፈጀበት። ሲወድቅ ሲነሣ ነበር እዚያ የደረሰው። በመሆኑም፣ ሰውነቱ በመጠኑም ቢሆን መላላጥና መቆሳሰል ደርሶበታል። ከፊል – ዘላን የሆኑት እነዚህ አርብቶ አደሮች በኃይለኛ ስስት የሚጠብቋቸው ብዙ ከብቶች እንዳሏቸው ለመመልከት ቻለ። ተዋጊዎቹ ኃይለኞች ነበሩ። ከእነርሱ ውጭ የሆነውን ሰው እንደሚገድሉም እውነት ነበር። ምንም ጥያቄ ሳይጠይቁ እንግዳ የሆኑትን ሰዎች ስለሚገድሉ ወደዚ ለመሄድ የሚደፍር ሰው አልነበረም።



ነገር ግን የክርስቶስ ፍቅር ያስገደደው ይህ ወጣት ወደ እነርሱ ሄደ። ፋንታ የሚያጣው ነገር አልነበረም። ጌታ ጠርቶታል። ከጠራቸው ሰዎች ጋር አብሮ እንደሚሄድ ቃል ገብቶ የለምን? እነዚያ ጨካኝ ሰዎች ቢገድሉት ወደ ጌታው ይሄዳል። ፋንታ እነዚህ አርብቶ አደሮች ከሌሎች የተለየ አንድ አስደናቂ ነገር እንዳላቸው ተገነዘበ። ይህም ሽባ ሰዎችን የሚያከብሩ መሆናቸው ነበር። ምናልባትም ቀደም ሲል በአገራቸው ብዙ ሰዎችን ለሽባነት የዳረገ በሽታ (ምናልባትም ፖሊዮ ወይም የልጅነት ልምሻ) ኖሮ ይሆናል። ሌሎች ጎሳዎች ግን ሽባ ወይም የተበላሸ ቅርጽ ላላቸው ልጆች ምግብ በመከልከል በረሃብ ስለሚገድሏቸው እንዲህ ዓይነት ሰዎች አይኖሩአቸውም።

ፋንታ በእግዚአብሔር መንፈስ በመመራት እርሱ ብቻ ያለ ስጋት የሚኖርበትን ጎሳ አገኘ። የጎሳው አባላት ፋንታን በአክብሮት ነበር የተቀበሉት። በእነርሱ መካከል መኖር ለእርሱ ችግር አልነበ ረም። በተለያዩ መንደሮችና ከብቶች በሚጠበቁባቸው ስፍራዎች በመዘዋወር የወንጌሉን ታሪክ እየደጋገመ ይነግራቸው ነበር። ረጅም ጊዜ ቢፈጅበትም፣ በየእንስሳት ማሰሪያ በረቶች እየዞረ አርቢዎችን ይጎበኝ ነበር። ጌታ ምስክርነቱን በመባረኩ በአምስት መንደሮች ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ!

በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ 250 ሰዎች በክርስቶስ አመኑ። ብዙዎቹ በቀጣዩ ኮንፈረንስ ላይ ከፋንታ ጋር አብረው በመምጣታቸው ላገኛቸው ቻልኩ። አንዳንድ ሴቶች ከእንጨት ቅርፊት የተሠሩ ቀሚሶች ለብሰውና ከከብት ቆዳ የተሠሩ ቆቦችን አድርገው ነበር የመጡት። ወንዶቹ ደግሞ አጎዛ ለብሰውና መሣሪያ ዎቻቸውን ይዘው ነበር። ለኢየሱስ ክርስቶስ እየዘመሩ መጡ። በአንድ እግሩና በበትሩ እየዘለለ ከሚሄደው መሪያቸው ፍጥነት እኩል ለመራመድ በዝግታ እየተጓዙ መጡ። እኔም እንደገና በእግዚአብሔር ጸጋ ደስ ተሰኘኹ አንድ ሰው እርሱን እስከ ወደደና እስከ ታዘዘ ድረስ ሊጠቀምበት መቻሉን በመገንዘብ አመሰገንኩት። ሽማግሌዎቹ የተተወውን ዕጩ በመጨረሻው ላይ ተቀበሉት!

የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዳዲስ ክርስቲያኖችን

ማስተማር ፋንታን የሚረዳ ብሔራዊ የወንጌል መልእክተኛ በፍጥነት ላኩ። የመጀመሪያዎቹ 28 አማኞች በብላቴ ወንዝ በተ ጠመቁበት ሥነ-ሥርዓት ላይ እንድሰብክ መሪዎቹ ጋበዙኝ። ከወንዙ ማዶ ሁኔታው የገረማቸው ታጣቂዎች ቆመው ትእይንቱን ሲከታተሉ ነበር። በእኛ በኩል ታዳጊ ወጣቶች አዞዎች የጥምቀት ሥነ -ሥርዓቱን እንዳያስተጓጉሉ ወኃው ውስጥ ድንጋይ እየወ ረወሩ ተከላከሉልን።

ዛሬ በዚህ የኦሮሞ ጎሳ አካባቢ ከ20 የሚበልጡ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አግኝተው የመሪነት አገልግሎት ይሰጣሉ። አንዳንዶች የራሳቸውን ሰዎች በመጋቢነት በማገልገል ላይ ናቸው። ሌሎች ደግሞ የክርስቶስን ታሪክ ለመናገር ወደ ሌሎች አካባቢዎች ሄደዋል። ባለትዳርና የልጆች አባት የሆነው ፋንታ አሁንም በወቅቱ ከእርሱ በቀር ማንም በማይሄድበት ቦታ በማገልገል ላይ ይገኛል።

አምላካችን ምንኛ ታላቅ፣ ድንቅ፣ ኃይለኛና አፍቃሪ ነው! እርሱ ሁሉንም ስለሚያውቅ አይሳሳትም። እርሱ ሕዝቡን በትክክለኛው ጊዜና በትክክለኛው ስፍራ ላይ እንዲያገለግሉ ያስታጥቃል። የሚገባውን ክብርና ውዳሴ ለመስጠት በታማኝነት ደፋ ቀና የሚሉትን ተራ ሰዎች ይጠቀማል። ጌታ ሆይ፣ ልዩ፣ የደከሙና አካል ጉዳተኛ የሆኑ አገልጋዮችህን በብዛት እንድትሰጠን እለምንሃለሁ!